# የሰብአዊ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳኖች

**በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን የተዘጋጀ**

**ሕዳር 2001 ዓ/ም**

**አዲስ አበባ**

© የሰብአዊ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳኖች

በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን የተዘጋጀ

2001ዓ.ም.

ይህ ህትመት በዲሞክራቲክ ተቋማት ፕሮግራም ማዕቀፍ በኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን እና በተባበሩት መንግስታት ሰብዓዊ መብት ቢሮ ምስራቅ አፍሪካ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ትብብር ተዘጋጀ።

# መግቢያ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግስት ከሚታወቅበት ልዩ ባህሪ አንዱ ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸው ሁሉም የዓለም አቀፍ ቃል ኪዳኖች፣ ስምምነቶች፣ ፕሮቶኮሎችና ሌሎች ዓለም አቀፍ ሕጎች የኢትዮጵያ ሕጎች አካል አድርጎ የተቀበላቸው መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም ሕገ-መንግስቱ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያላቸው ሁሉም የሕግ እሳቤዎች ያካተተ ከመሆኑም በላይ የአገራችን ልዩ ውስጣዊ ሁኔታም በሚገባ የዳሰሰ እንደሆነ ይታወቃል፡፡

ይሁን እንጂ አገራችን የተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳኖችና ሌሎች መሰረታዊ ስምምነቶች በአንድ ተጠቃለው ለሕትመት ሳይበቁ ቆይተዋል፡፡ በመሆኑም እነዚህ የዓለም አቀፍ ስምምነቶች በማወቅና በመገንዘብ ረገድ ክፍተት ተፈጥሮ እንደቆየ መገንዘብ ይቻላል፡፡

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን ከሰብአዊ መብቶች መከበር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው ዓለም አቀፍ ቃል-ኪዳኖች አዘጋጅቶ የማሰራጨትና የማስተማር ኃላፊነት እንዳለው ይታወቃል፡፡ በዚሁ መሰረትም ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌ፣ የኢኮኖሚ፣ የማሕበራዊና የባሕላዊ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳን፣ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳን ጨምሮ ዘጠኝ ዓለም አቀፍ

ቃል ኪዳኖች በአማርኛ፣ በኦሮሚኛና በትግርኛ ቋንቋዎች ተተርጉመው ተዘጋጅተዋል።

እነዚህ ለሰብአዊ መብቶች መከበር ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያላቸው ጠቃሚ ዓለም አቀፍ ሰነዶች ለመላው ሕብረተሰብ፣ ሕግ በማስከበር ለተሰማሩ የተለያዩ አካላት፣ ለሰብአዊ መብቶች መከበር ትኩረት ሰጥተው ለሚሰሩ አካላት በተለይ ደግሞ ለአስተማሪዎችና የመለስተኛና ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳላቸው እናምናለን።

በመሆኑም የነዚህ ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳኖች ይዘት በመጨበጥ ከአገራችን ሁኔታ ጋር በማጣጣም በስፋት የሚተገበሩበትና ሰብአዊ መብቶች ማክበር ባህላችን ሆኖ የሚሰርፅበት ሁኔታ መፍጠር የሁሉም ሕብረተሰብ ጥረት መሆኑን ማስገንዘብ እንወዳለን።

አምባሳደር ካሳ ገ/ህይወት<br>
(ዶ/ር)<br>
የሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን ዋና<br>
ኮሚሽነር

## ማውጫ


**ገጽ**

1. ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌ.............................. **6**
2. የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊና የባሕላዊ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳን ................................................................................ **23**
3. የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳን .......... **53**
4. በሴቶች ላይ የሚደረግ ማንኛውንምአድሎአዊ ልዩነት ማስወገድ የተደረገ ስምምነት ................................................ **107**
5. ማሰቃየትና ሌሎች ጨካኝ፣ ኢ-ሰብአዊና አዋራጅ አያያዝና ቅጣት ለማስቀረት የተፈረመ ቃል ኪዳን .................................. **144**
6. የሕጻናት መብቶች ስምምነት ................................................. **185**
7. ሁሉም ዓይነት የዘር ልዩነቶች ለማስወገድ የተፈረመ ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳን ........................................................ **244**

# የሰብዓዊ መብቶች አለም አቀፋዊ
# መግለጫ

*በተባበሩት መንግስታት ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ ቁጥር 217 A (III) የፀደቀ*

## መግቢያ

የሰው ዘር በሙሉ አብሯቸው የተፈጠረ ክብር ያላቸው መሆኑን፣ እንዲሁም ከስብአናቸው ሊነጠሉ የማይችሉ እና እኩል የሆኑ መብቶች ያሏቸው መሆኑን አውቆ መቀበል ለነፃነት፣ ለፍትህ እና ለአለም ሰላም መሰረት በመሆኑ፣

ሰብአዊ መብቶችን ትኩረት አለመስጠት እና መናቅ የሰውን ልጅ ሕሊና ያስጨነቀ አረመኔያዊ ተግባሮችን በማስከተሉና የሰዎችም ከፍተኛ ፍላጎት የሰው ልጆች ሁሉ የንግግርና የእምነት ነፃነት የሚጎናጸፉበትና ከፍርሃትና ከችግር ነፃ የሚወጡበት ዓለም መፍጠር ነው ተብሎ በመታወጁ፣

የሰው ልጅ አምባገነንነትን እና ጭቆናን ለማስወገድ ሲል የአመፅን መንገድ መከተል እንደ የመጨረሻው አማራጭ እንዲወስድ የሚገደድበትን ሁናቴ ለማስቀረት ሰብዓዊ መብቶች በሕግ እንዲከበሩ ማድረግ ወሳኝ በመሆኑ፣

በአገሮች መካከል የወዳጅነት ግንኙነት እንዲስፋፉ ማበረታታት ወሳኝ በመሆኑ፣

የተባበሩት መንግስታት አባል አገሮች ህዝቦች በመሰረታዊ የሰብአዊ መብቶች፣ በሰው ሰውነት ክብር እና ልዕልና እና በፆታዎች እኩልነት ላይ ያላቸውን ፅኑ እምነት በቃል ኪዳኑ ውስጥ በድጋሚ በማረጋገጣቸው እና ሰፋ ባለ የነፃነት ሁኔታ የማሕበራዊ እድገትና የተሻለ የኑሮ ደረጃን ለማረጋገጥ በመወሰናቸው፣

ከተባበሩት መንግስታት ጋር በመተባበር አባል አገሮች ሰብዓዊ መብቶችና መሰረታዊ ነፃነቶች በመላው ዓለም እንዲከበሩና በተግባር እንዲተረጎሙ ለማድረግ ቃል በመግባታቸው፣

ይህ ቃል ኪዳን ሙሉ በሙሉ ግቡን እንዲመታ ስለ እነዚህ መብቶችና ነፃነቶች የጋራ ግንዛቤ እንዲኖር ማድረግ እጅግ አስፈላጊ በመሆኑ፣

ስለሆነም እነሆ

በአገር እና በአለም አቀፍ ደረጃ በሚወስዱ እርምጃዎች አማካኝነት የእነዚህ መብቶች እና ነፃነትቶች መከበር እንዲስፋፉ አቅዶ ማንኛውም ግለሰብ እና የህብረተሰብ አካል ስለነዚህ መብቶች እና ነፃነቶች ማስተማር ይችል ዘንድ፤ እንዲሁም በአባል አገሮችም ሆነ በእነሱ ቁጥጥር ስር በሚገኙ ግዛቶች ውስጥ በሚኖሩ ህዝቦች ዘንድ እነዚህ መብቶች በተሟላ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ የሚታወቁበትን እና በተግባር የሚውሉበትን ሁኔታ ማረጋገጥ ይቻል ዘንድ

የተባበሩት መንግስታት ጠቅላላ ጉባኤ ይህን የሰብዓዊ መብቶች አለም አቀፋዊ መግለጫ ለሁሉም ህዝቦችና አገሮች የጋራ መመሪያ እና የስኬት መለኪያ እንዲሆን አውጇል።

## አንቀጽ 1

ሰዎች ሁሉ እኩል ክብርና መብቶች ይዘው ነፃ ሆነው ተፈጥረዋል። የማመዛዘን ችሎታን እና ህሊናን በተፈጥሮ ስለታደሉ እርስ በርሳቸው በወንድማማችነት መንፈስ ሊተያዩ ይገባል።

## አንቀጽ 2

በዘር፣ በቀለም፣ በጾታ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ ወይም በሌላ አመለካከት፣ በብሄራዊ ወይንም በማህበራዊ አመጣጥ ፣ በሃብት፣ በትውልድ፣ ወይም በሌላ አቋም ምክንያት ምንም ዓይነት ልዩነት ሳይደረግ እያንዳንዱ ሰው በዚህ ድንጋጌ ውስጥ በተጠቀሱት መብቶችና ነፃነቶች የመጠቀም መብት አለው።

በተጨማሪም አንድ ሰው ነፃ በሆነ ወይም በሞግዚትነት አስተዳደር ስር ባለ፣ ወይም ነፃ ባልሆነ ወይም ማናቸውም ሌላ የስልጣን ልዕልና ገደብ በተደረገበት አገር ውስጥ የሚኖር ነው በሚል የአገሩን የፖለቲካ ግዛት ክልል ስልጣን፣ ወይም ዓለም አቀፋዊ

አቋሙን ምክንያት በማድረግ ምንም ዓይነት ልዩነት አይደረግበትም።

## አንቀጽ 3

እያንዳንዱ ሰው የሕይወት፣ የነጻነትና የደህንነት መብት አለው።

## አንቀጽ 4

ማንም ሰው በባርነት ወይም በግዴታ አገልጋይነት አይያዝም፤ ባርነትና የባሪያ ንግድ በየትኛውም መልካቸው የተከለከሉ ናቸው።

## አንቀጽ 5

ማንም ሰው ሊሰቃይ ወይም ጨካኝና ኢሰብአዊ በሆነ መንገድ ሊጉላላ ወይም ሊዋረድ ወይም ሊቀጣ አይገባም።

## አንቀጽ 6

ማንም ሰው በየትም ቦታ በሕግ ፊት ሰው ሆኖ የመታወቅ መብት አለው።

## አንቀጽ 7

ሰዎች ሁሉ በሕግ ፊት እኩል ናቸው፤ ያለምንም ልዩነት እኩል የሕግ ጥበቃ የማግኘት መብት አላቸው። ይህንን መግለጫ በመፃረር የሚደረግ ልዩነት እና ለልዩነት የሚያነሳሳ ተግባር እንዳይፈፀምባቸው እኩል የሕግ ጥበቃ ይደረግላቸዋል።

## አንቀጽ 8

ማንም ሰው በሕገ መንገስትም ሆነ በሌላ ሕግ የተሰጡትን መሰረታዊ መብቶች የሚጥስ ድርጊት በተፈጸመበት ጊዜ ስልጣን ላላቸው ያገሩ ፍርድ ቤቶች አመልክቶ ውጤታማ መፍትሄ የማግኘት መብት አለው።

## አንቀጽ 9

ማንም ሰው ከህግ ውጭ ሊያዝ፣ ሊታሰር ወይም ሊጋዝ አይችልም።

## አንቀጽ 10

ማንም ሰው በመብቶቹና ግዴታዎቹ እንዲሁም በተከሰሰበት ማንኛውም ወንጀል ውሳኔ ለማግኘት ሙሉ የእኩልነት መብቱ ተጠብቆ ነጻ በሆነና አድልዎ በሌለበት ፍርድ ቤት ሚዛናዊና ይፋ የሆነ ፍርድ የማግኘት መብት አለው።

## አንቀጽ 11

1. በወንጀል የተከሰሰ ማንኛውም ሰው ክሱ በይፋ በሚሰማበት ግልጽ ፍርድ ቤት በሕግ መሰረት የመከላከል መብቱ ተጠብቆለት ጥፋተኛ መሆኑ እስኪረጋገጥ ድረስ እንደ ጥፋተኛ ያለመቆጠር መብት አለው።

2. ማንም ሰው በአገር ውስጥ ሕግ ወይም በዓለም አቀፍ ሕግ ወንጀል መሆኑ ባልደተደነገገበት ጊዜ ለፈጸመው ማናቸውም ድርጊት ወይም ሳይፈጽም ለቀረው ማናቸውም ተግባር ጥፋተኛ ሊደረግ አይችልም። እንዲሁም ወንጀሉ በተፈጸመበት ጊዜ ከነበረው ቅጣት የበለጠ ቅጣት አይወሰንበትም።

## አንቀጽ 12

የማንም ሰው የግል ሕይወት፣ ቤተሰብ፣ መኖሪያ ቤት ወይም የመላላክ ግንኙነት ከሕግ ውጭ አይደፈርም፤ ክብሩና መልካም ስሙ እንዲጠፋም አይደረግም። እንደነዚህ ዓይነቶች መብቶች የመድፈርና ክብርን የመንካት ድርጊቶች እንዳይፈፀሙ እያንዳንዱ ሰው የሕግ ድጋፍ የማግኘት መብት አለው።

## አንቀጽ 13

1. ማንም ሰው በአገሩ ክልል ውስጥ በነፃ የመዘዋወርና የመኖር መብት አለው።

2. ማንም ሰው ከራሱም ሆነ ከሌላ አገር የመውጣትና ወደ አገሩም የመመለስ መብት አለው፡፡

## አንቀጽ 14

1. ማንም ሰው ከጥቃት ለማምለጥና በሌሎች አገሮች ጥገኛ ሆኖ ለመኖር የመጠየቅ መብት አለው፡፡
2. ይህ መብት ፖለቲካዊ አለመሆናቸው በግልጽ የሚታወቁ ክሶች ወይም የተባበሩት መንግስታትን ዓላማዎችና መሰረተ ሃሳቦች የሚቃረኑ ድርጊቶች በተፈጸመ ጊዜ አይሰራም፡፡

## አንቀጽ 15

1. ማንም ሰው ዜግነት የማግኘት መብት አለው፡፡
2. ማንም ሰው የዜግነት መብቱን በዘፈቀደ አይገፈፍም፤ ዜግነቱን የመለወጥ መብቱንም አይነፈግም፡፡

## አንቀጽ 16

1. በዘር፣ በዜግነት ወይም በሃይማኖት ምክንያት ገደብ ሳይደረግባቸው ዕድሜአቸው ለጋብቻ የደረሱ ወንዶችና ሴቶች ተጋብተው ቤተሰብ የመመስረት መብት አላቸው:: ጋብቻቸውን ሲመሰርቱ፣ ተጋብተው ሲኖሩና ጋብቻው ሲፈርስም እኩል መብት አላቸው::
2. ጋብቻ የሚፈጸመው ለመጋባት በበፈለጉት ሰዎች ነፃና ሙሉ ፈቃድ ብቻ ነው::
3. ቤተሰብ የአንድ ሕብረተሰብ መሰረታዊና ተፈጥሯዊ አካል ስለሆነ የሕብረተሰቡና የመንግስት ጥበቃ ሊደረግለት ይገባል::

## አንቀጽ 17

1. ማንም ሰው ብቻውንም ሆነ ከሌሎች ጋር በመተባበር የንብረት ባለቤት የመሆን መብት አለው::
2. ማንም ሰው በዘፈቀደ ንብረቱን እንዲያጣ አይደረግም::

## አንቀጽ 18

ማንም ሰው የሃሳብ፣ የሕሊናና የሃይማኖት ነፃነት መብት አለው፡፡ ይህ መብት ሃይማኖቱን ወይም እምነቱን የመለወጥን፣ እንዲሁም ለብቻው ወይም ከሌሎች ጋር በኅብረት፣ በግል ወይም በአደባባይ ሃይማኖቱን ወይም እምነቱን የማስተማር፣ በተግባር የማዋል፣ የማምለክና ሕጎቹን የመፈጸም ነፃነትን ይጨምራል፡፡

## አንቀጽ 19

ማንም ሰው አስተያየት የመስጠትና ሃሳቡን የመግለጽ ነፃነት መብት አለው፡፡ ይህ መብት እያንዳንዱ ሰው ያለምንም ተጽዕኖ አስተያየት እንዲኖረውና ጠረፍ ሳይወስነው በማናቸውም ዓይነት መገናኛ መረጃዎችና ሃሳቦችን የመፈለግ፣ የመቀበልና የማስተላለፍ ነፃነትን ይጨምራል፡፡

## አንቀጽ 20

1. ማንም ሰው በሰላም የመሰብሰብ እና ማኅበር የማቋቋም ነፃነት መብት አለው።
2. ማንም ሰው የማኅበር አባል እንዲሆን አይገደድም።

## አንቀጽ 21

1. ማንም ሰው በአገሩ መንግስት አስተዳደር ውስጥ በቀጥታ ወይም በነፃ በተመረጡ ወኪሎቹ አማካይነት የመሳተፍ መብት አለው።
2. ማንም ሰው በአገሩ መንግስታዊ አገልግሎቶች ከሌሎች እኩል የመጠቀም መብት አለው።
3. የመንግስት አስተዳደር ስልጣን መሰረቱ የሕዝብ ፈቃድ መሆን ይኖርበታል፤ የሕዝቡ ፈቃድ የሚገለፀውም በተወሰኑ ጊዜያት በሚካሄዱ ሃቀኛ ምርጫዎች ሲሆን፣ እነዚህ ምርጫዎች ለሁሉም ሰው እኩል እድል የሚሰጡና በምስጢር ወይም በተመሳሳይ ነፃ የምርጫ ስነ ስርዓት የሚካሄዱ መሆን አለባቸው።

## አንቀጽ 22

ማንም ሰው የኅብረተሰብ አባል በመሆኑ የኑሮ ዋስትና የማግኘት መብት አለው፤ ለክብሩና ለስብእናው ነፃ እድገት እጅግ አስፈላጊ የሆኑት የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊና የባህላዊ መብቶች እንደ እያንዳንዱ አገር የድርጅትና የሃብት ሁኔታ በብሔራዊ ጥረትና በዓለም አቀፋዊ ትብብር ሊሟሉለት ይገባል።

## አንቀጽ 23

1. ማንም ሰው ስራ የመስራት፣ ስራውን በነፃነት የመምረጥ፣ በትክክለኛና በአመቺ የስራ ሁኔታ ውስጥ የመስራትና ከስራ አጥነት የመዳን መብት አለው።
2. ማንም ሰው ያለምንም ልዩነት ለተመሳሳይ ስራ ተመሳሳይ ክፍያ የማግኘት መብት አለው።
3. በስራ ላይ የተሰማራ ማንም ሰው ራሱንና ቤተሰቡን ለሰው ልጅ ክብር በሚገባ የኑሮ ደረጃ ላይ ለማኖር የሚያስችለው ትክክለኛና በቂ ደመወዝ የማግኘትና

አስፈላጊም ሲሆን በሌላ የማኅበራዊ ድጎማ የመታገዝ መብት አለው።

4. ማንም ሰው የራሱን ጥቅሞች ለማስከበር የሰራተኛ ማኅበሮችን የማቋቋምና አባል የመሆን መብት አለው።

## አንቀጽ 24

ማንም ሰው ዕረፍትና የመዝናኛ ጊዜ የማግኘት መብት አለው፤ በቀን ለተወሰኑ ሰዓቶች ብቻ የመስራትና በየጊዜው ከክፍያ ጋር የሚሰጥ ዕረፍት የማግኘት መብትም አለው።

## አንቀጽ 25

1. ማንም ሰው ለእራሱና ለቤተሰቡ ጤንነትና ደኅንነት በቂ በሚሆን የኑሮ ደረጃ የመኖር መብት አለው፤ ይህም ምግብን፣ ልብስን፣ መጠለያን፣ የሕክምና አገልግሎትን፣ አስፈላጊ የሆኑ የማኅበራዊ አገልግሎቶችን ማግኘትና ለስራ አጥነት፣ ለሕመም፣ ለአካል መጉደል፣ ለባለቤት ሞት፣ ለእርጅና ወይም

ለሌሎች ከአቅም በላይ በሆነ ሁኔታ የሕይወት መሰረትን ለሚያናጉ ችግሮች ዋስትና የማግኘት መብትን ይጨምራል።

2. እናትነትና ልጅነት ልዩ ጥንቃቄና እርዳታ ያስፈልጋቸዋል፤ ልጆች ሁሉ በጋብቻም ሆነ ከጋብቻ ውጭ ቢወለዱ እኩል ማኅበራዊ ድጋፍ ያገኛሉ።

## አንቀጽ 26

1. ማንም ሰው የመማር መብት አለው። ቢያንስ በአንደኛና በመሰረታዊ ደረጃዎች ትምህርት በነፃ ሊሰጥ ይገባል። የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ግዴታ ይሆናል፤ የተግባረ ዕድና የሙያ ትምህርት በጠቅላላ እንዲዳረስ መደረግ ያለበት ሲሆን፤ የከፍተኛ ትምህርት ደግሞ በችሎታ ላይ ተመስርቶ ለሁሉም እኩል ዕድል እንዲሰጥ መደረግ አለበት።
2. ትምህርት የሰውን ልጅ የተሟላ እድገት ለማራመድ እና የሰብአዊ መብቶችንና መሰረታዊ ነፃነቶችን ለማክበር የሚደረገውን ጥረት ለማጠናከር የታቀደ መሆን አለበት። ትምህርት መግባባትን፣ በሕዝቦች፣ በተለያዩ ዘሮችና በሃይማኖቶች መካከል መቻቻልንና

ወንድማማችነትን ማበረታታትና የተባበሩት መንግስታት ለሰላም ጥበቃ የሚያደርገውን ጥረት የሚያራምድ መሆን ይገባዋል፡፡

3. ወላጆች ለልጆቻቸው የሚሰጠውን የትምህርት ዓይነት ለመምረጥ የቅድሚያ መብት አላቸው፡፡

## አንቀጽ 27

1. ማንም ሰው በኅብረተሰቡ ባህላዊ ህይወት በነፃ የመሳተፍ፣ በስነ ጥበቦቹ የመደሰት፣ በሳይንሳዊ እድገቱ የመሳተፍና በውጤቱም የመጠቀም መብት አለው፡፡
2. ማንም ሰው ራሱ የደረሰውን የሳይንስ፣ የስነ ጽሑፍ ወይም የስነ ጥበብ ውጤት የመንፈስና የገንዘብ ጥቅም የማስከበር መብት አለው፡፡

## አንቀጽ 28

ማንም ሰው በዚህ መግለጫ ውስጥ የተዘረዘሩት መብቶችና ነፃነቶች ሙሉ በሙሉ የሰፈኑበት ማህበራዊ እና አለም አቀፋዊ ስርዓትን የመሻት መብት አለው፡፡

## አንቀጽ 29

1. ማንም ሰው ለነፃና የተሟላ ስብእናው ብቸኛ መሰረት ለሆነው ማህበረሰብ ግዴታዎች አሉበት፡፡
2. የሌሎች ሰዎች መብቶችና ነፃነቶች እውቅና ለመስጠትና ለማክበር፣ የህዝብ ሞራልና ፀጥታ እንዲሁም በዴሞክራሲያዊ ማህበረሰብ ተቀባይነት ላላቸው መልካም ተግባራት ሲባል ብቻ በማንኛውም ሰው መብትና ነፃነት በሕግ ብቻ የሚቀመጥ ገደብ ሊኖር ይችላል፡፡
3. ከተባበሩት መንግስታት ዓላማዎችና መሰረተ ሃሳቦች ተቃራኒ በሆነ መንገድ በእነዚህ መብቶችና ነፃነቶች በምንም ዓይነት ሁኔታ መጠቀም አይቻልም፡፡

## አንቀጽ 30

በዚህ መግለጫ የተጠቀሰ ማናቸውም አንቀጽ አንድ መንግስት፣ ቡድን ወይም ግለሰብ እዚህ የተዘረዘሩትን ማናቸውንም መብቶችና ነፃነቶች ለመጣስ በሚያስችል ድርጊት ወይም እንቅስቃሴ የመሳተፍ መብት እን እንዳለው በሚያስመስል መንገድ ፈፅሞ መተርጐም የለበትም፡፡

# የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊና የባሕላዊ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳን

*በጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔ ቁጥር 2200 A (XXI) ዲሴምበር 16 ቀን 1966 ዓ.ም. (እ..አ.አ) ፀድቆ አባል አገሮች እንዲያፀድቁት እና እንዲቀበሉት የቀረበ*
*ስራ ላይ የዋለበት ዕለት: በአንቀፅ 27 መሠረት ጃንዋሪ 3 ቀን 1976 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ)*

## መግቢያ

### የዚህ ቃል ኪዳን አካል የሆኑ አገሮች

በተባበሩት መንግስታት ቻርተር በታወጁት መርሆዎች መሰረት የሰው ዘር በሙሉ አብሯቸው የተፈጠረ ክብር ያላቸው መሆኑን፣ እኩል እና ከስብእናቸው ሊነጠሉ የማይችሉ መብቶች የኗቸበው መሆኑን አውቆ መቀበል ለነፃነት፣ ለፍትሕና ለአለም ሰላም መሰረት መሆኑን በመገንዘብ፤

እነዚህ መብቶች ሰው በተፈጥሮ ከተጐናፀፈው ክብር የሚመነጩ መሆናቸውን በማወቅ፣

በሰብአዊ መብቶች አለም አቀፍ መግለጫ መሰረት ሰዎች ከፍርሃትና ከድህነት ነፃ ሆነው የሚኖሩበት ሁነኛው ዓለም ሊፈጠር የሚችለው እያንዳንዱ ሰው የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊ እና የባህላዊ መብቶቹን እንደሁም የሲቪል አና የፖለቲካ መብቶቹ ለመቀዳጀት የሚየስችለው ሁኔታዎች ሲፈጠሩለት ብቻ መሆኑን በማወቅ

ሰብዓዊ መብቶችና ነፃነቶች በመላው ዓለም እንዲከበሩና እንዲጠበቁ ለማድረግ በተባበሩት መንግስታት ቻርተር መሰረት አገሮች ያለባቸውን ግዴታ በመገንዘብ፣

ግለሰቡም ለሌሎች ግለሰቦችና ለሚኖርበት ሕብረተሰብ ኃላፊነት ስለአለበት፣ በዚህ ቃል ኪዳን የተደነገጉት መብቶች እንዲከበሩና እንዲጠበቁ የበኩሉን ጥረት ማድረግ ያለበት መሆኑን በመረዳት፣ በሚከተሉት አንቀጾች ላይ ተስማምተዋል፤

## ክፍል አንድ

## አንቀጽ 1

1. ሁሉም ሕዝቦች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት አላቸው:: ይህን መብት በመጐናፀፋቸው የፖለቲካ ህልውናቸውን በነፃነት የመወሰን፤ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ባህላዊ ዕድገታቸውንም በነፃነት የማራመድ መብት አላቸው::

2. ሁሉም ሕዝቦች በጋራ ጥቅም መርሆ ላይ የተመሰረተ ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ትብብር ግዴታቸውንና ዓለም አቀፍ ሕግን ሳይጥሱ የተፈጥሮ ሀብታቸውን ለራሳቸው ጉዳይ በነፃነት መጠቀም ይችላሉ:: በማንኛውም ሁኔታ ቢሆን አንድ ህዝብ ለኑሮው አስፈላጊ የሆኑትን የራሱን ጥቅሞች አይነፈግም::

3. ራሳቸውን ለማያስተዳድሩና በሞግዚት ለሚተዳደሩ ግዛቶች የማስተዳደር ሃላፊነት ያለባቸው አገሮችን ጨምሮ፣ የዚህ ቃል ኪዳን ተዋዋይ አገሮች ሁሉ የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት ከተባበሩት

መንግስታት ቻርተር ድንጋጌ ጋር በሚጣጣም ሁኔታ ተግባራዊ እንዲሆን ይጥራሉ፤ ይህንን መብት ያከብራሉ፡፡

## ክፍል ሁለት

## አንቀጽ 2

1. እያንዳንዱ የዚህ ቃል ኪዳን ተዋዋይ አገር በግሉ እና በተለይ ደግሞ ኢኮኖሚያዊ እና ቴክኒካዊ ድጋፍ በታከለበት አለም አቀፍ እርዳታ እና ትብብር አማካኝነት በእጁ የሚገኙትን ሃብቶች አሟጦ በመጠቀም፣ በዚህ ቃል ኪዳን ዕውቅና ያገኙት መብቶች ቀስ በቀስ በሙሉ ተግባራዊ እንዲሆኑ ሕግ ማውጣትን ጨምሮ ማናቸውንም ተገቢ እርምጃዎች ለመውሰድ ተስማምተዋል፡፡

2. የዚህ ቃል ኪዳን ተዋዋይ አገሮች በዘር፣ በቀለም፣ በጾታ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ ወይም በሌላ አስተሳሰብ፣ በብሔራዊ ወይንም በማህበራዊ አመጣጥ መነሻነት በሀብት፣ በትውልድ ወይም

በሌላ አቋም ምክንያት ምንም ዓይነት ልዩነት ሳይደረግ በዚህ ቃል ኪዳን የተደነገጉትን መብቶች ለማስከበር ተስማምተዋል።

3. በመልማት ላይ ያሉ አገሮች ሰብአዊ መብቶችንና ሃገራዊ ኢኮኖሚያቸውን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ዜጎቻቸው ያልሆኑ ሰዎች በዚህ ቃል ኪዳን ዕውቅና ባገኙት የኢኮኖሚ መብቶች ተጠቃሚ የሚሆኑበት ደረጃ ሊወስኑ ይችላሉ።

## አንቀጽ 3

የዚህ ቃል ኪዳን ተዋዋይ አገሮች ወንዶችና ሴቶች በቃል ኪዳኑ በተደነገጉት ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ባሕላዊ መብቶች እኩል ተጠቃሚ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ተስማምተዋል።

## አንቀጽ 4

አንድ አገር ይህንን ቃል ኪዳን ተከትሎ በሚደነግጋቸው መብቶች አጠቃቀም ላይ ከመብቶቹ

ባሕርይ ጋር በሚስማማ መልክ በሕግ በተወሰነው መሰረት ብቻና በዴሞክራሲያዊ ህብረተሰብ የጠቅላላውን ጥቅም ለመንከባከብ ሲባል ብቻ ገደብ ለመጣል ያለውን መብት የዚህ ቃል ኪዳን ተዋዋይ አገሮች ይቀበላሉ፡፡

## አንቀጽ 5

1. በዚህ ቃል ኪዳን የተጠቀሰ ማንኛውም ድንጋጌ ማንኛውም አገር፣ ቡድን ወይም ግለሰብ በቃል ኪዳኑ የተደነገጉትን ማናቸውንም መብቶችና ነፃነቶች ለመግፈፍ ወይም በቃል ኪዳኑ ከተደነገገው በበለጠ ሁኔታ ለመገደብ የታቀደ ድርጊት ለመፈፀም የሚያስችል መብት እንዳለው ተደርጎ ሊተረጎም አይችልም፡፡
2. በየትኛውም አገር በሕግ፣ በስምምነት፣ በደንብ ወይም በልማድ ተቀባይነት ያገኙትን መሰረታዊ ሰብአዊ መብቶች ይህ ቃል ኪዳን ዕውቅና አይሰጣቸውም ወይም እኩል አያያቸውም በሚል ሰበብ መገደብ ወይም መፃረር አይፈቀድም፡፡

## ክፍል ሶስት

## አንቀጽ 6

1. የዚህ ቃል ኪዳን ተዋዋይ አገሮች የመስራት መብትን ተቀብለዋል፡፡ ይህ መብት ማንኛውም ሰው በነፃ ፈቃዱ የመረጠውን ወይም የተቀበለውን ስራ ሰርቶ ሕይወቱን ለመምራት የሚያስችል የተመቻቸ ሁኔታ መፍጠርን የሚጨምር ሆኖ የዚህ ቃል ኪዳን ተዋዋዩ አገሮች ይህን መብት ለማስከበርም ተገቢውን እርምጃ ይወስዳሉ፡፡

2. የዚህ ቃል ኪዳን ተዋዋይ አገር ይህን መብት ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ለማድረግ የሚወስዳቸው እርምጃዎች፣ ለግለሰቡ መሰረታዊ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ነፃነቶቹን በሚያስጠብቁ ሁኔታዎች ቀጣይነት ያለው ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ባሕላዊ ዕድገትን የሚያስገኙና ምርታማ የስራ ዕድል የሚፈጥሩ የቴክኒክ፣ የሙያ አመራርን የስልጠና ፕሮግራሞችን፣ ዘዴዎችንና ፖሊሲዎችን መንደፍን የሚያካትት መሆን ይኖርበታል፡፡

## አንቀጽ 7

የዚህ ቃል ኪዳን ተዋዋይ አገሮች እያንዳንዱ ሰው በተለይ የሚከተሉትን የሚያረጋግጥ ፍትሓዊና አመቺ የስራ ሁኔታ የማግኘት መብት እንዳለው ተቀብለዋል፡፡

ሀ/ ለሁሉም ሰራተኞች የሚሰጥ ክፍያ ቢያንስ፡-

1. ምንም ዓይነት ልዩነት ሳይደረግ እኩል ዋጋ ላለው ስራ ተገቢ እና እኩል ክፍያ፣ በተለይ ሴቶች ወንዶች ከሚሰሩበት ባላነሰ የስራ ሁኔታ ውስጥ መስራታቸውና ለእኩል ስራ እኩል ክፍያ የሚያገኙ መሆኑን
2. በዚህ ቃል ኪዳን ድንጋጌዎች መሰረት ራሳቸውንም ሆነ ቤተሰቦቻቸውን በደህና ሁኔታ ለማኖር የሚያስችል ክፍያ  የሚያገኙ መሆኑን፣

ለ/  ከአደጋ ነፃ የሆነና ጤናማ የስራ ሁኔታ፣

ሐ/  ከአገልግሎት ዘመንና ከችሎታ በስተቀር ሌሎች መመዘኛዎች ከግምት ውስጥ ባለማስገባት እያንዳንዱ ሰራተኛ በተቀጠረበት ስራ ከፍ ወዳለ ደረጃ ለማደግ እኩል ዕድል ማግኘቱን፡፡

መ/ ዕረፍት፣ የመዝናኛ ጊዜና ተገቢ የሆነ የስራ ሰዓቶች ገደብ፣ በተወሰኑ ወቅቶች ከክፍያ ጋር የሚሰጥ ፈቃድ፣ እንዲሁም ለሕዝብ በዓላት የሚሰጥ ክፍያ ማግኘቱን

## አንቀጽ 8

1. የዚህ ቃል ኪዳን ተዋዋይ አገሮች የሚከተሉትን መብቶች ለማስከበር ተስማምተዋል

   ሀ/ ማንኛውም ሰራተኛ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጥቅሞቹን ለማስጠበቅ የሰራተኛ ማህበራትን ለማቋቋምና፣ የሚመለከተው ማህበር ደንቦች እስከፈቀዱ ድረስ፣ የመረጠው ማህበር አባል የመሆን መብት አለው:: በህግ ከተደነገገውና በዴሞክራሲያዊ ሕብረተሰብ ብሔራዊ ፀጥታን ወይም የህዝብን ሰላም ወይም የሌሎች መብትና ነፃነት ለማስከበር አስፈላጊ ከሆነው በስተቀር ምንም ዓይነት ገደብ አይደረግበትም::

   ለ/ የሰራተኞች ማህበራት ብሔራዊ ፌዴሬሽኖችን ወይም ኮንፌዴሬሽኖች የመመስረት መብት አላቸው፤ ኮንፌዴሬሽኖቹም ዓለም አቀፍ

የሰራተኛ ማህበራት ድርጅቶችን የመመስረት ወይም አባል የመሆን መብት አላቸው::

ሐ/ በሕግ ከተደነገገውና በዴሞክራሲያዊ ሕብረተሰብ ብሔራዊ ፀጥታን፣ የሕዝብን ሰላም፣ ወይም የሌሎችን መብትና ነፃነት ለማስከበር አስፈላጊ ከሆነው በስተቀር የሰራተኞች ማህበራት ምንም ዓይነት ሌላ ገደብ ሳይደረግባቸው በነፃነት የመንቀሳቀስ መብት አላቸው::

መ/ በሚመለከተው አገር ሕግ መሰረት የሚከናወን ስራ የማቆም አድማ መብት ይከበራል::

2. ይህ አንቀጽ የጦር ኃይል ወይም የፖሊስ አባላት ወይም የመንግስት አስተዳደር ሰራተኞች በእነዚህ መብቶች ስለሚጠቀሙበት ሁኔታ ላይ ሕጋዊ ገደቦች ማድረግን አይከለክልም::

3. በነፃ መደራጀትንና የመደራጀት መብትን ለማስከበር እንደ እ.ኤ.አ በ1948 ዓ/ም የተደረገው ዓለም አቀፍ የስራ ድርጅት ስምምነት ፈራሚ አገሮች በዚህ ስምምነት የተረጋገጡትን የመብት ዋስትናዎች የሚፃረር ሕግ እንዲደነግጉ ወይም ዋስትናዎቹን ሊፃረር በሚችል መልክ ሕጉን ስራ ላይ እንዲያውሉ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ አይፈቅድላቸውም::

## አንቀጽ 9

የዚህ ቃል ኪዳን ተዋዋይ አገሮች ማንኛውም ሰው ማህበራዊ መድንን ጨምሮ ማህበራዊ ዋስትና የማግኘት መብት ያለው መሆኑን ተቀብለዋል፡፡

## አንቀጽ 10

የዚህ ቃል ኪዳን ተዋዋይ አገሮች የሚከተሉትን ተቀብለዋል፣

1. ቤተሰብ የሕብረተሰብ መሰረት በመሆኑ በተለይ በሚመሰረትበት ጊዜና ለልጆች አስተዳደግና ትምህርት ኃላፊነትን በሚሸከምበት ጊዜ አቅም በፈቀደ መጠን ከሁሉም የሰፋ ጥበቃና ድጋፍ ሊሰጠው ይገባል፡፡ ጋብቻም በተጋቢዎቹ ፈቃድ የሚመሰረት ይሆናል፡፡
2. ለእናቶች ከወሊድ በፊትና በኋላ በቂ ለሆነ ጊዜ እንክብካቤ መደረግ አለበት፡፡ በዚህ ጊዜም ለሚሰሩ እናቶች ከደመወዝ ጋር ወይም ከበቂ የማህበራዊ ዋስትና ጥቅሞች ጋር ፈቃድ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

3. በወላጆቻቸው ወይም በሌላ ምክንያት ምንም ዓይነት ልዩነት ሳይደረግ ለሕፃናት እና አካለ መጠን ላልደረሱ ወጣቶች ልዩ ጥበቃና ድጋፍ የሚሹ እርምጃዎች ሊወሰዱ ይገባል፡፡ ሕፃናት እና ወጣቶች ከኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ብዝበዛ መጠበቅ አለባቸው፡፡ ለስነ ምግባራቸው ወይም ለጤንነታቸው ጎጂ፣ ወይም ለሕይወታቸው አደገኛ በሆነ ወይም የተፈጥሮ ዕድገታቸውን በሚያስናክል ስራ ላይ እንዲሰማሩ ማድረግ በሕግ የሚያስቀጣ ሊሆን ይገባል፡፡ እንዲሁም ለጋ ሕፃናትን በደመወዝ ቀጥሮ ማሰራት የሚከለከልበትንና የሚያስቀጣበትን ዝቅተኛ የዕድሜ ገደብ አገሮች መወሰን አለባቸው፡፡

## አንቀጽ 11

1. የዚህ ቃል ኪዳን ተዋዋይ አገሮች ማንኛውም ሰው በቂ ምግብ፣ ልብስና መኖሪያ ቤትን ጨምሮ ለራሱና ለቤተሰቡ በቂ በሆነ የኑሮ ደረጃ ለመኖርና የኑሮውን ሁኔታ ለማሻሻል መብት ያለው መሆኑን ያውቃሉ፡፡ አባል አገሮቹ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ዓለም አቀፍ ትብብርን አስፈላጊነት

ተገንዝበው የዚህ መብት ተግባራዊ ለማረጋገጥ ተገቢውን እርምጃ ይወስዳሉ።

2. የዚህ ቃል ኪዳን ተዋዋይ አገሮች ማንኛውም ሰው ሳይራብ ለመኖር ያለውን መሰረታዊ መብት በመገንዘብ በተናጠልም ሆነ በዓለም አቀፍ ትብብር አማካይነት የሚከተሉትን ለማሳካት ዝርዝር መርሃ ግብርን ጨምሮ አስፈላጊ እርምጃዎችን ይወስዳሉ፣

ሀ/ ቴክኒካዊና ሳይንሳዊ ዕውቀትን በመጠቀም የምግብ አመራረት፣ ክምችትና ስርጭት ዘዴን ለማሻሻል፣ የአልሚ ምግብ መሰረታዊ እውቀቶች ለማሰራጨት፣ እጅግ የተመጣጠነ የተፈጥሮ ሃብት ልማትና አጠቃቀም እንዲኖር የግብርና ስርዓቱን ለማሻሻል፣

ለ/ ምግብ አስመጪና ላኪ አገሮች የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች ግምት ውስጥ በማስገባት በፍላጎታቸው መሰረት የተመጣጠነ የዓለም የምግብ አቅርቦት ስርጭት እንዲኖር ለማረጋገጥ፣

## አንቀጽ 12

1. የዚህ ቃል ኪዳን ተዋዋይ አገሮች ማንኛውም ሰው ሊደረስበት ወደሚችል ከፍተኛ የአካልና የአእምሮ ጤንነት ወደ ተሟላበት የኑሮ ደረጃ የመድረስ መብት ያለው መሆኑን ያውቃሉ፡፡
2. ይህን መብት ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ለማድረግ በቃል ኪዳኑ ተዋዋይ አገሮች የሚወስዱት እርምጃዎች የሚከተሉትን ማካተት አለባቸው፡-
   ሀ/ ሞተው የሚወለዱትንና ከተወለዱ በኋላ የሚሞቱትን ሕፃናት ቁጥር መቀነስ እና የሕፃናት ጤና ዕድገት ማመቻቸት፣
   ለ/ የአካባቢና የኢንዱስትሪን ንጽሕና አጠባበቅ ማሻሻል፣
   ሐ/ ወረርሽኝን፣ አካባቢያዊና ከስራ ጋር የተዛመዱ በሽታዎችን መከላከል፣ ማከምና መቆጣጠር፣
   መ/ ሰዎች ሲታመሙ የሕክምና አገልግሎትና እንክብካቤ የሚያገኙበትን አስፈላጊ ሁኔታ ማመቻቸት፡፡

## አንቀጽ 13

1. የዚህ ቃል ኪዳን ተዋዋይ አገሮች ማንኛውም ሰው ትምህርት የማግኘት መብት ያለው መሆኑን ያውቃሉ፡፡ ትምህርት የሰውን ሰብዕናና የክቡርነት ስሜት ሙሉ በሙሉ ለማሳደግ በሚያስችል አቅጣጫ መመራት እንዳለበትና ለሰብአዊ መብቶችና መሰረታዊ ነፃነቶች የሚሰጠውን ከበሬታ የሚያጠናክር መሆን እንዳለበትም ተስማምተዋል፡፡ ትምህርት ማንኛውም ሰው በነፃ ሕብረተሰብ ውስጥ ፍሬያማ ተሳትፎ እንዲኖረው የሚያስችል፣ በሁሉም አገሮች፣ ዘሮች፣ ጎሳዎች ወይም የሃይማኖት ክፍሎች መካከል መግባባትን፣ መቻቻልንና ወዳጅነትን የሚያጠናክርና የተባበሩት መንግስታትን የሰላም ጥበቃ እንቅስቃሴዎች የሚያግዝ እንዲሆን ተስማምተዋል፡፡
2. የዚህ ቃል ኪዳን ተዋዋይ አገሮች ይህ መብት ሙሉ ለሙሉ እንዲረጋገጥ ለሚከተሉት ዕውቅና ይሰጣሉ፤
   ሀ/ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት መማር ለሁሉም ግዴታ ሆኖ ትምህርቱም በነፃ የሚሰጥ ይሆናል፡፡

ለ/ የቴክኒክና የሙያ ትምህርትን ጨምሮ በማናቸውም ተስማሚ በሆኑ ዘዴዎች በተለያየ መልኩ የሚሰጠው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በአጠቃላይ ለሁሉም ክፍት እና የሚዳረስ ይሆናል፣ ትምህርቱም ደረጃ በደረጃ በነፃ እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡

ሐ/ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ችሎታን መሰረት በማድረግ በማንኛውም አመቺ ዘዴ ለሁሉም ይዳረሳል፣ ትምህርቱም በሂደት በነፃ እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡

መ/ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን ያልተማሩ ወይም ያላጠናቀቁ ሰዎች በተቻለ መጠን መሰረታዊ ትምህርት እንዲከታተሉ ይበረታታሉ ትምህርቱም በስፋት እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡

ሠ/ ትምህርት ቤቶችን በየደረጃው የማስፋፋት ያልተቆጠበ ጥረት ይደረጋል፣ ብቃት ያለው የነፃ ትምህርት ስርዓት ይመሰረታል፣ የመምህራን የኑሮ ሁኔታም ያለማቋረጥ ይሻሻላል፡፡

3. የዚህ ቃል ኪዳን ተዋዋይ አገሮች ወላጆችና እነደነገሩ ሁኔታ ሕጋዊ ሞግዚቶች፣ መንግስት ካወጣው መሰረታዊ የጥራት መመዘኛ የሚያንስ እስካልሆነ ድረስ በማንኛውም ትምህርተ ቤት ልጆቻቸውን የማስተማርና እንደየእምነታቸውም የሃይማኖትና የግብረገብ ትምህርት እንዲማሩ የማድረግ መብታቸውን ለማክበር ተስማምተዋል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሱት መርሆዎች እስከ ተጠበቁና በትምህርት ተቋሙ የሚሰጠው ትምህርት መንግስት የወሰነውን መሰረታዊ የትምህርት ጥራት መመዘኛ እስካሟላ ድረስ፣ የዚህ አንቀጽ ማናቸውም ክፍል ግለሰቦችና ሌሎች አካላት የትምህርት ተቋማትን ለመመስረትና ለመምራት ባላቸው ነፃነት ውስጥ ጣልቃ ለመግባት እንደሚያስችል ተደርጎ ሊተረጎም አይችልም፡፡

## አንቀጽ 14

የዚህ ቃል ኪዳን እያንዳንዱ ተዋዋይ አገር የቃል ኪዳኑ አባል በሆነበት ግዜ ግዛቱ በሆነ ከተማ ወይም በሌሎች ግዛቶቹ ውስጥ ከክፍያ ነፃ የሆነ

የአንደኛ ደረጃ ትምህርት በግዴታ መስጠት አልቻለ እንደሆን፣ ይህን ለሁሉም ሰዎች ከክፍያ ነፃ የሆነ ትምህርት በግዴታ የሚሰጥበትን መርህ በተወሰኑ ዓመታት ውስጥ ደረጃ በደረጃ በስራ ለመተርጎም የሚያስችል ዝርዝር የስራ ዕቅድ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ አዘጋጅቶ ያፀድቃል።

## አንቀጽ 15

1. የዚህ ቃል ኪዳን ተዋዋይ አገሮች ማንኛውም ሰው፣

   ሀ/ በባህላዊ እንቅስቃሴዎች የመሳተፍ

   ለ/ ሳይንሳዊ ዕድገት በሚያስገኛቸው ጥቅሞች የመጠቀም፣

   ሐ/ ፈጣሪ ለሆነባቸው የሳይንስ፣ የስነ ፅሑፍ ወይም የስነ ጥበብ ውጤቶች መንፈሳዊና ቁሳዊ ጥቅም የማግኘት፣

   መብት ያለው መሆኑን ያውቃሉ።

2. ይህን መብት ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ለማድረግ በቃል ኪዳኑ ተዋዋይ አገሮች የሚወሰዱ እርምጃዎች ሳይንስንና ባሕልን ለመንከባከብ፣ ለማሳደግና

ለማስፋፋት የሚያስፈልጉ እርምጃዎችን ይጨምራሉ፡፡

3. የዚህ ቃል ኪዳን ተዋዋይ አገሮች ለሳይንሳዊ ምርመራና ለፈጠራ ስራ አስፈላጊ የሆነውን ነፃነት ለማክበር ተስማምተዋል፡፡
4. የዚህ ቃል ኪዳን ተዋዋይ አገሮች በሳይንስና ባሕል መስኮች የዓለም አቀፍ ግንኙነቶችንና ትብብሮችን በማበረታታትና በማሳደግ የሚገኘውን ጥቅም ይገነዘባሉ፡፡

## ክፍል አራት

## አንቀጽ 16

1. የዚህ ቃል ኪዳን ተዋዋይ አገሮች ስለወሰዷቸው እርምጃዎችና በቃል ኪዳኑ ዕውቅና ያገኙትን መብቶች በማስከበሩ ረገድ ስለተገኘው ውጤት በዚህ የቃል ኪዳኑ ክፍል በተደነገገው መሰረት ዘገባ ያቀርባሉ፡፡
2. ሀ/ ሁሉም ዘገባዎች ለተባበሩት መንግስታት ዋና ፀሐፊ መቅረብ አለባቸው፣ ዋና ፀሐፊውም የቀረቡለትን ዘገባዎች ቅጂዎች በዚህ ቃል ኪዳን

በተደነገገው መሰረት እንዲመረመሩ ለተባበሩት መንግስታት ድርጅት የኢኮኖሚና ማህበራዊ ጉዳዮች ምክር ቤት ያቀርባል፡፡

ለ/ የተባበሩት መንግስታት ዋና ፀሐፊ በዚህ ቃል ኪዳን ተዋዋይ አገሮች የቀረቡለትን የዘገባዎች ቅጂዎች ወይም የዘገባዎቹን የተወሰኑ ክፍሎች እነዚሁ አገሮች አባል ለሆኑባቸውና ልዩ ተልእኮ ለተሰጣቸው ድርጅቶች ያስተላልፋል፡፡ ዋና ፀሐፊው የዘገባዎቹን ቅጂዎች ወይም የተወሰኑትን ክፍሎች ለእነዚህ ድርጅቶች የሚያስተላልፈው በመተዳደሪያ ደንባቸው መሰረት ጉዳዩ የሚመለከታቸው ከሆነ ነው፡፡

## አንቀጽ 17

1. የኢኮኖሚና ማህበራዊ ጉዳዮች ምክር ቤት ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ልዩ ተልእኮ የተሰጣቸው የተባበሩት መንግስታት ድርጅቶችንና የዚህን ቃል ኪዳን ተዋዋይ አገሮችን አማክሮ በሚያወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ይህ ቃል ኪዳን ስራ ላይ በዋለ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ተዋዋይ አገሮች

በሚወሰንላቸው ቅደም ተከተል ዘገባቸውን ያቀርባሉ፡፡

2. ዘገባዎቹ በዚህ ቃል ኪዳን ውስጥ የተደነገጉትን ግዴታዎች በመፈፀም በኩል ያጋጠሙትን ችግሮችና ምክንያታቸው ሊገልፁ ይችላሉ፡፡
3. ቀደም ሲል ተፈላጊውን መረጃ ለተባበሩት መንግስታት ድርጅት ወይም ልዩ ተልእኮ ለተሰጠው ለተገቢው የድርጅቱ አካል በዚህ ቃል ኪዳን ተዋዋይ አገሮች ቀርቦ ከሆነ እንደገና ዝርዝር ዘገባ ማቅረብ ሳያስፈልግ ይህንኑ በትክክል መጥቀስ በቂ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 18

የኢኮኖሚና ማህበራዊ ጉዳዮች ምክር ቤት ሰብአዊ መብቶችና መሰረታዊ ነፃነቶችን በሚመለከት በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ቻርተር በተሰጡት ኃላፊነቶች መሰረት ልዩ ተልእኮ ከተሰጣቸው የተባበሩት መንግስታት ድርጅት አካላት የዚህን ቃል ኪዳን ድንጋጌዎች በማስፈፀም በኩል ስለተገኙት ውጤቶች በሃላፊነታቸው ክልል ዘገባ እንዲያቀርቡለት ሁኔታዎችን ሊያመቻች ይችላል፡፡ እነዚህ ዘገባዎችም የድርጅቶቹ

አካላት በአፈፃፀም ረገድ ያደረጓቸውን ውሳኔዎችና ያቀረቧቸውን ሃሳቦች ዝርዝር ሊያካትቱ ይችላሉ።

## አንቀጽ 19

የኢኮኖሚና ማህበራዊ ጉዳዮች ምክር ቤት በአንቀፅ 16 እና 17 መሰረት አገሮች ያቀረቡለትንና በአንቀጽ 18 መሰረት ልዩ ተልእኮ ከተሰጣቸው አካላት የቀረቡለትን ሰብአዊ መብቶችን የሚመለከቱ ዘገባዎች ለጥናት፣ ለውሳኔና እንደየሁኔታው ለመረጃ እንዲያገለግለው ለሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን ሊያስተላልፍለት ይችላል።

## አንቀጽ 20

የዚህ ቃል ኪዳን ተዋዋይ አገሮችና የሚመለከታቸው ልዩ ተልእኮ የተሰጣቸው የተባበሩት መንግስታት ድርጅት አካላት በአንቀጽ 19 መሰረት በሚቀርብ ማናቸውም የወሳኔ ሃሳብ፣ ወይም በሰብአዊ መብት ኮሚሽን በሚቀርብ ሰነድ ወይም በሰነዱ

በተመለከተ ጉዳይ ላይ አስተያየታቸውን ለኢኮኖሚና ማህበራዊ ጉዳዮች ምክር ቤት ማቅረብ ይችላሉ፡፡

## አንቀጽ 21

የኢኮኖሚና ማህበራዊ ጉዳዮች ምክር ቤቱ በቃል ኪዳኑ የተገለፁትን መብቶች በማስከበር ረገድ የተሰወዱ እርምጃዎችን እና የተገኙ ውጤቶችን በተመለከተ በተመለከተ አጠቃላይ ዘገባዎችንና የውሳኔ ሃሳቦች እንዲሁም በዚህ ረገድ ከአባል አገሮችና ልዩ ተልእኮ ከተሰጣቸው አካላት የሚቀርቡለትን መረጃዎች በማጠናቀር ለጠቅላላ ጉባኤው በየጊዜው መግለጫ ያቀርባል፡፡

## አንቀጽ 22

የቃል ኪዳኑን ድንጋጌዎች በማስከበር ረገድ ባላቸው የስልጣን ክልል ውስጥ ተገቢ የሆኑ እርምጃዎች ለመውሰድ ይችሉ ዘንድ፣ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ጉዳዮች ምክር ቤት በዚህ የቃል ኪዳኑ ክፍል መሰረት የሚቀርቡለትን ዘገባዎች ወይም ዘገባዎቹ ካካተቱዋቸው

ጉዳዮች ተገቢ የሆኑትን ፍሬ ነገሮች ለተባበሩት መንግስታት ድርጅት ሌሎች አካላትና ለእነርሱ ተጠሪ ለሆኑ ክፍሎች እንዲሁም ቴክኒካዊ ድጋፍ በመስጠት ረገድ ልዩ ተልእኮ የተሰጣቸው አካላት እንዲያውቋቸው ሊያደርግ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 23

የዚህ ቃል ኪዳን አባል አገሮች በዚህ ቃል ኪዳን ውስጥ ዕውቅና ያገኙትን መብቶች ለማስከበር የሚደረግ ዓለም አቀፍ እንቅስቃሴ፣ ቃል ኪዳኖችን መፈፀም፣ የውሳኔ ሃሳቦችን መቀበል፣ የቴክኒክ ዕርዳታ ማቅረብ፣ ከሚመለከተው አገር ጋር በመተባበር ለምክክርና ለጥናት የሚደረጉ አካባቢያዊ ቴክኒካዊ ስብሰባዎችን ማካሄድና የመሳሰሉትን እንደሚችሉ ተስማምተዋል፡፡

## አንቀጽ 24

የዚህ ቃል ኪዳን ማንኛውም ድንጋጌ በቃል ኪዳኑ የተገለፁትን ጉዳዮች በተመለከተ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ቻርተር ወይም ልዩ ተልእኮ

የተሰጣቸው አካላቱ በተቋቋሙባቸው ደንቦች ውስጥ የሚገኙትን የአካላቱን ተግባርና ኃላፊነት የሚወስኑ ድንጋጌዎችን እንደሚያፋልስ ሆኖ አይተረጎምም፡፡

## አንቀጽ 25

ማንኛውም የዚህ ቃል ኪዳን ድንጋጌ ማንኛውም ሕዝብ የተፈጥሮ ሃብቱን በሙሉና በነፃ ለመጠቀም ያለውን ተፈጥሮአዊ መብት እንደሚገድብ ተደርጎ አይተረጎምም፡፡

# ክፍል አምስት

## አንቀጽ 26

1. ይህ ቃል ኪዳን ለማንኛውም የተባበሩት መንግስታት ድርጅት አባል አገር ወይም ልዩ ተልእኮ የተሰጣቸው አካላት አባል አገር፣ የዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት መተዳደሪያ ሕግን ለተቀበለ አገር፣ በተባበሩት መንግስታት ጠቅላላ ጉባዔ የዚህ ቃል ኪዳን ፈራሚ እንዲሆን ለተጋበዘ አገር ለፊርማ ክፍት ነው፡፡

2. ይህ ቃል ኪዳን በየአገሩ የሕግ አውጪ አካል ፀድቆ ተቀባይነት ማግኘት አለበት። ቃል ኪዳኑ የፀደቀበት ማረጋገጫ ሰነድ ለተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ መቅረብ አለበት።
3. ይህ ቃል ኪዳን በዚህ አንቀጽ ቁጥር 1 ውስጥ ለተጠቀሱት አገሮች እንዲቀበሉት ክፍት ይሆናል።
4. የአገሮች መቀበል የሚረጋገጠው የመቀበያ ሰነዱን በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ ዘንድ በማኖር ነው።
5. የተባበሩት መንግስታት ዋና ፀሐፊ ይህን ቃል ኪዳን ለፈረሙ ወይም ለተቀበሉ አገሮች የማፅደቂያ ወይም የስምምነት ማረጋገጫ ሰነዶችን መረከቡን ያስታውቃቸዋል።

## አንቀጽ 27

1. ይህ ቃል ኪዳን ሰላሳ አምስተኛው የማፅደቂያ ወይም የመቀበያ ሰነድ ለተባበሩት መንግስታት ዋና ፀሐፊ ከቀረበበት ከሶስት ወራት በኋላ የፀና ይሆናል።

2. ሠላሳ አምስተኛው የማፅደቂያ ወይም የመቀበያ ሰነድ ከቀረበ በኋላ ይህንን ቃል ኪዳን ያፀደቀ ወይም የተቀበለ እያንዳንዱ አገር የራሱን የማፅደቂያ ወይም የመቀበያ ማረጋገጫ ሰነድ ካስረከበበት ከሶስት ወራት በኋላ ቃል ኪዳኑ በአገሩ የፀና ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 28

ፌዴራላዊ አስተዳደር ባላቸው አገሮች የዚህ ቃል ኪዳን ድንጋጌዎች በሁሉም የአስተዳደር ክልሎች ያለምንም ገደብ ወይም ልዩነት ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

## አንቀጽ 29

1. ማንኛውም የዚህ ቃል ኪዳን አባል አገር የማሻሻያ ሃሳብ ለተባበሩት መንግስታት ዋና ፀሐፊ ማቅረብ እና ይሄው ሃሳብም በፀሐፊው ዘንድ እንዲቀመጥለት ማድረግ ይችላል፡፡ ዋና ፀሐፊውም የቀረበለትን የማሻሻያ ሃሳብ ለሌሎች ቃል ኪዳኑን ለተቀበሉ አገሮች በማስታወቅ የቀረበው ማሻሻያ ላይ

ለመወያየትና ድምፅ ለመስጠት አገሮቹ ጉባኤ እንዲካሄድ መፈለግ አለመፈለጋቸውን እንዲገልፁለት ይጠይቃል። ቃል ኪዳኑን ከተቀበሉት አገሮች አንድ ሶስተኛው የጉባኤውን መካሄድ የሚፈልጉ ከሆነ ዋና ፀሐፊው ጉባኤውን በተባበሩት መንግስታት ድርጅት አማካይነት ጉባኤው እንዲካሄድ ያደርጋል። በጉባኤው የተገኙት ድምፅ የሰጡት ፈራሚ አገሮች ማሻሻያውን በአብላጫ ድምፅ ከተቀበሉ ማሻሻያው እንዲፀድቅ ለተባበሩት መንግስታት ጠቅላላ ጉባኤ ይቀርባል።

2. የቃል ኪዳኑ ማሻሻያ ሃሳብ የፀና የሚሆነው በተባበሩት መንግስታት ጠቅላላ ጉባኤ ሲፀድቅና ቃል ኪዳኑን የተቀበሉት አገሮቸ ሁለት ሦስተኛው በአብላጫ ድምፅ እንደየአገራቸው የሕግ አወጣጥ ስርአት ሲቀበሉት ነው።
3. ማሻሻያው ከፀና በኋላ ቃል ኪዳኑን በተቀበሉት አገሮች ውስጥ የሕግ ኃይል ይኖረዋል። እንዲሁም በሌሎቹ ፈራሚ አገሮች ውስጥ ከዚህ ማሻሻያ በፊት የነበሩት የዚህ ቃል ኪዳን ድንጋጌዎችና እነሱ

የተሰማሙባቸው የቀድሞ ማሻሻያዎች የፀኑ ይሆናሉ።

## አንቀጽ 30

በአንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ 5 የተገለፁት ማስገነዘቢያዎች ቢኖሩም በዚያው አንቀፅ በንዑስ አንቀጽ 1 ለተጠቀያሱት አገሮች የድርጅቱ ዋና ፀሐፊ ስለሚከተሉት ዝርዝር ያስታውቃል፤

ሀ/ በአንቀጽ 26 ስለተጠቀሱት ፊርማዎች፣ ማፅደቂያዎችና መቀበያዎች፣

ለ/ በአንቀጽ 27 መሰረት ይህ ቃል ኪዳን የፀናበትን ጊዜና በአንቀጽ 29 መሰረት ማሻሻያዎቹ የፀኑበትን ጊዜ።

## አንቀጽ 31

1. የዚህ ቃል ኪዳንን ቅጅዎች በተባበሩት መንግስታት ድርጅት መዝገብ ቤት ይቀመጣል፤ የቻይንኛ፣ የእንግሊዝኛ፣ የፈረንሳይኛ፣ የሩሲኛና የስፓንኛ ቋንቋ ሁሉም ቅጅዎች እኩል እውቅና አላቸው።

2. የተባበሩት መንግስታት ዋና ፀሐፊ ትክክለኛነታቸው የተረጋገጠውን የዚህ ቃል ኪዳን ቅጂዎች በአንቀጽ 26 ለተጠቀሱት ተዋዋይ አገሮች ያስተላልፋል።

# የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ዓለም

# አቀፍ ቃል ኪዳን

*በጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔ ቁጥር 2200 A (XXI) ዲሴምበር 16 ቀን 1966 ዓ.ም. (እ..አ.አ) ፀድቆ አባል አገሮች እንዲያፀድቁት እና እንዲቀበሉት የቀረበ*
*ስራ ላይ የዋለበት ዕለት በአንቀፅ 49 መሠረት ማርች 23 ቀን 1976 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ)*

## መግቢያ

**የዚህ ቃል ኪዳን ተዋዋይ አገሮች፤**

በተባበሩት መንግስታት ቻርተር መርሆች መሰረት የሰው ዘር በሙሉ አብሯቸው የተፈጠረ ክብር ያላቸው መሆኑን፣ እኩል እና ከስብእናቸው ሲነጠሉ የማይችሉ መብቶች የሏቸበው መሆኑን አውቆ መቀበል ለነፃነት፣ለፍትሕና ለአለም ሰላም መሰረት መሆኑን በመገንዘብ፤

እነዚህ መብቶች ሰው በሰውነቱ ከተጐናፀፈው ተፈጥሮአዊ ክብር የሚመነጩ መሆናቸውን በማወቅ፤

በአለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች መግለጫ መሰረት ሰዎች ከፍርሃትና ከድህነት ነፃ ሆነው የሚኖሩበት ዓለም ሊፈጠር የሚችለው እያንዳንዱ ሰው የሲቪል እና የፖለቲካ መብቶቹን እንደሁም የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊ እና የባህላዊ መብቶቹን ለመቀዳጀት የሚያስችሉት ሁኔታዎች ሲፈጠሩለት ብቻ መሆኑን በማወቅ

ሰብዓዊ መብቶችና ነፃነቶች በመላው ዓለም እንዲከበሩና እንዲጠበቁ ለማድረግ በተባበሩት መንግስታት ቻርተር መሰረት አገሮች ያለባቸውን ግዴታ በመገንዘብ፣

ግለሰቡም ለሌሎች ግለሰቦችና ለሚኖርበት ሕብረተሰብ ኃላፊነት ስለአለበት፣ በዚህ ቃል ኪዳን የተደነገጉት መብቶች እንዲከበሩና እንዲጠበቁ የበኩሉን ጥረት ማድረግ ያለበት መሆኑን በመረዳት፣

በሚከተሉት አንቀጾች ላይ ተስማምተዋል፤

# ክፍል አንድ

## አንቀጽ 1

1. ሁሉም ሕዝቦች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት አላቸው:: ይህንን መብት በመጐናፀፋቸው የፖለቲካ ሕልውናቸውን በነፃነት የመወሰን፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ባሕላዊ ዕድገታቸውን በነፃነት የማራመድ መብት አላቸው፡

2. ሁሉም ሕዝቦች በዓለም አቀፍ ሕግ መሠረት እና በጋራ ጥቅም መርሆ ላይ የተመሰረተውን ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ትብብር ግዴታቸውን ሳይጥሱ የተፈጥሮ ሀብታቸውንና ሌሎች ሃብቶቻቸዉን ለየራሳቸው አላማ በነፃነት መጠቀም ይችላሉ:: በማንኛውም ሁኔታ ቢሆን አንድ ሕዝብ ለኑሮው አስፈላጊ የሆኑትን ጥቅሞች ሊነፈግ አይገባም::

3. ራሳቸውን ለማያስተዳድሩና በሞግዚት ለሚተዳደሩ ግዛቶች የማስተዳደር ሃላፊነት ያለባቸው አገሮችን ጨምሮ፣ የዚህ ቃል ኪዳን ተዋዋይ አገሮች ሁሉ

የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት ከተባበሩት መንግስታት ቻርተር ድንጋጌ ጋር በሚጣጣም ሁኔታም ተግባራዊ እንዲሆን ይጥራሉ፣ ይህንን መብት ያከብራሉ።

## ክፍል ሁለት

## አንቀጽ 2

1. እያንዳንዱ ይህን ቃል ኪዳን የተቀበለ አገር በግዛቱ ውስጥ ለሚኖርና በስሩ ለሚተዳደር ማንኛውም ግለሰብ በዘር፣ በቀለም፣ በጾታ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ ወይም ሌላ አመለካከት፣ በብሔራዊም ሆነ ማህበራዊ አመጣጡ፣ በሀብት፣ በትውልድ ወይም በሌላ መለኪያ ምንም ልዩነት ሳያደርግ በዚህ ሕግ ዕውቅና ያገኙትን መብቶች ሊያስከብርለትና ሊያረጋግጥለት ተስማምቷል።
2. በስራ ላይ ባሉት የአገሩ ሕጎች ወይም ሌሎች እርምጃዎች መሰረት እነዚህ መብቶች ከአሁን በፊት ዕውቅና ያልተሰጣቸው ከሆነ እያንዳንዱ ይህን ቃል ኪዳን የተቀበለ አገር በአገሩ የሕግ አወጣጥ ስርዓትና በዚህ ቃል ከዳን ውስጥ ባሉት ድንጋጌዎች መሰረት

መብቶቹን ተግባራዊ የሚያደርጉ ሕጎች ለማውጣትና ሌሎች አስፈላጊ እርምጃዎችን ለመውሰድ ተስማምቷል፡፡

3. እያንዳንዱ ይህን ቃል ኪዳን የተቀበለ አገር የሚከተሉትን ለመፈፀም ተስማምቷል፤

   ሀ/ ማንኛውም ሰው በዚህ ሕግ ዕውቅና ያገኙት መብቶቹና ነፃነቶቹ ሲጣሱበት፣ እነዚህ መብቶችና ነፃነቶች የተጣሱበት በመንግስት ባለስልጣኖች ቢሆንም እንኳ ለደረሰበት በደል ውጤታማ መፍትሔ እንዲያገኝ ለማድረግ፣

   ለ/ ለደረሰበት በደል መፍትሔ የሚሻ ማንኛውም ሰው ስልጣን ባለው የፍትሕ፣ የአስተዳደር ወይም የሕግ አውጪ አካል፣ ወይም በአገሪቱ የሕግ ስርዓት መሰረት ስልጣን በተሰጠው ሌላ አካል መብቱ እንዲረጋገጥለት ለማድረግና ፍትሕ እንዲያገኝ ለማመቻቸት፤

   ሐ/ የፍትሕ ውሳኔ ሲያገኝም ስልጣን በተሰጣቸው አካላት ውሳኔውን ለማስፈፀም፡፡

## አንቀጽ 3

ይህን ቃል ኪዳን የተቀበሉ አገሮች በዚህ ድንጋጌ የሰፈሩትን የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ወንዶችና ሴቶች በእኩልነት በመጠቀም ረገድ ያላቸውን መብት ለማረጋገጥ ተስማምተዋል።

## አንቀጽ 4

1. ይህን ቃል ኪዳን የተቀበሉ አገሮች የአገራቸውን ሕልውና የሚያናጋ የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ሲከሰትና ይህም በይፋ የታወጀ ሲሆን ሁኔታውን ለመቆጣጠር በሚያስፈልገው መጠን ልክ ብቻ በዚህ ቃል ኪዳን ከተቀበሏቸው ግዴታዎች ለየት ያሉ አንዳንድ እርምጃዎችን መውሰድ ይችላሉ። ሆኖም የሚወስዷቸው እርምጃዎች በሌላ ዓለም አቀፋዊ ሕግ የተደነገጉትን ግዴታዎች የሚጥሱና በዘር፣ በቀለም፣ በጾታ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት ወይም በማህበራዊ አመጣጥ ምክንያትነት ልዩነት የሚያደርጉ መሆን አይገባቸውም።

2. በዚህ አንቀፅ የተገለፀው ቢኖርም በዚህ ቃል ኪዳን ውስጥ በአንቀጽ 6፣7፣8 (ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2፣) 11፣15፣16 እና 18 የተጠቀሱትን ድንጋጌዎች የሚቃረን እርምጃ መውሰድ አይቻልም፡፡

3. ይህን ቃል ኪዳን የተቀበለ ማንኛውም አገር በአስቸኳይ ግዜ ሁኔታ ምክንያት በቃል ኪዳኑ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ጋር የማይጣጣሙ እርምጃዎችን የመውሰድ መብቱን ለመጠቀም በሚፈለግበት ጊዜ የማያከብራቸውን ድንጋጌዎች ከነምክንያቶቻቸው በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ጸሐፊ በኩል ለዚህ ቃል ኪዳን አባል አገሮች ያስታውቃል፡፡ ሁኔታው ሲለወጥም ወዲያውኑ ሌላ ማስታወቅያ በተመሳሳይ መንገድ ለአባል አገሮች መስጠት ይኖርበታል፡፡

## አቀንጽ 5

1. በዚህ ቃል ኪዳን የተጠቀሰ ማንኛውም ድንጋጌ ማንኛውም አገር፣ ቡድን ወይም ግለሰብ በቃል ኪዳኑ የተደነገጉትን ማናቸውንም መብቶችና ነፃነቶች ለመግፈፍ ወይም በቃል ኪዳኑ ከተደነገገው

በበለጠ ሁኔታ ለመገደብ የታቀደ ድርጊት ለመፈፀም የሚያስችል መብት እንዳለው ተደርጎ ሊተረጎም አይችልም።

2. ይህ ቃል ኪዳን ዕውቅና አይሰጣቸውም ወይም እኩል አያያቸውም በሚል ሰበብ ይህን ቃል ኪዳን በተቀበለ በማንኛውም አገር በሕግ፣ በስምምነት፣ በልማድ፣ በባህል ወይም በሌላ ደንብ ሲሰራባቸው የቆዩ መሰረታዊና ሰብአዊ መብቶች መገደብ ወይም መጻረር አይፈቀድም።

## ክፍል ሶስት

## አንቀጽ 6

1. ማንኛውም ሰው በሕይወት የመኖር ተፈጥሮአዊ መብት አለው። ይህ መብት በህግ ይከበራል፤ ማንኛውም ሰው ያላግባብ ሕይወቱን አይነፈግም።
2. የሞት ቅጣትን እንዲቀር ባላደረጉ አገሮች ውስጥ የሞት ፍርድ የሚወሰነው ወንጀል በሚፈፀምበት ጊዜ በነበረው ሕግ መሰረት በጣም ከባድ ለሆነ ወንጀል ነው። ፍርዱም ሲወሰን የዚህን ዓለም አቀፍ ቃል

ኪዳን ድንጋጌዎችና፣ የዘር ማጥፋት ወንጀል ለመከላከልና ለመቅጣት የወጡ ሕጐችን በማይፃረር መልኩ ነው፡፡ ቅጣቱ የሚፈፀመው በሕግ በተቋቋመ ፍርድ ቤት የመጨረሻ ውሳኔ ሲሰጥ ብቻ ነው፡፡

3. የተፈፀመው የህይወት ማጥፋት ተግባር የዘር ማጥፋት ወንጀል ዓይነት የሆነ እንደሆነ በዚህ አንቀፅ ውስጥ የተደነገጉት አንዳቸውም ድንጋጌዎች ይህንን ቃል ኪዳን የተቀበሉ አገሮች በዘር ማጥፋት ወንጀል መከላከያ እና መቅጫ ስምምነት መሰረት የገቧቸውን ግዴታዎች የሚፃረሩ እርምጃዎች እንዲወስዱ እንደሚፈቅዱላቸው ተደርገው ሊነበቡ እንደሚችሉ ግንዛቤ ተወስዶበታል፡፡
4. ማንኛውም የሞት ቅጣት የተፈረደበት ሰው ይቅርታ የመጠየቅ ወይም የሞት ቅጣቱ ወደ እስራት እንዲለወጥለት የመጠየቅ መብት አለው፡፡ በሁሉም ጉዳዮች ይቅርታ ወይም ምሕረት ማድረግ፣ ወይም የሞት ቅጣቱን ወደ እስራት ቅጣት መለወጥ ይቻላል፡፡
5. ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች በሆኑ ወንጀል ፈፃሚዎች የሞት ፍርድ አይወሰንም፡፡ ነፍሰ ጡር በሆኑ ሴቶች ላይም ቅጣቱ አይፈጸምም፡፡

6. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች የሞት ቅጣትን ለማስወገድ የሚወሰዱ እርምጃዎችን ለማዘግየት ወይም ለማስቀረት በቃል ኪዳኑ አባል አገሮች በምክንያትነት ሊጠቀሱ አይችሉም፡፡

## አንቀጽ 7

ማንም ሰው ስቃይ ወይም ጭካኔ ለተሞላበት፣ ኢሰብዓዊ ወይም ክብርን ለሚያዋርድ አያያዝና ቅጣት መጋለጥ የለበትም፡፡ በተለይም በማንኛውም ሰው ላይ ያለፈቃዱ የሕክምና ወይም ሳይንሳዊ ሙከራ መደረግ የለበትም፡፡

## አንቀጽ 8

1. ማንኛውም ሰው በባርነት አይያዝም፡፡ ባርነትና የባርያ ንግድ በማንኛውም መልካቸው የተከለከሉ ናቸው፡፡
2. ማንኛውም ሰው ተገዶ በአገልጋይነት አይያዝም፡፡
3. ሀ/ ማንኛውም ሰው በሃይል ተገዶ ወይንም የግዳጅ ስራዎችን እንዲያከናውን  አይደረግም፡፡

ለ/ በንኡስ አንቀፅ 3/ሀ/ የተደነገገው ድንጋጌ የግዳጅ ስራ ከእስራት ጋር እንደቅጣት በሚወሰንባቸው አገሮች ውስጥ ስልጣን ያለው ፍርድ ቤት ከባድ የጉልበት ስራን እንደቅጣት እንዳይወሰን የሚከለክለው እንደሆነ ተደርጐ አይተረጐምም፡፡

ሐ/ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ለተመለከተው ጉዳይ «በሃይል ተገዶ ወይንም የግዳጅ ስራ» የሚለው አነጋገር የሚከተሉትን አይጨምርም፡፡

i. በንዑስ አንቀጽ 3(ለ) ውስጥ ያልተጠቀሰና በፍርድ ቤት ውሳኔ በእስር ላይ ባለ ሰው መፈፀም ያለበት ማንኛውም ስራ ወይም አገልግሎት ወይም ከሕጋዊ እስራት በገደብ በተለቀቀ ሰው መፈፀም ያለበት ማንኛውም ስራ ወይም አገልግሎት፤
ii. ማንኛውም ወታደራዊ ባሕርይ ያለው አገልግሎት ወይም የሕሊና ተቃውሞ ዕውቅና ባገኘበት አገር ውስጥ የሕሊና

ተቃዋሚዎች በሕግ ማሟላት ያለባቸውን ብሔራዊ አገልግሎት፤

iii. በአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ወይም የሕብረተሰቡን ሕይወት ወይም ደህንነት ለጥፋት በሚያጋልጥ አደጋ ጊዜ መፈፀም ያለበት ማንኛውም አገልግሎት፤

iv. መደበኛ የሲቪል ግዴታዎች አካል የሆነ ማንኛውም ስራ ወይም አገልግሎት::

## አንቀጽ 9

1. ማንኛውም ሰው የነፃነትና የደህንነት መብት አለው:: ማንኛውም ሰው በዘፈቀደ አይያዝም፤ አይታሰርም:: ማንኛውም ሰው በሕግ ከተደነገገው ምክንያትና ስርዓት ውጭ ነፃነቱ አይገፈፍም::
2. ማንኛውም ሰው በሚያዝበት ጊዜ የተያዘባቸውን ምክንያቶችና የቀረቡበትን ክሶች ምንነት ወድያውኑ የማወቅ መብት አለው::
3. በወንጀል ክስ የተያዘ ወይም የታሰረ ሰው ከዳኛ ወይም በሕግ ስልጣን ከተሰጠው አካል ዘንድ በአፋጣኝ ሊቀርብ ይገባል:: ተገቢ በሆነ ጊዜ

ውስጥም ዳኝነት የማግኘት ወይም የመለቀቅ መብት አለው:: ዳኝነት የሚጠባበቁ ሰዎችን በእስር ማቆየት እንደመደበኛ አፈጻጸም ሊታይ አይገባውም:: ይሁን እንጂ ከእስር መልቀቁ ግለሰቡን ጉዳዩ በሚታይበት ጊዜ እንዲቀርብ፣ ወይም ፍርዱ እንዲፈጸምበት ለማድረግ እንዲያመች በዋስትና ላይ የተመሰረተ ሊሆን ይችላል::

4. ማንኛውም በመታሰሩ ወይም በመያዙ ምክንያት ነፃነቱን የተነፈገ ሰው ፍርድ ቤቱ የእስራቱን ሕጋዊነት ወዲያውኑ መርምሮ እንዲወስንለት ያላግባብ መታሰሩን ካረጋገጠ ደግሞ በነፃ እንዲለቀቅ እንዲያዝለት ፍርድ ቤት የመቅረብ መብት አለው::
5. ማንኛውም በሕገ ወጥ ሁኔታ የተያዘ ወይም የታሰረ ሰው ካሳ የማግኘት መብት አለው::

## አንቀጽ 10

1. በሕግ ነፃነታቸውን የተገፈፉ ሰዎች ሁሉ ሰብአዊ አያያዝ ሊደረግላቸውና ሰው በመሆናቸው በተፈጥሮ የተጐናፀፉት ክብር ሊጠበቅላቸው ይገባል::

2. (ሀ) የተለየ ሁኔታ ካላጋጠመ በስተቀር ክስ የተመሰረተባቸው ሰዎች ከተፈረደባቸው ሰዎች ሊለዩና ጥፋተኛ ላልሆኑ ሰዎች የሚሰጠው አያያዝ ሊደረግላቸው የገባል፡፡

(ለ) ወጣት አጥፊዎች ከአዋቂዎች በተለየ ቦታ መጠበቅና ባስቸኳይ ፍርድ ቤት መቅረብ አለባቸው፡፡

3. የእስራት ዓላማ አስረኞች ከጥፋታቸው እንዲታረሙና የተሻሻሉ የሕብረተሰብ አባላት እንዲሆኑ ማድረግ ነው፡፡ ወጣት አጥፊዎች ከአዋቂ እስረኞች በተለየ ቦታ የመጠበቅና ከዕድሜያቸውና የሕግ አቋማቸው ጋር የሚስማማ እንክብካቤ የማግኘት መብት አላቸው፡፡

## አንቀጽ 11

ማንኛውም ሰው የውል ግዴታውን ባለማሟላቱ ብቻ አይታሰርም፡፡

## አንቀጽ 12

1. በአንድ አገር የግዛት ክልል ውስጥ በሕጋዊ መንገድ ያለ ማንኛውም ሰው በዚያ አገር ውስጥ በነፃነት የመንቀሳቀስና የመኖሪያ አካባቢውን በነፃነት የመምረጥ መብት አለው።
2. ማንኛውም ሰው የትኛውንም አገር፣ የራሱንም ጭምር፣ ለቆ የመውጣት መብት አለው።
3. ብሔራዊ ጸጥታን፣ ሰላምና ደህንነትን፣ የሕዝብን ጤና፣ መልካም ስነ ምግባርና እንዲሁም የሌሎችን መብቶችና ነፃነቶች ለመጠበቅ ሲባል በዚህ ቃል ኪዳን ከሰፈረሩት ድንጋጌዎች ጋር በሚስማማ አኳኋን በሚወጣ ሕግ መሰረት ካልሆነ በስተቀር ከላይ በተጠቀሱት መብቶች ላይ ምንም አይነት ገደብ አይደረግም።
4. ማንኛውም ሰው ወደ ራሱ አገር የመግባት መብቱ በዘፈቀደ አይከለከልም።

## አንቀጽ 13

ይህን ቃል ኪዳን በተቀበለ አገር ውስጥ በሕጋዊ መንገድ የሚኖር የውጭ አገር ሰው አስገዳጅ አገራዊ

ፀጥታ ካላጋጠመ በስተቀር ከዚያ አገር ሊባረር የሚችለው ሕግን ተከትሎ በሚሰጥ ውሳኔ ብቻ ነው። ግለሰቡም ይህንንም እርምጃ በመቃወም ጉዳዩ እንደገና እንዲታይለት ስልጣን ላለው አካል ወይም በዚህ አካል ለተሰየመ ሰው ወይም ሰዎች ራሱ ወይም በወኪሉ አማካይነት አቤቱታ የማቅረብ መብት አለው።

## አንቀጽ 14

1. ሰዎች ሁሉ በፍርድ ቤቶችና በዳኝነት አካላት ፊት በእኩልነት ይታያሉ። በቀረበበት የወንጀል ክስም ሆነ ስለ መብቶቹ እና ግዴታዎቹ በሚወሰንበት ማንኛውም ጉዳይ ማንኛውም ሰው በሕግ በተቋቋመ፣ ስልጣን ባለው፣ ነፃና ገለልተኛ በሆነ የዳኝነት አካል ዘንድ የመቅረብና አድልኦ የሌለበትና ግልፅ የሆነ ዳኝነት የማግኘት መብት አለው። ለዴሞክራሲያዊ ሕብረተሰብ አስፈላጊ የሆኑትን የመልካም ስነ ምግባር፣ የሕዝብ ደህንነት፣ ወይም ብሔራዊ ፀጥታን ለመጠበቅ ሲባል ወይም የተከራካሪ ወገኖች የግል ሕይወት የሚነካ ሲሆን፣ አለበለዚያም ፍርድ ቤቱ የጉዳዩ ይፋ መውጣት የዳኝነትን ስራ

አካሄድ የሚያሰናክል መሆኑን በማመን በሚሰጠው ትእዛዝ፣ አንድ ጉዳይ በዝግ ችሎት ሊታይ ይችላል። ይሁን እንጂ፣ የወጣት ጥፋተኞችን መብትና ጥቅም ለመጠበቅ ወይም በፍች ክርክር ጊዜ የሚወሰዱ የሕፃናት አጠባበቅን እርምጃዎች የሚመለከቱ ካልሆኑ በስተቀር በዝግ ችሎት የተሰጡ ማናቸውም የወንጀልና የፍትሐ ብሔር ውሳኔዎች ይፋ ይደረጋሉ።

2. ማንኛውም በወንጀል ጥፋት የተከሰሰ ሰው በሕጉ መሰረት ጥፋተኛነቱ እስከሚረጋገጥ ድረስ እንደ ንጹሕ ሰው የመቆጠር መብት አለው።
3. የቀረበበት የወንጀል ክስ በሚታይበት ጊዜ ማንኛውም ተከሳሽ ቢያንስ የሚከተሉትን ዋስትናዎች በእኩልነት የማግኘት መብት አለው።
   ሀ/ የቀረበበትን ክስና ምክንያቱን በሚገባው ቋንቋ በፍጥነትና በዝርዝር የማወቅ፤
   ለ/ ለቀረበበት ክስ መከላከያ ለማዘጋጀት አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮችና በቂ ጊዜ የማግኘትና አማካሪ እንዲሆን የመረጠውን ሰው የማማከር፤
   ሐ/ አግባብ ባልሆነ ሁኔታ ሳይዘገይ የመዳኘት፣

መ/ ራሱ በተገኘበት የመዳኘት፣ ራሱን በግል ወይም በመረጠው ጠበቃ በኩል የመከላከል፣ ጠበቃ ከሌለው የሕግ አማካሪ እርዳታ የማግኘት መብት እንዳለው የማወቅ፣ ትክክለኛ ዳኝነት የሚጓደል ሆኖ ሲታይና የገንዘብ አቅሙ የማይፈቅድ ሲሆን ሳይከፍል ጠበቃ የማግኘት መብቱ፣

ሠ/ የሚመሰክሩበትን ምስክሮች በግሉም ሆነ በጠበቃው አማካይነት የመመርመር፣ እንዲሁም በራሱ ላይ በተቆጠሩበት ምስክሮች ሁኔታ የራሱ ምስክሮች ቀርበው እንዲመረመሩለት የማድረግ፤

ረ/ ፍርድ ቤቱ የሚጠቀምበትን ቋንቋ የማይናገር ወይም የማይረዳ ከሆነ በነፃ አስተርጓሚ የማግኘት፤

ሰ/ በራሱ ላይ እንዲመሰክር ወይም ጥፋተኛነቱን እንዲያምን ያለመገደድ።

4. በወጣት ተከሳሾች ላይ የሚካሄድ የዳኝነት ስራ የዕድሜያቸውን ለጋነትና ከጥፋተኝነት ታርመው የሚታነፁበትን ስርዓት ግንዛቤ ውስጥ ያስገባል።
5. ማንኛውም በወንጀል የተፈረደበት ሰው በሕግ መሰረት ፍርዱም ሆነ ቅጣቱ በበላይ ፍርድ ቤት እንደገና እንዲታይለት የማድረግ መብት አለው።

6. በአንድ ሰው ላይ ተላልፎ የነበረው የመጨረሻ ፍርድ በማያሻማ አኳኋን ኢፍትሃዊ የነበረ ስለመሆኑ አዲስ በተገኘ ማስረጃ አማካኝነት የተረጋገጠ የሆነ እንደሆነ እና በዚህም ምክንያት ይህ ሰው ምህረት ካገኘ አልያም ደግሞ ተላልፎበት የነበረው ውሳኔ የተሻረ እንደሆነ በእንዲህ ዓይነቱ ፍርድ ምክንያትነት ደርሶበት ለነበረው ቅጣት በህጉ መሰረት ሊካስ ይገባል። ይህ የሚፈፀመዉ ለፍርዱ መቀልበስ ምክንያት የሆነው መረጃ ሳይታወቅ የቆየው በከፊልም ሆነ በሙሉ በተከሳሹ ምክንያት ያለመሆኑ ሲረጋገጥ ነው።

7. ማንኛውም ሰው በአገሩ ሕግና በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ መሰረት ለመጨረሻ ጊዜ በተፈረደበት ወይም ነፃ በወጣበት ጥፋት ዳግመኛ አይዳኝም ወይም አይቀጣም።

## አንቀጽ 15

1. ማንኛውም ሰው የፈፀመው ወይም ማድረግ ሲገባው ያልፈፀመው ተግባር በአገራዊም ሆነ ዓለም አቀፋዊ ሕግ መሰረት እንደ ወንጀል ባልተደነገገበት ግዜ

እንደ ወንጀለኛ ሊወሰድ አይገባውም:: እንዲሁም ጥፋቱን በፈፀመበት ጊዜ ስራ ላይ ውሎ ከነበረው ቅጣት የከበደ ቅጣት አይፈጸምበትም:: ጥፋቱ ከተፈፀመ በኋላ ለእንዲህ ዓይነቱ ወንጀል ቀለል ያለ ቅጣት የሚያስጥ ሕግ ከተደነገገ ጥፋተኛው ሰው የዚህ ሕግ ተጠቃሚ ይሆናል::

2. አገሮች እውቅና በሰጧቸው አጠቃላይ የሕግ መርሆች መሰረት የተፈፀመው ወይም መደረግ ሲገባው ሳይፈፀም የቀረው ድርጊት እንደ ወንጀል የሚቆጠር ከሆነ የጥፋተኛውን ለፍርድ መቅረብና መቀጣት ይህ አንቀጽ አይከለክልም::

## አንቀጽ 16

ማንኛውም ሰው በየትም ቦታ በሕግ ፊት እንደ ሰው የመታወቅ መብት አለው::

## አንቀጽ 17

1. በማንኛውም ሰው የግል ሕይወት፣ ቤተሰብ፣ መኖሪያ ቤት ወይም ደብዳቤ ላይ ያለ አግባብ ወይም ሕግ ወጥ በሆነ መንገድ ጣልቃ ገብነት

አይፈጸምም፡፡ መልካም ዝናውም ከሕግ ውጭ አይደፈርም፡፡

2. ማንኛውም ሰው ከእንዲህ ዓይነቱ ጣልቃ ገብነት ወይም መደፈር የሕግ ጥበቃ የማግኘት መብት አለው፡፡

## አንቀጽ 18

1. ማንኛውም ሰው የሀሳብ፣ የኅሊናና የሃይማኖት ነፃነት መብት አለው፡፡ ይህም መብት የመረጠውን ሃይማኖት ወይንም እምነት የመከተል ወይንም የመያዝ ነፃነትን፣ እንዲሁም ለብቻም ሆነ ከሌሎች ጋር በመሆን ሃይማኖቱን ወይም እምነቱን በአደባባይም ሆነ በግል በአምልኮ የመግለጽ፣ ስርዓቱን የማክበር፣ በተግባር የማዋልና የመስበክ ነፃነትን ይጨምራል፡፡
2. ማንም ሰው የመረጠውን ሃይማኖት ወይንም እምነት የመከተል ወይንም የመያዝ ነፃነቱን በሚነካ አኳኋን አይገደድም፡፡
3. የራስን ሃይማኖት ወይም እምነት የመግለጽ ነፃነት ሊገደብ የሚችለው በሕግ በተደነገገው መሰረትና የሕዝብን ደህንነት፣ ፀጥታ፣ ጤና፣ ወይም ስነ

ምግባር ወይም የሌሎችን መሰረታዊ መብቶችና ነፃነቶች ለማስከበር አስፈላጊ ሲሆን ብቻ ነው።

4. ይህን ቃል ኪዳን የተቀበሉ አገሮች ወላጆችና ሁኔታው ሲፈቅድ ሕጋዊ ሞግዚቶች የልጆቻቸው የሃይማኖትና የግብረ ገብነት ትምህርት የራሳቸውን እምነት የተከተለ መሆኑን የማረጋጥ መብታቸውን ለማክበር ተስማምተዋል።

## አንቀጽ 19

1. ማንኛውም ሰው ያለማንም ጣልቃ ገብነት የራሱ አመለካከት ሊኖረው መብት አለው።
2. ማንኛውም ሰው ሀሳብን የመግለጽ ነፃነት መብት አለው። ይህም መብት መረጃና ማንኛውም ዓይነት ሀሳብ፣ ያለምንም የድንበር ገደብ፣ በቃል፣ በጽሑፍ ወይም በሕትመት፣ በስነ ጥበብ ወይም ሌላ በመረጠው የመገናኛ ዘዴ የመፈለግ፣ የማግኘትና የማስተላለፍ መብትን ያጠቃልላል።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር 2 የተደነገጉት መብቶች ያጠቃቀም ሁኔታ ልዩ ግዴታዎችንና ኃላፊነቶችንም ጭምር ይዘዋል። በዚህም ምክንያት የተወሰኑ ገደቦች

ሊደረጉበት ይቻላል፤ ይሁን እንጂ ገደቦቹ በሕግ የተደነገጉና፣

ሀ/ የሌሎችን መብቶችና ክብር ለማስጠበቅ፣

ለ/ ብሔራዊ ጸጥታን፣ የሕዝብ ደህንነትን፣ ወይም ጤናን ወይም ስነ ምግባርን ለማስከበር አስፈላጊ መሆን አለባቸው።

## አንቀጽ 20

1. ማንኛውም ለጦርነት የሚደረግ ፕሮፓጋንዳ በሕግ የተከለከለ ነው።
2. አድልዎን፣ ጠላትነትን ወይንም ሁከትን ሊያስነሳ የሚችል የብሄር፣ የዘር ወይንም የሃይማኖት ጥላቻን የሚፈጥር ቅስቀሳ በህግ የተከለከለ ነው።

## አንቀጽ 21

ሰላማዊ ስብሰባ የማድረግ መብት እውቅና ይሰጠዋል። በዴሞክራሲያዊ ሕብረተሰብ ውስጥ ለብሔራዊ ደህንነት፣ የሕዝብ ሰላምና ፀጥታ ጥቅም

ወይም የሕዝብን ጤናና ስነ ምግባር ለመጠበቅ ወይም የሌሎችን መብቶችና ነፃነቶች ለማስከበር ከሚያስፈልገው እና በሕግ ከተደነገገው በቀር በዚህ መብት አጠቃቀም ላይ ምንም ዓይነት ገደብ አይደረግም።

## አንቀጽ 22

1. ማንኛውም ሰው ከሌሎች ጋር በመሆን የመደራጀት መብት አለው፤ ይህም መብት ጥቅሞቹን ለማስከበር የሰራተኛ ማኅበራትን የማቋቋም እና አባል የመሆን መብትን ያጠቃልላል።
2. በዴሞክራሲያዊ ሕብረተሰብ ውስጥ ለብሔራዊ ደህንነት፣ ለሕዝብ ሰላምና ፀጥታ ጥቅም ወይም የሕዝብን ጤናና ስነምግባር ለመጠበቅ ወይም የሌሎችን መብቶችና ነፃነቶች ለማስከበር ከሚያስፈልገው እና ህግ ከሚደነግገው በቀር በዚህ መብት አጠቃቀም ላይ ምንም ዓይነት ገደብ አይደረግም። ይህ አንቀጽ በጦር ኃይሎች እና በፖሊስ ሰራዊት አባላት ላይ በዚህ መብት

አጠቃቀም ረገድ ሊደረግ የሚችለውን ሕጋዊ ገደብ አይከለክልም።

3. ይህ አንቀጽ «ማህበር የማቋቋም ነፃነትና የመደራጀት መብት ጥበቃን» የሚመለከተውን የ1948 (እ.ኤ.አ) የዓለም አቀፍ የስራ ድርጅት ስምምነት የተቀበሉ አገሮች በስምምነቱ የተረጋገጡትን ዋስትናዎች የሚፃረር ሕግ እንዲያወጡ ወይም ሕጉን ዋስትናዎቹን ሊፃረር በሚችል መልክ እንዲጠቀሙበት አይፈቀድላቸውም።

## አንቀጽ 23

1. ቤተሰብ የሕብረተሰቡ ተፈጥሯዊ መሰረት እንደመሆኑ በመንግስትና ሕብረተሰብ ጥበቃ ሊደረግለት ይገባል።
2. ለጋብቻ የደረሱ ወንዶችና ሴቶች የመጋባትና ቤተሰብ የመመስረት መብታቸው እውቅና ተሰጥቶታል።
3. ያለ ተጋቢዎች ነፃና ሙሉ ፈቃድ ጋብቻ መመስረት የለበትም።

4. ይህን ቃል ኪዳን የተቀበሉ አገሮች ተጋቢዎች ጋብቻ ሲመሰርቱ፣ ጋብቻው በሚቆይበት ጊዜ እና ጋብቻው ሲፈርስ እኩል መብትና ኃላፊነት ያላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ተገቢውን እርምጃ ይወስዳሉ። ጋብቻው በሚፈርስበት ጊዜ ለልጆቹ ጥቅም ተገቢውን ጥበቃ የሚያደርግ ሕግ ተግባራዊ መሆን አለበት።

## አንቀጽ 24

1. የዘር፣ የቀለም፣ የቋንቋ፣ የሃይማኖት፣ የብሔርም ሆነ የማሕበራዊ አመጣጥ፣ የሃብት ወይም የትውልድ ምንም ዓይነት ልዩነት ሳይደረግበት ማንኛውም ልጅ ለአካለ መጠን ባለመድረሱ ምክንያት የሚያስፈልገውን ጥበቃና እንክብካቤ ከቤተሰብ፣ ከህብረተሰቡና ከመንግስት የማግኘት መብት አለው።
2. ማንኛውም ሕፃን ወዲያውኑ እንደተወለደ ይመዘገባል፤ ስም ይሰጠዋል።
3. እያንዳንዱ ልጅ ዜግነት የማግኘት መብት አለው።

## አንቀጽ 25

ማንኛውም ዜጋ በአንቀጽ 2 የተጠቀሱት ልዩነቶች ሳይደረጉበትና አግባብነት የሌላቸው ገደቦች ሳይደረጉበት፣

ሀ/ በቀጥታ ራሱ ወይም በነፃ በተመረጡ ተወካዮቹ አማካይነት በሕዝብ ጉዳዮች የመሳተፍ፤

ለ/ ሁሉም በእኩልነት በሚሳተፍባቸውና የመራጮቹ ፈቃድ በነፃ የሚገለጥባቸው ለመሆኑ ዋስትና ባላቸው በምስጢር በሚካሄዱ እና እውነተኛ በሆኑ ወቅታዊ ምርጫዎች የመመረጥ እና የመመረጥ፤

ሐ/ በአገር ውስጥ ለህዝብ በተዘረጉ አገልግሎቶች በእኩልነት የመጠቀም፣ መብትና ዕድል ይኖረዋል።

## አንቀጽ 26

ሁሉም ሰው በሕግ ፊት እኩል ነው፤ ያለምንም ልዩነት እኩል የሕግ ጥበቃ የማግኘት መብት አለው። በዚህ ረገድ ሕጉ ማንኛውንም ልዩነት በመከልከል በዘር፣ በቀለም፣ በጾታ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ ወይም በሌላ አመለካከት፣ በብሔር ወይም በማህበራዊ

አመጣጥ፣ በሀብት፣ በትውልድ ወይም በሌላ ተመሳሳይ ምክንያት አድሎአዊ ልዩነት እንዳይፈፀምበት ለሁሉም ሰው እኩልና አስተማማኝ ጥበቃ ያደርጋል፣ ዋስትናም ይሰጣል::

## አንቀጽ 27

በጎሳ፣ በሃይማኖት ወይም በቋንቋ ንኡሳን የሆኑ ማህበረሰቦች ባሉበት አገር ውስጥ የንኡሳን ማህበረሰቡ አባል የሆኑ ግለሰቦች በጋራ ባህላቸውን እንዳያከብሩ፣ ሃይማኖታቸውን እንዳያስፋፉ በቋንቋቸው እንዳይጠቀሙ መብታቸው ሊገፈፍ አይገባም::

## ክፍል አራት

## አንቀጽ 28

1. በዚህ ቃል ኪዳን መሰረት ኮሚቴ እየተባለ የሚጠቀስ የሰብአዊ መብት ኮሚቴ ይቋቋማል:: ኮሚቴው 18 አባላት የሚኖሩት ሲሆን ከዚህ በታች የተደነገጉትን ተግባሮች ያከናውናል::

2. ኮሚቴው ስነምግባራቸው ከፍተኛ በሆነ እና በሰብአዊ መብቶች መስክ በችሎታቸው ዕውቅና ባገኙ የዚህ ቃል ኪዳን አባል አገሮች ዜጎች በሆኑ ሰዎተ የሚመሰረት ሲሆን በተለይ የህግ ልምድ ያላቸው ሰዎች ማሳተፍ የሚኖረው ጥቅም ግምት ውስጥ ይገባል፡፡

3. የኮሚቴው አባላት በምርጫ የሚሰየሙና እራሳቸውን ወክለው የሚያገለግሉ ይሆናሉ፡፡

## አንቀጽ 29

1. የኮሚቴው አባላት ይህን ቃል ኪዳን የተቀበሉ አገሮች ለዚሁ አላማ ከሚያቀርቧቸው እና በአንቀጽ 28 የተጠቀሱትን መስፈርቶች ከሚያሟሉ የዕጩዎች ዝርዝር ውስጥ በምስጢር ድምፅ አሰጣጥ ይመረጣሉ፡፡

2. እያንዳንዱ ይህን ቃል ኪዳን የተቀበለ አገር ከሁለት ዕጩዎች በላይ አይጠቁምም፡፡ እነዚህ ዕጩዎች የጠቋሚው አገር ዜቶች መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

3. አንድ ሰው ለኮሚቴው እንደገና የመጠቆም መብት አለው።

## አንቀጽ 30

1. የመጀመሪያው ምርጫ ይህ ቃል ኪዳን ከፀናበት ከስድስት ወራት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ይካሄዳል።
2. በአንቀጽ 34 መሰረት ክፍት ቦታዎችን ለመሙላት ካልሆነ በስተቀር እያንዳዱ ምርጫ ከመካሄዱ ቢያንስ አራት ወራት ቀደም ብሎ የተባበሩት መንግስታት ዋና ፀሐፊ ይህን ቃል ኪዳን የተቀበሉ አገሮች በሶስት ወራት ውስጥ ለኮሚቴው አባልነት ዕጩዎቻቸውን እንዲጠቀሙ በጽሑፍ ይጠይቃል።
3. ዋና ፀሐፊው የተጠቆሙትን ዕጩዎች ዝርዝር በስማቸው ፊደላት ቅደም ተከተል አዘጋጅቶ የጠቆሟቸውን አገሮች ጭምር በማመልከት እያንዳንዱ ምርጫ ከመካሄዱ ከአንድ ወር በፊት ይህን ቃል ኪዳን ለተቀበሉት አገሮች ያቀርባል።
4. የኮሚቴው አባላት ምርጫ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ በድርጅቱ ዋና ጽሕፈት ቤት በሚጠራውና ይህን ቃል ኪዳን የተቀበሉ አባል አገሮች በሚያደርጉት ስብሰባ ይከናወናል። ይህን

ቃል ኪዳን ከተቀበሉ አባል አገሮች ሁለት ሦስተኛው በተገኙበት ምልዓተ ጉባኤ በስብሰባው ላይ አገሮቹን ወክለው ከተገኙትና ድምፅ ከሰጡት መካከል የአብላጫውን ድምፅ ያገኙት ዕጩዎች የኮሚቴው አባላት ይሆናሉ፡፡

## አንቀጽ 31

1. ኮሚቴው ከአንድ አገር ውስጥ ከአንድ ዜጋ በላይ አባል አይኖረውም፡፡
2 በኮሚቴው ምርጫ ረገድ የኮሚቴው አባልነት የተመጣጠነ የአካባቢ ስብጥርን እንዲያንፀባርቅና የተለያዩ የስልጣኔ ዓይነቶችንና አበይት የሕግ ስርዓቶችን እንዲወክል የማድረግ አስፈላጊነት ግምት ውስጥ ይገባል፡፡

## አንቀጽ 32

1. የኮሚቴው አባላት ለአራት ዓመት የስራ ጊዜ ይመረጣሉ፡፡ በድጋሚ ከተጠቆሙ ለሁለተኛ ግዜ

ሊመረጡ ይችላሉ። ይሁን እንጂ በመጀመሪያው ዙር ከተመረጡት ውስጥ የዘጠኙ አባላት የስራ ጊዜ በሁለተኛው ዓመት መጨረሻ ላይ ያበቃል። የመጀመሪያው ምርጫ እንደተፈፀመ ወዲያውኑ በአንቀጽ 30 ንዑስ ቁጥር 4 የተጠቀሰው ስብሰባ ሊቀመንበር በሚያወጣው ዕጣ የዘጠኙ አባላት ስም ይታወቃል።

2. የኮሚቴው አባላት የስራ ጊዜ ሲያበቃ ምርጫዎች ቀደም ባሉት የዚህ ቃል ኪዳን አንቀጾች መሰረት ይከናወናሉ።

## አንቀጽ 33

1. አንድ የኮሚቴው አባል ጊዜያዊ ባልሆነ በማናቸውም ሌላ ምክንያት ስራውን ያቋረጠ መሆኑን የቀሩት አባላት ሁሉም በጋራ ከተስማሙ የኮሚቴው ሊቀመንበር ለተባበሩት መንግስታት ዋና ፀሐፊ ወዲያውኑ ያስታውቃል። ፀሐፊውም በአባሉ ተይዞ የነበረው የኃላፊነት ቦታ ክፍት መሆኑን ይገልጻል።
2. አንድ የኮሚቴ አባል በሞት ከተለየ ወይም ስራውን በራሱ ፈቃድ ከለቀቀ የኮሚቴው ሊቀመንበር ሁኔታውን ለዋና ፀሐፊው ወዲያውኑ የሰታውቃል።

ዋና ፀሐፊውም አባሉ ከሞተበት ወይም ስራውን ከለቀቀበት ጊዜ ጀምሮ ቦታው ክፍት መሆኑን ይገልጻል፡፡

## አንቀጽ 34

1. በአንቀጽ 33 መሰረት የኮሚቴው አባል የስራ ቦታ ክፍት መሆኑ ሲገለጽና ይህ መሆኑ በታወቀ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የተተኪው አባል የስራ ዘመን የማያበቃ ሲሆን፣ ዋና ፀሐፊው ሁኔታውን ለእያንዳንዱ ይህን ቃል ኪዳን ለተቀበለ አገር ያስታውቃል፡፡ እነዚህ አገሮችም በአንቀጽ 29 መሰረት ክፍት የስራ ቦታውን ለመሙላት በሁለት ወራት ጊዜ ውስጥ ዕጩዎቻቸውን ይጠቁማሉ፡፡

2. ዋና ፀሐፊው በፊደል ቅድም ተከተል መሰረት የተጠቆሙትን ዕጩዎች የስም ዝርዝር አዘጋጅቶ ለቃል ኪዳኑ አባል አገሮች ያቀርባል፡፡ ክፍት የስራ ቦታውን ለመሙላትም በዚህ የቃል ኪዳኑ ክፍል ውስጥ በተጠቀሱት አግባብ ባላቸው ድንጋጌዎች መሰረት ምርጫ ይካሄዳል፡፡

3. በአንቀጽ 33 መሰረት የተገለጸውን ክፍት ቦታ ለመሙላት የተመረጠ የኮሚቴ አባል በዚያው አንቀጽ መሰረት የቀድሞው አባል ሳይጨርሰው ለቀረው የስራ ጊዜ በኃላፊነት ይቆያል፡፡

## አንቀጽ 35

በተባበሩት መንግስታት ጠቅላላ ጉባኤ ሲፀድቅና ጠቅላላ ጉባዔው በሚወስነው ሁኔታዎች መሰረት፣ እንዲሁም የኮሚቴውን የስራ ኃላፊነት ክብደት ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ለኮሚቴው አባላት ከተባበሩት መንግስታት ድርጅት ሀብት ላይ ምንዳ ይከፈላቸዋል፡፡

## አንቀጽ 36

ኮሚቴው በዚህ ቃል ኪዳን የተደነገጉትን ተግባራት በሚገባ ማከናወን ይችል ዘንድ የተባበሩት መንግስታት ዋና ፀሐፊ አስፈላጊውን የሰው ኃይልና ድርጅት ያሟላለታል፡፡

## አንቀጽ 37

1. የተባበሩት መንግስታት ዋና ፀሐፊ የኮሚቴውን የመጀመሪያ ስብሰባ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ጽሕፈት ቤት እንዲሰየም ያደርጋል፡፡
2. ከመጀመሪያ ስብሰባ በኋላ ኮሚቴው በራሱ የስነ ስርዓት ደንብ መሰረት በየጊዜው ይሰበሰባል፡፡
3. የኮሚቴው መደበኛ ስብሰባዎች በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ጽሕፈት ቤት ወይም ጄኔቫ በሚገኘው የድርጅቱ ጽሕፈት ቤት ይካሄዳሉ፡፡

## አንቀጽ 38

እያንዳንዱ የኮሚቴው አባል መደበኛ ስራውን ከመጀመሩ በፊት በኮሚቴው ግልጽ ስብሰባ ላይ የተሰጠውን ኃላፊነት ያለ አድሎና በቅን ኅሊና ለመወጣት ቃል ይገባል፡፡

## አንቀጽ 39

1. ኮሚቴው የስራ አስፈፃሚ አባላቱን ለሁለት ዓመት የስራ ጊዜ ይመርጣል። እነዚህም እንደገና ሊመረጡ ይችላሉ።
2. ኮሚቴው የራሱን የስነ ስርዓት ደንቦች ያወጣል። ከእነዚህ ደንቦች ውስጥ የሚከተሉት ሊኖሩ ይገባል፤
   ሀ/ የኮሚቴው ምልዓተ ጉባኤ በ12 አባላት ይሟላል።
   ለ/ የኮሚቴው ውሳኔ የሚፀድቀው በስብሰባው ላይ በተገኙት አባላት አብላጫ ድምፅ ሲደገፍ ይሆናል።

## አንቀጽ 40

1. ይህን ቃል ኪዳን የተቀበሉ አገሮች በዚህ ቃል ኪዳን ተቀባይነት ያገኙትን መብቶች ለማክበር ስለሚወስዷቸው እርምጃዎችና መብቶቹን በማረጋገጥ ረገድ ስለተመዘገቡት ውጤቶች ሪፖርት ሊያቀርቡ ይገባል። ሪፖርቱ የሚቀርበውም

ሀ/ የቃል ኪዳኑ አባል አገሮች ቃል ኪዳኑ ከፀናባቸው ጊዜ አንስቶ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ እና

ለ/ ከዚያ በኋላ ኮሚቴው በጠየቀ ጊዜ ይሆናል፡፡

2. ማንኛውም ዘገባ ለተባበሩት መንግስታት ዋና ፀሐፊ ይቀርባል፡፡ ዋና ፀሐፊውም የደረሱትን ዘገባዎች ኮሚቴው እንዲያያቸው ያስተላልፍለታል፡፡ ዘገባዎቹም ከዚህ ቃል ኪዳን አፈጻጸም ጋር የተያያዙ ጉዳዮችንና ካሉም ችግሮችን ያመለክታሉ፡፡

3. ዋና ፀሐፊው ከኮሚቴው ጋር ከተመካከረ በኋላ ከዘገባዎቹ በስራ ድርሻቸው ክልል ውስጥ የሚገኙትን ክፍሎች ቅጂ ለሚመለከታቸው ልዩ ተልእኮ ለተሰጣቸው የተባበሩት መንግስታት አካላት ማስተላለፍ ይችላል፡፡

4. ኮሚቴው ይህን ቃል ኪዳን የተቀበሉ አገሮች ያቀረቡለትን ሪፖርቶች ይመረምራል፡፡ የራሱን ሪፖርትና ተገቢ ነው ያላቸውን አስተያየቶች ቃል ኪዳኑን ለተቀበሉት አገሮች ያቀርባል፡፡ በተጨማሪም ኮሚቴው አስተያየቱን ቃል ኪዳኑን ከተቀበሉ አገሮች የደረሰው ዘገባ ቅጂውን ጨምሮ

ለኢኮኖሚና ማህበራዊ ምክር ቤት ሊልከው ይችላል፡፡

5. ቃል ኪዳኑን የተቀበሉት አገሮች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 መሰረት በቀረቡት አስተያየቶች ላይ ያላቸውን ሃሳብ ለኮሚቴው ማቅረብ ይችላሉ፡፡

## አንቀጽ 41

1. አንድ ይህን ቃል ኪዳን የተቀበለ አባል አገር በዚህ አንቀጽ የሰፈሩት ግዴታዎች በሌላው ፈራሚ አገር ተፈፃሚነት አላገኙም ብሎ አቤቱታ በሚያቀርብበት ወቅት ኮሚቴው ያንን ተቀብሎ ለመመርመር ላለው ስልጣን በማናቸውም ጊዜ ቢሆን ዕውቅና መስጠት ይችላል፡፡ በዚህ አንቀጽ መሰረት የዚህ ዓይነት አቤቱታ መቀበልም ሆነ ማየት የሚቻለው አቤቱታውን ያቀረበው ቃል ኪዳኑን የተቀበለ አገር ራሱ ለኮሚቴው ስልጣን እውቅና የሰጠ ሲሆን ነው፡፡ እንዲህ ዓይነቱን ዕውቅና ያልሰጠ አገርን የሚመለከት አቤቱታን ኮሚቴው ተቀብሎ አያይም፡፡ በዚህ አንቀጽ መሰረተ ኮሚቴው ዘንድ የደረሱ

አቤቱታዎች ቀጥሎ ያሉትን ስርዓቶች በመከተል እርምጃ ይወሰድባቸዋል፡፡

ሀ/ አንድ ይህን ቃል ኪዳን የተቀበለ አገር ሌላ ቃል ኪዳኑን የተቀበለ አገር የዚህን ሕግ ድንጋጌዎች በስራ ላይ አላዋለም ብሎ ካመነ ቅሬታውን ኃላፊነቱን አልወጣም ላለው አገር በጽሑፍ ያስታውቃል፡፡ ያም አገር ቅሬታው በደረሰው በሶስት ወራት ጊዜ ውስጥ ለላኪው አገር ስለጉዳዩ ማብራሪያ በጽሑፍ ይልካል፡፡ ማብራሪያውም በተቻለ መጠንና እንደየአግባቡ ጉዳዩን የሚመለከቱት በአገሩ ውስጥ ያሉ ስነ ስርዓቶች እና የተወሰዱ፣ ሊወሰዱ የታሰቡ ወይም ያሉ የማሻሻያ እርምጃዎችን መያዝ ይኖርበታል፡፡

ለ/ የመጀመሪያው ቅሬታ በደረሰ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ሁለቱም ቃል ኪዳኑን የተቀበሉትን አገሮች የሚያረካ መፍትሔ ካልተገኘ ከሁለቱ አንዱ አገር ጉዳዩን ለኮሚቴው የማቅረብና ሌላውን አገር ስለዚሁ የማስታወቅ መብት አለው፡፡

ሐ/ ኮሚቴው ጉዳዩን ማየት የሚችለው የሚመለከተው አገር በቅድሚያ የዓለም አቀፍ ሕግ አጠቃላይ

መርሆዎችን በመከተል ባሉት የመፍትሔ ማግኛ መንገዶች ሁሉ በመጠቀም ውጤት ማስገኘት አለመቻሉን ሲያረጋግጥ ብቻ ነው፡፡ መፍትሔዎችን ለማግኘት የሚወስደው ጊዜ በአዕምሮ ግምት ከልክ ያለፈ የተራዘመ ሆኖ ሲገኝ ይህ ደንብ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

መ/ በዚህ አንቀጽ መሰረት የቀረቡለትን ቅሬታዎች ኮሚቴው የሚመረምረው በዝግ ስብሰባዎች ነው፡፡

ሠ/ በፊደል (ሐ) የተጠቀሰው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚቴው በዚህ ቃል ኪዳን ዕውቅና ያገኙትን መሰረታዊ ነፃነቶችና ሰብአዊ መብቶች በሚያስከብር መልክ ጉዳዩ በመግባባት መፍትሔ እንዲያገኝ አገልግሎቱን ለሚመለከታቸው ለሁለቱ ቃል ኪዳን የተቀበሉ አገሮች ያበረክታል፡፡

ረ/ ለእሱ በቀረቡ በማንኛውም አቤቱታዎች ላይ ቃል ኪዳኑን የተቀበሉ የሚመለከታቸው አገሮች በንዑስ አንቀጽ 1(ለ) መሰረት ተጨማሪ መረጃ እንዲያቀርቡለት መጠየቅ ይችላል፡፡

ሰ/ በንዑስ አንቀጽ "ለ" የተጠቀሱት ቃል ኪዳኑን የተቀበሉ አገሮች ኮሚቴው ቅሬታውን

በሚመረምርበት ጊዜ የመወከልና አስተያየታቸውን በቃል ወይም በጽሑፍ የማቅረበ መብት አላቸው፡፡

ሸ/ በንዑስ አንቀጽ "ለ" መሰረት ቅሬታ በደረሰው በ12 ወራት ጊዜ ውስጥ ኮሚቴው በሚከተሉት አገባቦች ዘገባውን ያቀርባል፡፡

1. በንዑስ አንቀጽ "ሠ" መሰረት ለጉዳዩ መፍትሔ ከተገኘ ኮሚቴው በዘገባው ውስጥ ይህንኑና የተባለውን መፍትሔ በአጭሩ ይገልጻል፡፡
2. በንዑስ አንቀጽ "ሠ" መሰረት መፍትሔ ካልተገኘ ኮሚቴው ይህንኑ በዘገባው ውስጥ በአጭሩ ይገለጽና ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሁለቱ ቃል ኪዳኑን የተቀበሉ አገሮች በጹሑፍና በቃል ያቀረቡትን አባሪ አድርጎ ያቀርባል፡፡ ማንኛውም ሁኔታ የኮሚቴው ዘገባ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ባለጉዳዮችና ቃል ኪዳኑን ለተቀበሉ አገሮች እንዲያውቁት ይተላለፋል፡፡

3. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ የሚሆኑት ይህን ቃል ኪዳን ከተቀበሉት አገሮች ውስጥ 10 የሚሆኑት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ለኮሚቴው ስልጣን ዕውቅና መስጠታቸውን ሲያረጋግጡ ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ የጽሑፍ ማረጋገጫ ቃል ኪዳኑን ከተቀበሉት አገሮች ለተባበሩት መንግስታት ዋና ፀሐፊ ይተላለፍና በእርሱ ዘንድ ይቀመጣል፡፡ ዋና ፀሐፊውም ቅጂዎቹን ለሌሎቹ ቃል ኪዳኑን ለተቀበሉ አገሮች ያስተላልፋል፡፡ አንድ ቃል ኪዳኑን የተቀበለ አገር ለዋና ፀሐፊው በማስታወቅ የሰጠውን የስልጣን ዕውቅና የማረጋገጫ ቃል በማንኛውም ጊዜ መሻር ይችላል፡፡ ይሁን እንጂ፣ የስልጣን ዕውቅናን የመሻሩ ጉዳይ ቀደም ሲል የቀረበን ቅሬታ ከመመርመር አያግድም፡፡ ጉዳዩ

የሚመለከተው ቃል ኪዳኑን የተቀበለ አገር ሌላ አዲስ የስልጣን ዕውቅና የማረጋገጫ በጽሑፍ ካልሰጠ በስተቀር ለዋና ፀሐፊው ጽሑፉን የሚሽር መግለጫ ከደረሰው ጊዜ ጀምሮ ኮሚቴው ከዚያ አገር የሚቀርብ ቅሬታ አይቀበልም፡፡

## አንቀጽ 42

1. ሀ/ በአንቀጽ 41 መሰረት ለኮሚቴው የቀረበ ቅሬታ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ቃል ኪዳኑን የተቀበሉ አገሮች በሚያረካ ሁኔታ መፍትሔ ካልተገኘለት እነዚህ አገሮች ኮሚቴው አንድ ጊዜያዊ አስታራቂ ኮሚሽን (ከዚህ በኋላ ኮሚሽን እየተባለ የሚጠቀስ) ይሰይማል፡፡ ኮሚሽኑም ይህን ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳን በማክበር ዓላማ ላይ በመመስረት ሁለቱ የሚመለከታቸው ይህን ቃል ኪዳን የተቀበሉ አባል አገሮች በማግባባት ለጉዳዩ መፍትሔ እንዲያስገኙ አገልግሎቱን ይሰጣል፡፡

ለ/ ኮሚሽኑ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ቃልኪዳኑን የተቀበሉ አገሮች የተስማሙባቸው አምስት አባላት ይኖሩታል:: በሶስት ወራት ጊዜ ውስጥ አገሮቹ በሁሉም የኮሚሽኑ አባላት ወይም በከፊሉ ላይ ካልተስማሙባቸው ኮሚቴው ያልተስማሙባቸውን አባላት የሚተኩ ከራሱ አባላት ውስጥ በሁለት ሦስተኛ አብላጫ ድምፅ በምስጢር ይመርጣል::

2. የኮሚሽኑ አባላት የሚያገለግሉት እራሳቸውን በመወከል ነው:: በተጨማሪም የኮሚሽኑ አባላት ጉዳዩ የሚመለከታቸው አገሮች ዜጎች ወይም ይህን ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳን ያልተቀበሉ አገሮች ዜጎች ወይም በአንቀጽ 41 መሰረት ማረጋገጫ ያልሰጠ አገር ዜጎች መሆን የለባቸውም::
3. ኮሚሽኑ የራሱን ሊቀመንበር ይመርጣል፤ የሚመራበትን የስነ ስርዓት ደንብም ያወጣል::
4. የኮሚሽኑ ስብሰባዎች የሚካሄዱት በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፅሕፈት ቤት ወይም በድርጅቱ የጄኔቫ ፅሕፈት ቤት ውስጥ ይሆናል::

ነገር ግን የተባበሩት መንግስታት ዋና ፀሐፊንና ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ቃል ኪዳኑን የተቀበሉ አገሮች በማማከር ኮሚሽኑ በሌሎች አመቺ ቦታዎች ስብሰባውን ማካሄድ ይችላል፡፡

5. በአንቀጽ 36 መሰረት የተቋቋመው ጽሕፈት ቤት በዚህ አንቀጽ መሰረት የሚቋቋሙ ኮሚሽኖችንም ያገለግላል፡፡
6. ኮሚቴው የተቀበላቸውንና ራሱም ያጠናቀራቸውን መረጃዎችን ኮሚሽኑ ሊያያቸው ይችላል፤ በተጨማሪም ኮሚሽኑ ሌሎች ጠቃሚ መረጃዎችን ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ቃል ኪዳኑን የተቀበሉ አገሮች ማግኘት ይችላል፡፡
7. ኮሚሽኑ የተሰየመበትን ጉዳይ ከመረመረ በኋላ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አገሮች የሚተላለፍ ዘገባ ለኮሚቴው ሊቀመንበር ያቀርባል፡፡ በማናቸውም ጊዜ ዘገባው ኮሚሽኑ ጉዳዩን መመልከት ከጀመረ ከ12 ወራት ጊዜ በላይ ሊዘገይ አይችልም፡፡
   ሀ/ ኮሚሽኑ ጉዳዩን በ12 ወራት ውስጥ መርምሮ ማጠናቀቅ ካልቻለ ዘገባው ጉዳዩ ያለበትን ደረጃ ብቻ ባጭሩ የሚገልጽ ይሆናል፡፡

ለ/ በዚህ ቃል ኪዳን ዕውቅና ያገኙትን ሰብአዊ መብቶች በማክበር ላይ የተመሰረተ የሚያግባባ መፍትሔ ከተገኘ የኮሚሽኑ ዘገባ ፍሬ ነገር በተገቢው መፍትሔ ላይ ያተኩራል፡፡

ሐ/ በንዑስ አንቀጽ 7(ለ) መሰረት መፍትሔ ካልተገኘ የኮሚሽኑ ዘገባ ጉዳዩን በሚመለከት በተነሱት ጥያቄዎች ላይ የሱን ግኝቶችና ለችግሩ ማግባቢያ የተሰጠውን አስተያየቶች ይይዛል፡፡ ይህ ዘገባ በተጨማሪ ጉዳዩ በሚመለከታቸው ቃል ኪዳኑን በተቀበሉ አገሮች የቀረቡትን የጽሑፍና የቃል መግለጫዎች ያጠቃልላል፡፡

መ/ የኮሚሽኑ ዘገባ በንዑስ አንቀጽ 7(ሐ) መሰረት የቀረበ ከሆነ ጉዳዩ የሚመለከታቸው አገሮች ዘገባው በደረሳቸው በሶስት ወራት ጊዜ ውስጥ በዘገባው ይዘት መስማማት ያለመስማማታቸውን ለኮሚቴው ሊቀ መንበር ያስታውቃሉ፡፡

8. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች በአንቀጽ 41 ውስጥ የተጠቀሱትን የኮሚቴውን ኃላፊነቶች የሚነኩ አይሆኑም፡፡

9. ጉዳዩ የሚመለከታቸው ቃል ኪዳኑን የተቀበሉ አገሮች የተባበሩት መንግስታት ዋና ጸሐፊ

በሚያቀርበው ተመን መሰረት የኮሚሽኑን አባላት ወጪዎች በሙሉ እኩል ይከፍላሉ::

10. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የተባበሩት መንግስታት ዋና ፀሐፊ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 9 መሰረት ጉዳዩ የሚመለከታቸው ይህን ቃል ኪዳን የተቀበሉ አገሮች ክፍያውን ከመተካታቸው በፊት የኮሚሽኑን አባላት ወጪዎች የመሸፈን ስልጣን አለው::

## አንቀጽ 43

አግባብ ባላቸው በተባበሩት መንግስታት የልዩ መብቶችና የማይደፈሩ መብቶች ስምምነት ደንጋጌዎች መሰረት የኮሚቴውና በአንቀጽ 42 መሰረት የተሰየሙት የጊዜያዊ አስታራቂ ኮሚሽኑ አባላት ለተባበሩት መንግስታት ተልዕኮ ለሚሰማሩ ባለሙያዎች የሚገባውን ስራ ማከናወኛ፣ ጥቅሞች እና ያለመከሰስ መብት አላቸው::

## አንቀጽ 44

ይህን ቃል ኪዳን በስራ ላይ ለማዋል የተቀመጡት ድንጋጌዎች የተባበሩት መንግስታትና ልዩ ተልእኮ የተሰጣቸው አካላት ስምምነቶችና ማስፈፀሚያ ደንቦች ውስጥ በሰብአዊ መብቶች መስክ የተዘረዘሩትን ስነ ስርዓቶች የሚነኩ አይሆኑም፡፡ በተጨማሪም ድንጋጌዎቹ ይህን ቃል ኪዳን የተቀበሉ አገሮች በመካከላቸው ባሉት አጠቃላይ ወይም ልዩ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች መሰረት በመካከላቸው ያለውን ክርክር ለመፍታት ሌሎች ዘዴዎችን ከመከተል አያግዷቸውም፡፡

## አንቀጽ 45

ኮሚቴው በየዓመቱ ስለስራ እንቅስቃሴው የሚገልጽ ዘገባ በኢኮኖሚና ማህበራዊ ምክር ቤት በኩል ለተባበሩት መንግስታት ጠቅላላ ጉባኤ ያቀርባል፡፡

# ክፍል አምስት

## አንቀጽ 46

የዚህ ቃል ኪዳን ማንኛውም ድንጋጌ የተባበሩት መንግስታት ቻርተር እና ልዩ ተልእኮ የተሰጣቸው የድርጅቱ አካላትና ልዩ ልዩ ክፍሎች በዚህ ቃልኪዳን ውስጥ ከተካተቱት ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ያሏቸውን ኃላፊነትና ተግባር የሚወስኑት መተዳደሪያ ደንቦችን እንደሚያፋልስ ሆኖ አይተረጎምም፡፡

## አንቀጽ 47

የዚህ ቃል ኪዳን ማንኛውም ድንጋጌ ሕዝቦች በተፈጥሮ ሀብታቸውና ችሎታቸው በሙሉና በነፃነት የመጠቀም መብታቸውን እንደሚቀንስ ሆነ አይተረጎምም፡፡

# ክፍል ስድስት

## አንቀጽ 48

1. ይህ ቃል ኪዳን የተባበሩት መንግስታት አባል ለሆነ አገር ወይም ልዩ ተልእኮ ለተሰጣቸው አካላት አባል የሆነ አገር፣ የዓለም አቀፍ ፍርድ ቤትን መተዳደሪያ ደንብ ለተቀበለ አገር፣ እንዲሁም ይህን ሕግ እንዲፈርም በተባበሩት መንግስታት ጠቅላላ ጉባኤ ለተጋበዘ ሌላ አገር ለፊርማ ክፍት ነው።
2. ይህ ቃል ኪዳን በፈራሚ አገሮች መፅደቅ ይኖርበታል። የማጽደቂያ ሰነዶችም በተባበሩት መንግስታት ዋና ፀሐፊ ዘንድ ይቀመጣሉ።
3. ይህ ቃል ኪዳን በዚህ አንቀጽ 1 የተጠቀሰው ማንኛውም አገር እንዲቀበለው ክፍት ይሆናል።
4. መቀበል የሚረጋገጠው የመቀበያ ሰነድን በተባበሩት መንግስታት ዋና ፀሐፊ ዘንድ በማኖር ነው።
5. የተባበሩት መንግስታት ዋና ጸሐፊ ቃል ኪዳኑን የፈረሙ ወይም የተቀበሉ አገሮች እሱ ዘንድ ስለተቀመጡት የማጽደቂያ ወይም የመቀበያ ሰነድ እንዲያውቁ ያደርጋል።

## አንቀጽ 49

1. ይህ ቃል ኪዳን የሚፀናው 35ኛው የማጽደቂያ ወይም የመቀበያ ሰነድ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ ዘንድ ከተቀመጠ ዕለት አንስቶ ከሶስት ወራት በኋላ ነው።
2. 35ኛው የማፅደቂያ ወይም የመቀበያ ሰነድ ከዋና ፀሐፊው ዘንድ ከተቀመጠ በኋላ ይህን ቃል ለሚያጸድቅ ለእያንዳንዱ አገር ቃል ኪዳኑን የሚፀናው የራሱን የማፅደቀያ ወይም የመቀበያ ሰነድ ካኖረበት ዕለት ከሶስት ወራት በኋላ ነው።

## አንቀጽ 50

ፌዴራላዊ አስተዳደር ባላቸው አገሮች የዚህ ቃል ኪዳን ድንጋጌዎች በሁሉም የአስተዳደር ክልሎች ያለምንም ገደብ ወይም ልዩነት ተፈጻሚ ይሆናሉ።

## አንቀጽ 51

1. ይህን ቃል ኪዳን የተቀበለ ማንኛውም አገር ለቃል ኪዳኑ ማሻሻያ ሀሳቦች ለተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ ማቅረብ ይችላል፡፡ ዋና ፀሐፊውም ስለቀረቡት የማሻሻያ ሀሳቦች ይህን ቃል ኪዳን ለተቀበሉት አገሮች በማስታወቅ በቀረቡት ሀሳቦች ላይ ለመወያየትና ድምፅ ለመስጠት ጉባኤ እንዲጠራ ይፈልጉ እንደሆነ እንዲገልጹለት ይጠይቃል፡፡ ቃል ኪዳኑን ከተቀበሉት አገሮች አንድ ሦስተኛው የጉባኤውን መጠራት የሚደግፉ ከሆነ ዋና ፀሐፊው በተባበሩት መንግስታት አማካይነት ጉባኤው እንዲካሄድ ስብሰባውን ያዘጋጃል፡፡ ቃል ከዲኑን ተቀብለው በስብሰባው ከተገኙትና ድምፅ ከሰጡት አገሮች በአብዛኛው አባል የተደገፈው የማሻሻያ ሀሳብ የተባበሩት መንግስታት ጠቅላላ ጉባኤ እንዲያጸድቀው ይቀርብለታል፡፡
2. አንድ የማሻሻያ ሀሳብ በሕግ የሚፀናው የተባበሩት መንግስታት ጠቅላላ ጉባኤና ይህን ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳን ከተቀበሉት መንግስታት ውስጥ ሁለት

ሦስተኛው በአገራቸው ሕገ መንግስታዊ ደንብ መሰረት ሲያፀድቁት ነው።

3. ማሻሻያዎች ስራ ላይ ሲውሉ በተቀበሏቸው አገሮች ላይ አስገዳጅነት ይኖራቸዋል። ሌሎች ይኸን ቃል ኪዳን የተቀበሉ አገሮችም በዚህ ቃል ኪዳን ድንጋጌዎችና ቀደም ሲል በተቀበሏቸው ማሻሻያዎች የሚገደዱ ይሆናሉ።

## አንቀጽ 52

በአንቀጽ 48 ንዑስ አንቀጽ 5 የተጠቀሱት ማስታወቂያዎች ያሉ ቢሆንም የተባበሩት መንግስታት ዋና ፀሐፊ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ ለተጠቀሱት አገሮች ስለሚከተሉት ጉዳዮች ሊገለጽላቸው ይገባል።

ሀ/ በአንቀጽ 48 መሰረት ስለፊርማዎች፣ ማጽደቂያዎችና የመቀበያ ማረጋገጫዎች

ለ/ በአንቀጽ 49 መሰረት ይህ ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳን የሚፀናበትን ጊዜና በአንቀጽ 51 መሰረት ማንኛውም የማሻሻያ ሀሳብ የሚፀናበት ጊዜ።

## አንቀጽ 53

1. ይህ ቃል ኪዳን በተባበሩት መንግስታት ድርጅት መዝገብ ቤት ይቀመጣል፤ የቃል ኪዳኑ የቻይንኛ፣ የእንግሊዝኛ፣ የፈረንሳይኛ፣ የሩሲያንኛና የስፓንኛ ቋንቋ ቅጂዎች እኩል እውቅና ይኖራቸዋል።
2. የተባበሩት መንግስታት ዋና ፀሐፊ የዚህን ቃል ኪዳን የተረጋገጡ ቅጂዎች በአንቀጽ 48 ውስጥ ለተጠቀሱት አገሮች ያስተላልፋል።

# በሴቶች ላይ የሚደረግ ማንኛውንም አድላዊ ልዩነት ለማስወገድ የተደረገ ስምምነት

*የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ ቁጥር 34/180 እ.ኤ.አ ዲሴምበር 18 ቀን 1979 ተቀባይነት አግኝቶ ለአባል አገራት ፊርማ የቀረበ። ስራ ላይ የዋለበት ጊዜ እ.ኤ.አ. ሴኘቴምበር 3 ቀን 1981*

**ይህን ስምምነት የተቀበሉ አገሮች፣**

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ቻርተር በሰዎች መሰረታዊ መብቶች፣ በሰው ልጅ ክቡርነትና በወንዶችና ሴቶች የእኩልነት መብት፣ እምነት ላይ የተመረኮዘ መሆኑን በመገንዘብ፣

የሰብአዊ መብቶች ዓለም አቀፍ መግለጫ ለአድሏዊ ልዩነት ተቀባይነት በሚነሳ መርህ ላይ የተመሠረተ መሆኑን፤ ሰዎች ሁሉ ነፃ ሆነው መወለዳቸውንና እኩል መብትና ክብር ያላቸው መሆኑን፣ እንዲሁም ማንኛውም ሰው በመግለጫው በተዘረዘሩት መብቶችና ነጻነቶች ጾታን ጨምሮ ያለምንም ልዩነት ተጠቃሚ መሆኑን እንደሚያረጋግጥ በማጤን፤

የሰብአዊ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃልኪዳኖችን የተቀበሉ አገሮች ወንዶችና ሴቶች በኢኮኖሚ፣ በማሕበራዊ፣ በሲቪልና በፖለቲካ መብቶች እኩል እንዲጠቀሙ የማድረግ ግዴታ እንዳለባቸው በመረዳት፣

በተባበሩት መንግሥታትና ልዩ ተልእኮ በተሰጣቸው የድርጅቱ አካላት አማካይነት የወንዶችንና የሴቶችን መብቶች እኩልነት ለማረጋገጥ የጸደቁትን ዓለም አቀፍ ስምምነቶች በመገንዘብ፣

እንዲሁም በተባበሩት መንግሥታትና ልዩ ተልእኮ በተሰጣቸው የድርጅቱ አካላት አማካይነት የወንዶችንና የሴቶችን መብቶች እኩልነት ለማረጋገጥ የተላለፉትን ውሳኔዎች፣ መግለጫዎችና የእርምጃ ሀሳቦች በማስታወስ፣

እነዚህ እርምጃዎች ቢወሰዱም ቅሉ በሴቶች ላይ የሚደረገው አድሎአዊ ልዩነት መቀጠሉን በማሰብ፣

በሴቶች ላይ የሚደረግ አድሎአዊ ልዩነት የመብቶች እኩልነትን መርህ የሚጥስና የሰውን ልጅ

ክብር የሚፃረር መሆኑን፣ ሴቶች ከወንዶች እኩል በአገሮቻቸው ፖለቲካዊ፣ ማሕበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ባሕላዊ ሕይወት ውስጥ ሊኖራቸው የሚገባውን ተሳትፎ የሚያሰናክል መሆኑን፣ የሕብረተሰብንና የቤተሰብ ብልፅግናና ዕድገት የሚቀጭና ሴቶች ለሰው ዘርና ለአገሮቻቸው አገልግሎት ለመስጠት ያላቸው እምቅ ችሎታ እንዳያጎለብቱ የሚያደናቅፍ መሆኑን በመገንዘብ፤

ድህነት በተንሰራፋበት ሁኔታ ውስጥ ሴቶች ምግብ፣ የጤና አገልግሎት፣ የትምህርት፤ የስልጠናና የስራ ዕድል ለማግኘትና ሌሎች ፍላጎቶቻቸውን ለሟሟላት ያላቸው ዕድል ጠባብ መሆኑን በማሰብ፤

አዲሱ የዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ስርዓት በርትዕና በፍትሕ ላይ መመስረቱ በወንዶችና በሴቶች መካከል እኩልነትን ለማስፈን በከፍተኛ ደረጃ እንደሚረዳ በማመን፤

የአፓርታይድ፣ የማንኛውም ዓይነት ዘረኛነትና በዘር ላይ የተመሰረተ አድሎአዊነት፤ የቅኝ አገዛዝና

የስውር ቅኝ አገዛዝ፣ የጠብ አጫሪነት፣ የባዕዳን ወረራ፣ ተጽዕኖና በሌሎች አገሮች የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ መግባት እንዲወገድ ማድረግ ወንዶችና ሴቶች መብቶቻቸውን በእኩልነት እንዲጠቀሙባቸው አስፈላጊ መሆኑን ትኩረት በመስጠት፣

የዓለም አቀፍ ሰላምና ፀጥታ መጠናከር፣ የዓለም አቀፍ ውጥረት መርገብ፣ በሁሉም አገሮች መካከል በማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ስርዓቶቻቸው ምክንያት ልዩነት ሳይደረግ የጋራ ትብብር መኖር፣ የአውዳሚ መሳሪያዎች ትጥቅ ሙሉ በሙሉ መፍታት፣ በተለይም በጠበቀና ስኬታማ ዓለም አቀፍ ቁጥጥር ስር የኑክሊየር ጦር መሳሪያዎች ትጥቅ መፍታት፣ በአገሮች መካከል በሚኖር ግንኙነት የፍትሕ፣ የእኩልነትና የጋራ ጥቅም መርሖዎች መስፍን፣ በባዕዳን የቅኝ አገዛዝ ቀንበር ስር ያሉ ሕዝቦች የራስን ዕድል በራስ የመወሰንና ነጻነታቸውን ለማጎናጸፍ መቻል፣ የአገራዊ ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት መከበር፣ ማሕበራዊ ዕድገትን በማጠናከር በሴቶችና በወንዶች መካከል እኩልነት እንዲኖር ያለውን አስተዋፅኦ በማረጋገጥ፣

የአንድ አገር የተሟላ ዕድገት፣ የዓለም ደህንነትና የሰላም ተልዕኮ የሴቶችን በሁሉም መስክ ከወንዶች እኩል ከፍ ያለ ተሳትፎ የሚጠይቅ መሆኑን በማመን፤

እስካሁን በደንብ ዕውቅና ያላገኘውን የቤተሰብን ደሕንነትና የሕብረተሰብን ዕድገት በማሟላት ረገድ ሴቶች የሚያደርጉት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ከግምት በማስገባት፤ እናትነት ያለውን ማሕበራዊ አስተዋፅኦ እና ሁለቱም ወላጆች በቤተሰብ ውስጥና ሕፃናትን በማሳደግ ረገድ ያላቸውን ሚና በመገንዘብ፣ ሴቶች የሰውን ልጅ ዘር በማብዛት በኩል ያላቸው ሚና የአድሎአዊ ልዩነት መሰረት መሆን እንደሌለበትና ሕፃናትን ማሳደግ ወንዶች፣ ሴቶችና ሕብረተሰቡ በአጠቃላይ መጋራት ያለባቸው ኃላፊነት መሆኑን በመረዳት፣

በወንዶችና በሴቶች መካከል ሙሉ እኩልነት ለማስፈን ወንዶችና ሴቶች በልማድ በሕብረተሰብና በቤተሰብ ውስጥ የነበሯቸው ሚናዎች መለወጥ እንዳለባቸው በመገንዘብ፤

በሴቶች ላይ የሚደረግ አድሎአዊ ልዩነትን ለማስወገድ በወጣው መግለጫ ውስጥ የቀረቡትን መርሆዎች በስራ ላይ ለማዋልና ለዚሁ ዓላማም ማንኛውንም ዓይነት አድሏዊ ልዩነት ለማጥፋት አስፈላጊ እርምጃዎችን ለመውሰድ ቆርጠው በመነሳት፣ ከዚህ እንደሚከተለው ተስማምተዋል፡፡

## ክፍል አንድ

## አንቀጽ 1

በዚህ ስምምነት ውስጥ «በሴቶች ላይ የሚደረግ አድልዎና ልዩነት» ማለት ጾታን መሰረት በማድረግ ሴቶች አገቡም አላገቡም፣ ከወንዶች ጋር በእኩልነት በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚ፣ በማሕበራዊ፣ ባሕላዊ፣ በሲቪል ወይም ሌሎች መስኮች የሰብአዊ መብቶችና መሰረታዊ ነጻነቶች ሙሉ ተጠቃሚ እንዳይሆኑ የሚያደርግ ማንኛውም ልዩነት፣ ማግለል ወይም መገደብ ማለት ነው፡፡

## አንቀጽ 2

ይህን ስምምነት የተቀበሉ አገሮች በሴቶች ላይ የሚደረገውን ማንኛውንም ዓይነት አድሎአዊ ልዩነት ያወግዛሉ፤ ማንኛውንም ተገቢ መንገድ በአፋጣኝ በመጠቀም በሴቶች ላይ የሚደረግ አድሏዊ ልዩነትን የማጥፋት ፖሊሲ ይከተላሉ። እናም ይህን ለማሳካትም፦

ሀ/ እስካሁን ያልተካተተ ከሆነ የወንዶችንና የሴቶችን እኩልነት በብሔራዊ ሕገ መንግስቶቻቸው ወይም ሌሎች አግባብ ባላቸው ሕጎቻቸው ውስጥ ለማካተት፣ እንዲሁም ይህን መርሕ በሕግና በሌላ ዘዴ ለመተግበር፤

ለ/ በሴቶች ላይ የሚደረግ አድልዎና ልዩነት ተገቢውን ሕግ በማውጣትና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እንደ ማዕቀብ የመሰለውን እርምጃ ጭምር በመውሰድ ለማገድ፤

ሐ/ ለሴቶች መብቶች ከወንዶች እኩል የሕግ ጥበቃ ለማድረግ፣ እንዲሁም ብቃት ባላቸው አገራዊ ፍርድ ቤቶችና ሌሎች የመንግስት ተቋማት አማካይነት በሴቶች ላይ አድልዎና ልዩነት እንዳይደረግባቸው ለመከላከል፤

መ/ በሴቶች ላይ አድልዎና ልዩነት ከሚፈጥር ድርጊት ወይም አሰራር ለመታቀብና የመንግስት መስሪያ ቤቶችና ባለስልጣናት ይህን ግዴታ ማክበራቸውን ለማረጋገጥ፤

ሠ. በማንኛውም ሰው፣ ድርጅት ወይም የንግድ ሥራ ተቋም አማካይነት በሴቶች ላይ የሚደረግ አድሏዊ ልድነትን ለማስወገድ ተገቢውን እርምጃ ሁሉ ለመውሰድ

ረ/ በሴቶች ላይ አድልዎና ልዩነት የሚፈጥሩ ሕጎችንና ደንቦችን ለማሻሻል ወይም ለመሻር ልማዶችንና አሰራሮችን ለማረም ወይም ለማስተካከል ሕግ ለማውጣትና ተገቢውን እርምጃ ሁሉ ለመውሰድ፤

ሰ/ በሴቶች ላይ አድልዎና ልዩነት የሚፈጥሩ አገራዊ የወንጀለኛ መቅጫ ሕጎችን ለመሻር፤ ተስማምተዋል።

## አንቀጽ 3

የሴቶችን ስብዕና የሚያበለጽጉና ዕድገታቸውንም የሚያፋጥኑ ማናቸውንም ተገቢ እርምጃዎች በተለይም ሴቶች በመብቶቻቸው ከወንዶች ጋር በእኩልነት መጠቀም ይችሉ ዘንድ ሕግ ማውጣትን ጨምሮ ተገቢ

የሆኑ ፖለቲካዊ፣ ማሕበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ እርምጃዎችን የመውሰድ ግዴታ በአባል አገሮች ላይ ተጥሎባቸዋል፡፡

## አንቀጽ 4

1. ይህን ስምምነት የተቀበሉ አገሮች በወንዶችና በሴቶች መካከል በተጨባጭ እኩልነትን በፍጥነት ለማስፈን የሚወስዷቸው ልዩ ጊዜያዊ እርምጃዎች በዚህ ስምምነት ውስጥ እንደ አድሎአዊ ልዩነት አይቆጠሩም፡፡ የእነዚህ እርምጃዎች ውጤት ግን ያልተመጣጠኑ ወይም የተለያዩ ደረጃዎች እንዲሰፍኑ ማድረግ መሆን የለበትም፡፡ እኩል ዕድልና አያያዝ የማስገኘቱ ዓላማ ስኬታማ ከሆነ በኋላ እነዚህ እርምጃዎች መቋረጥ አለባቸው፡፡
2. ይህን ስምምነት የተቀበሉ አገሮች እናትነትን ለመንከባከብ የሚወስዷቸው ልዩ እርምጃዎች፣ በዚህ ስምምነት ውስጥ የተደነገጉት ጭምር ፣ እንደ አድሎአዊ ልዩነት አይቆጠሩም፡፡

## አንቀጽ 5

ይህን ስምምነት የተቀበሉ አገሮች የሚከተሉትን ዓላማዎች ለማሳካት ተገቢ እርምጃዎችን ሁሉ ይወስዳሉ፣

ሀ/ አንዱ ጾታ ከሌላው ያንሳል ወይም ይበልጣል በሚል እምነት ወይም በልማዳዊ የወንዶችና የሴቶች ሚናዎች ላይ የተመሰረቱትን ባሕላዊና ትክክለኛ ያልሆኑ አመለካከቶችና አሰራሮችን ለማጥፋት የወንዶችና የሴቶችን ባሕላዊና ማሕበራዊ ባሕርያት ለማሻሻል፤

ለ/ የቤተሰብ ትምህርት እናትነት ማሕበራዊ ተግባር ስለመሆኑ ትክክለኛ ግንዛቤ መስጠቱን ለማረጋገጥ፣ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻቸውን ለማሳደግና በአእምሮና በአካል ለማበልፀግ የጋራ ኃላፊነት ያለባቸው መሆኑን ዕውቅና ለመስጠት፤ በዚህም ግንኙነት ከሁሉ አስቀድሞ የሕጻናት መብትና ጥቅም የላቀ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ ለማስገንዘብ።

## አንቀጽ 6

ይህን ስምምነት የተቀበሉ አገሮች በማናቸውም መልክ በሴቶች መነገድንና ሴቶችን በዝሙት ስራ በማሠማራት መበዝበዝን ለማስወገድ ሕግ ማውጣትን ጨምሮ ተገቢውን እርምጃ ሁሉ ይወስዳሉ፡፡

## ክፍል ሁለት

## አንቀጽ 7

ይህን ስምምነት የተቀበሉ አገሮች ሴቶች በአገሪቱ የፖለቲካና ሕዝብ ነክ ሕይወት ውስጥ የተሟላ ተሳትፎ እንዳይኖራቸው የሚያስናክል ልዩነትን ለማጥፋት ተገቢ እርምጃዎችን ሁሉ ይወስዳሉ፡፡ በተጨማሪም ሴቶች ከወንዶች እኩል የሚከተሉትን መብቶች መጎናፀፋቸውን ያረጋግጣሉ፣

ሀ/ በሁሉም ምርጫዎችና ውሳኔ ሕዝብ ድምጽ የመስጠትና ለማናቸውም በሕዝብ ለሚመረጡ መንግስታዊ አካላት ዕጩ ተመራጭ የመሆን መብት፤

ለ/ የመንግስት ፖሊሲን በመቅረጽና በማስፈጸም ሂደት ውስጥ የመሳተፍ፣ የመንግስት ባለስልጣን የመሆን፣ በማናቸውም የመንግስት ዕርከን ውስጥ ኃላፊነትን ተረክቦ የመስራት መብት፣

ሐ/ በማናቸውም የአገሪቱ የፖለቲካና የሕዝብ ሕይወት በሚመለከታቸው መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ማሕበራት ውስጥ የመሳተፍ መብት::

## አንቀጽ 8

ይህን ስምምነት የተቀበሉ አገሮች ሴቶች ከወንዶች እኩልና ምንም ልዩነት ሳይደረግባቸው መንግስቶቻቸውን በዓለም አቀፍ ደረጃ የመወከልና በዓለም አቀፍ ድርጅቶች ስራ ውስጥም የመሳተፍ ዕድል ማግኘታቸውን ያረጋግጣሉ::

## አንቀጽ 9

1. ይህን ስምምነት የተቀበሉ አገሮች ሴቶች ከወንዶች እኩል ዜግነት የማግኘት፣ የመለወጥ ወይም ይዞ የመቆየት መብቶችን ያረጋግጡላቸዋል:: በተለይም

የውጭ ዜጋ ማግባታቸው ወይም የባለቤትየው ዜግነቱን በጋብቻ ዘመን መለወጥ የሴትዬዋም ዜግነት ወዲያው መለወጥ ያለመሆኑን፣ ወይም አገር አልባ የሚያደርጋት ወይም የባሌቤቷን ዜግነት እንድትወስድ የሚያስገድዳት ያለመሆኑን ያረጋግጣሉ።

2. ይህን ስምምነት የተቀበሉ አገሮች ሴቶች የልጆቻቸውን ዜግነት በሚመለከት ከወንዶች እኩል መብት እንዲኖራቸው ያደርጋሉ።

## ክፍል ሶስት

## አንቀጽ 10

ይህን ስምምነት የተቀበሉ አገሮች ሴቶች በትምህርት መስክ ከወንዶች እኩል መብቶች እንዲኖራቸው ለማድረግና ማንኛውም ዓይነት አድሎአዊ ልዩነት እንዳይደረግባቸው ለማረጋገጥ ተገቢ እርምጃዎችን ሁሉ ይወስዳሉ። በተጨማሪም ሴቶች ከወንዶች እኩል የሚከተሉት እንዲሟሉላቸው ያደርጋሉ፣

ሀ/ ሙያቸውን ለማበልፀግና ስራቸውን ለማሻሻል በሚሰጥ የምክር አገልግሎት፣በከተማም ሆነ በገጠር ውስጥ በማንኛውም ዓይነት የትምህርት ተቋም ውስጥ ተምሮ ዲፕሎማም ሆነ ዲግሪ ለማግኘት ተመሳሳይ ሁኔታዎች እንዲፈጠርላቸው፤ ይህም እኩልነት በመዋዕለ ሕፃናት፤ በአጠቃላይ ፣በቴክኒክ፣ በሙያና ከፍተኛ የቴክኒክ ትምህርት መስኮች ሁሉ እንዲኖር ለማድረግ፤

ለ/ ተመሳሳይ ስርዓተ ትምህርቶች፣ ፈተናዎች፣ ተመጣጣኝ የሙያ ብቃት ያላቸው መምህራን፣ ተመሳሳይ ጥራት ያላቸው ትምህርት ቤቶች (ሕንፃ፣ የትምህርት ክፍሎች፣ ግቢው፣ ወዘተ) እና የትምህርት መሳሪያዎች የማግኘት ዕድል፤

ሐ/ አንድ ላይ እንዲማሩ በማበረታታትና በሌሎች ትምህርታዊ ዘዴዎች፣ በተለይም መማሪያ መፃሕፍትን፣ የትምህርት ፕሮግራሞችንና የማስተማር ዘዴዎችን በማሻሻል ስለወንዶችና ሴቶች ሚናዎች መሰረተቢስና ኋላቀር አመለካከቶችን በማናቸውም የትምህርት ደረጃና ዓይነት ማስወገድ፤

መ/ በነፃ ትምህርት ዕድልና ሌሎች ለተማሪዎች በሚሰጡ ድጋፎች እኩል ተጠቃሚ የመሆን ዕድል፤

ሠ/ በመሠረተ ትምህርት ፕሮግራሞችና በተለይም በሴቶችና በወንዶች መካከል ያለውን የትምህርት ክፍተት ባጭር ጊዜ ውስጥ ለማጥበብ በሚሰጠው የጎልማሶች ትምህርት ጭምር በተከታታይ የትምህርት ፕሮግራሞች ውስጥ ለመሳተፍ እኩል ዕድል የማግኘት፤

ረ/ ትምህርታቸውን የሚያቋርጡ ሴት ተማሪዎችን ቁጥር መቀነስና ያቋረጡትን ትምህርት የሚቀጥሉበት ፕሮግራም ማዘጋጀት፤

ሰ/ በስፖርትና የአካል ብቃት ትምህርት እኩል በንቃት የመሳተፍ ዕድል እንዲኖራቸው ማድረግ፤

ሸ/ የቤተሰብን ጤንነትና ደኅንነት ለማረጋገጥ የሚረዳ ስለቤተሰብ ምጣኔ የሚሰጥ ምክርን ጨምሮ አስፈላጊውን ትምህርታዊ መረጃ የማግኘት ዕድል እንዲያገኙ ማድረግ፡፡

## አንቀጽ 11

1. ይህን ስምምነት የተቀበሉ አገሮች ሴቶች ከወንዶች እኩል ተመሳሳይ መብቶች ይኖራቸው ዘንድ በስራ መስክ በሴቶች ላይ የሚደረግ አድሎአዊ ልዩነትን ለማስወገድ ተገቢውን እርምጃዎች ሁሉ ይወስዳሉ። በተለይም ከዚህ የሚከተሉትን መብቶች ለሴቶች ያረጋግጣሉ፣

ሀ/ የመስራት መብት የሰው ልጆች ሁሉ የማይገሰስ መብት መሆኑን፤

ለ/ ተመሳሳይ የቅጥር መስፈርቶች መጠቀምን ጨምሮ ተመሳሳይ የስራ ዕድሎች የማግኘት መብት፣

ሐ/ በነፃ ሙያንና ስራን የመምረጥ መብት፣ የደረጃ ዕድገት፣ የስራ ዋስትና፣ ጥቅማ ጥቅሞችንና የአገልግሎት ሁኔታን የማግኘት መብት፣ የሙያ ስልጠናና መልሶ ስልጠናን በስራ ላይ ስልጠናንና የላቀ የሙያ ስልጠናን የማግኘት መብት፤

መ/ ጥቅማ ጥቅሞችን ጨምሮ እኩል ክፍያ የማግኘት፣ እኩል ክብደት ላለው ስራ እኩል መጠቀም ስራ ጥራት ሲገመገም እኩል የመታየት መብት፤

ሠ/ የማሕበራዊ ዋስትና መብት፣ በተለይም በጡረታ፣ በስራ አጥነት፣ በሕመም ፣በአካለ ስንኩልነት፣ በእርጅናና በሌላ ምክንያት ስራ መስራት በሚያዳግትበት ጊዜ እንዲሁም ከክፍያ ጋር የስራ ፈቃድ የማግኘት መብት፤

ረ/ የጤና እንክብካቤንና፣ ዘር ማፍራትን ጨምሮ የራስን ደኅንነት የሚያረጋግጡ አመቺ የስራ ሁኔታዎች የማግኘት መብት፤

2. ሴቶች በጋብቻ ወይም በወሊድ ምክንያት አድሎአዊ ልዩነት እንዳይደረግባቸውና የመስራት መብታቸውን ለማረጋገጥ፣ ይህን ስምምነት የተቀበሉ አገሮች በሚከተሉት መስኮች ተገቢ እርምጃዎችን ይወስዳሉ፤

ሀ/ በእርግዝና ወይም በወሊድ ምክንያት ከስራ መባረርንና ከጋብቻ ጋር በተያያዘ ምክንያት በሚኖር ከስራ ማባረር ላይ አድሎአዊ ልዩነትን ለማገድ፤ ይህን ዓይነት እርምጃ በሚወስዱ ወገኖች ላይ ተገቢውን ሕጋዊ እርምጃ ለመውሰድ፤

ለ/ የወሊድ ፈቃድ ከክፍያ ጋር ወይም ከተመጣጣኝ ማኅበራዊ ጥቅም ጋር፣ የበፊቱን ስራ፣ የስራ ልምድ መጠን፣ ወይም ማሕበራዊ አበል ሳያጡ እንዲቀጥሉ ለማድረግ፤

ሐ/ ወላጆች የቤተሰብ ኃላፊነትን ከስራ ግዴታና የማሕበራዊ ኑሮ ተሳትፎ ጋር አጣምረው እንዲይዙ ለማበረታታት አስፈላጊ ድጋፍ ሰጭ ማሕበራዊ አገልግሎቶች በተለይም የሕፃናት መንከባከቢያዎች በየቦታው እንዲቋቋሙና እንዲደራጁ ለማድረግ፣

መ/ በእርግዝና ጊዜ ለጤንነታቸው አደገኛ መሆናቸው የተረጋገጡ የስራ ዓይነቶች በተመለከተ ለሴቶች ልዩ ጥንቃቄ ለማድረግ፤

3. በዚህ አንቀጽ ውስጥ የተዘረዘሩ ጉዳዮችን በሚመለከት የወጡ የጥበቃ ወይም የመከላከያ ሕጎች በየጊዜው ከሳይንሳዊና ቴክኖሎጂያዊ ዕውቀት አንፃር እንዲገመገሙና እንደ አስፈላጊነቱ እንዲሻሻሉ፣ እንዲሻሩ ወይም እንዲቀጥሉ ለማድረግ፣

## አንቀጽ 12

1. ይህን ስምምነት የተቀበሉ አገሮች የቤተሰብ ምጣኔን ጨምሮ በጤና አገልግሎቶች እኩል ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ በጤና አጠባበቅ መስክ በሴቶች ላይ የሚደረግ አድልዎና ልዩነት ለማስወገድ አስፈላጊውን እርምጃ ሁሉ ይወስዳሉ።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለጸው ቢኖርም ሴቶች በእርግዝና፣ በወሊድና ከወሊድ በኋላ ባሉት

ወቅቶች ሁሉ ተገቢውን ማሕበራዊ አገልግሎት፣ እንደ አስፈላጊነቱም ተገቢውን ነፃ አገልግሎት ፣ምግብና እንክብካቤ የሚያገኙባቸውን መንገዶች ለማረጋገጥ ይህን ስምምነት የተቀበሉ አገሮች እርምጃዎችን እንዲወስዱ ይጠበቅባቸዋል፡፡

## አንቀጽ 13

ይህን ስምምነት የተቀበሉ አገሮች በሌሎች የኢኮኖሚና ማሕበራዊ መስኮች በሴቶች ላይ የሚደረግ አድሎአዊ ልዩነት በማጥፋት ሴቶች ከወንዶች እኩል የሚከተሉት መብቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተገቢ እርምጃዎችን ሁሉ ይወስዳሉ፤ በተለይም፡-

ሀ/ የቤተሰብ ጥቅማ ጥቅም የማግኘት መብት፤

ለ/ ለቤት መስሪያ ወይም መግዣና ለሌሎች ጉዳዮች ከባንክም ሆነ ከሌላ ምንጭ የገንዘብ ብድር አገልግሎት የማግኘት መብት፤

ሐ/ በመዝናኛ፣ በስፖርትና በሌሎች ባሕላዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የመሳተፍ መብት፡፡

# አንቀጽ 14

1. ይህን ስምምነት የተቀበሉ አገሮች የገጠር ሴቶች ያሉባቸውን ልዩ ችግሮችና የቤተሰቦቻቸውን ኢኮኖሚያዊ ሕልውና በማስጠበቅ በኩልና በገንዘብ ያልተተመነ የአገሪቱ ክፍለ ኢኮኖሚ ውስጥ ጭምር ያላቸውን ከፍተኛ አስተዋፅኦ ግምት ውስጥ በማስገባት የዚህን ስምምነት ድንጋጌዎች ለገጠር ሴቶችም ተፈፃሚነታቸውን ለማረጋገጥ ተገቢውን እርምጃ ሁሉ ይወስዳሉ፡፡
2. ይህን ስምምነት የተቀበሉ አገሮች በገጠር ሴቶች ላይ የሚደረግ አድሎአዊ ልዩነት በማጥፋት ሴቶች ከወንዶች እኩል በገጠር ልማት እንቅስቃሴ ውስጥ እንዲሳተፉና ከዚሁም ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ተገቢውን እርምጃ ሁሉ ይወስዳሉ፡፡ በተጨማሪም ለሴቶች የሚከተሉትን መብቶች ያረጋግጣሉ፤

   ሀ/ በሁሉም ደረጃ ባለ የልማት ዕቅድ የመንደፍና የማስፈፀም ስራ ውስጥ የመሳተፍ መብት፤

   ለ/ የቤተሰብ ምጣኔን የሚመለከት መረጃን፣ የምክርና ሌሎች ተዛማጅ አገልግሎቶችን

ጨምሮ በቂ የጤና እንክብካቤ አገልግሎቶችን የማግኘት መብት፤

ሐ/ በማህበራዊ ዋስትና ፕሮግራሞች ቀጥተኛ ተጠቃሚ የመሆን መብት፤

መ/ የቴክኒክ ብቃታቸውን ለማጎልበት መሰረተ ትምህርትን ጨምሮ ማናቸውንም ዓይነት መደበኛና መደበኛ ያልሆነ ስልጠናና ትምህርት የማግኘት፣ የማሕበረሰብና የኤክስቴንሽን አገልግሎቶች ተጠቃሚ የመሆን መብት፤

ሠ/ ስራ በመቀጠር ወይም የራስን ስራ በመፍጠር በኢኮኖሚ የመሻሻል እኩል ዕድል እንዲኖር የራስን አገዝ ቡድኖችንና የሕብረት ስራ ማሕበራትን የማቋቋም መብት

ረ/ በማንኛውም የማኅበረሰብ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የመሳተፍ መብት፤

ሰ/ የግብርና የብድር አገልግሎት፣ የመገበያያና የተስማሚ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ የመሆን መብት፣ መሬት የማግኘት፣ የገጠር ማሻሻያዎችና የሰፈራ ፕሮግራሞች እኩል ተጠቃሚ የመሆን መብት፤

በ/ የመኖሪያ ቤት፣ የአካባቢ ንጽሕና፣ የኤሌክትሪክና የውሃ አቅርቦት፣ ትራንስፖርትና መገናኛን በሚመለከት በቂ የኑሮ ሁኔታ ተጠቃሚ የመሆን መብት።

## ክፍል አራት

## አንቀጽ 15

1. ይህን ስምምነት የተቀበሉ አገሮች ሴቶች በሕግ ፊት ከወንዶች እኩል መብት እንዲኖራቸው ያደርጋሉ።
2. ይህን ስምምነት የተቀበሉ አገሮች በፍትሐብሔር ጉዳዮች ሴቶች ከወንዶች ጋር ተመሳሳይ የሕግ ችሎታ እንዲኖራቸውና ይህንንም የሕግ ችሎታ የመጠቀም እኩል ዕድል እንዲኖራቸው ያደርጋሉ። በተለይም ውል ለመዋዋልና ንብረትን ለማስተዳደር ለሴቶች እኩል መብት ይሰጣሉ። በፍርድ ቤቶችና በችሎቶችም ሴቶች እኩል እንዲስተናገዱ ያደርጋሉ።
3. ይህን ስምምነት የተቀበሉ አገሮች የሴቶችን የሕግ ችሎታ የሚገድብ ማንኛውም ውልና ሌላ ሕጋዊ

የግል ስምምነት ይሽራሉ፣ ወይም ሕገ ወጥ ያደርጋሉ፡፡

4. ይህን ስምምነት የተቀበሉ አገሮች የመንቀሳቀስና የመኖሪያ አገርን፣ ቤትን/ሰፈርን በነፃነት የመምረጥ ሕግን በሚመለከት ለወንዶችና ለሴቶች እኩል መብት ይሰጣሉ፡፡

## አንቀጽ 16

1. ይህን ስምምነት የተቀበሉ አገሮች ከጋብቻና የቤተሰብ ግንኙነቶች አንፃር በሴቶች ላይ የሚደረግ አድሎአዊ ልዩነት ለማጥፋት ተገቢውን እርምጃ ሁሉ ይወስዳሉ፡፡ በተለይም ሴቶች ከወንዶች እኩል የሚከተሉት መብቶች ተጠቃሚ መሆናቸውን ያረጋግጣሉ፡፡

   ሀ/ ትዳር የመመስረት እኩል መብት፤

   ለ/ የትዳር ጓደኛን የመምረጥና ጋብቻን በውዴታና በነፃ ፍላጎት ብቻ የመፈፀም መብት፣

   ሐ/ በጋብቻ ወቅትና ጋብቻው ሲፈርስ እኩል መብትና ግዴታ፤

መ/ የጋብቻቸው ሁኔታ ምን ሆነ ምን ልጆቻቸውን በሚመለከት በወላጅነታቸው እኩል መብትና ግዴታ፤ በዚህ ረገድ ቀዳሚውን ስፍራ የሚይዘው የልጆቹ ደህንነትና ጥቅም ብቻ ይሆናል፡፡

ሠ/ ስንት ልጆችና በምን ያህል የጊዜ ርቀት መውለድ እንዳለባቸው በነፃነትና በኃላፊነት እኩል የመወሰን መብትና በዚህ መብት ለመጠቀም የሚያስችላቸውን መረጃ፣ ትምህርትና ዘዴ የማግኘት መብት፤

ረ/ የልጆች አሳዳጊነትን፣ ሞግዚትነትን፣ ባለአደራነትንና ጉዲፈቻን ወይም እነዚህ ፅንሰ ሀሳቦች በሕግ በተደነገጉበት ሁኔታ ውስጥ ተቋማቱን በሚመለከት ከወንዶች ጋር ተመሳሳይ መብት የማግኘት፤ ይህም ሆኖ የልጆቹ ጥቅምና ደህንነት ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ይሆናል፡፡

ሰ/ የቤተሰቡን የጋራ መጠሪያ ስም፤ ሙያና የመተዳደሪያ ስራን መምረጥን ጨምሮ ባልና ሚስት ተመሳሳይ መብት የማግኘት፤

ሸ/ በክፍያም ሆነ በነፃ የንብረት ባለቤት መሆንን፣ ከሌላ ማግኘትን፣ መምራትን፣ ማስተዳደርን፣ ማስተላለፍንና መጠቀምን በሚመለከት ባልና ሚስት ተመሳሳይ መብቶች እንዲኖሯቸው የማድረግ፣

2. የህፃን ልጅ መታጨት ወይም ጋብቻ መፈፀም በሕግ ፊት የሚፀና ዉጤት የለዉም። አንድ ሰው ለጋብቻ የሚበቃበት አነስተኛ ዕድሜ መወሰን አለበት። ማንኛውም ጋብቻ ስልጣን ባለው አካል መመዝገብ እንዳለበት በሕግ መደንገግና ሌሎች እርምጃዎችን መዉሰድም ያስፈልጋል።

## ክፍል አምስት

## አንቀጽ 17

1. ይህን ስምምነት በማስፈፀም ረገድ የሚወሰዱ እርምጃዎችን እያየ የሚመረምር «በሴቶች ላይ የሚደረግ አድሏዊ ልዩነትን የሚያስወግድ ኮሚቴ» (ከዚህ በኋላ «ኮሚቴ» ተብሎ የሚጠቀስ)

ይቋቋማል፡፡ ስምምነቱ በሚፀናበት ጊዜ የኮሚቴው አባላት 18 ይሆናሉ፡፡ ስምምነቱን 35ኛው አገር ካፀደቀ ወይም ከተቀበለ በኋላ ግን የኮሚቴው አባላት 23 ከፍተኛ ስነ ምግባርና በስምምነቱ ውስጥ በተዘረዘሩት መስኮች ብቃት ያላቸው ባለሙያዎች ይሆናሉ፡፡ ባለሙያዎቹ ስምምነቱን ከተቀበሉት አገሮች ዜጎች መካከል ይመረጣሉ፤ የሚያገለግሉትም በግል ደረጃ ነው፡፡ አባላቱ በሚመረጡበትም ጊዜ ተመጣጣኝ ጂኦግራፊያዊ ስርጭት እንዳላቸውና የተለያዩትን የስልጣኔ ዓይነቶችና ዋና ዋና የሕግ ስርዓቶችን መወከላቸው በግንዛቤ ውስጥ ይገባል፡፡

2. የኮሚቴው አባላት ስምምነቱን ከተቀበሉት አገሮች ዕጩዎች መካከል በምስጢር የድምፅ አሰጣጥ ይመረጣሉ፡፡ እያንዳንዱ ስምምነቱን የተቀበለ አገር አንድ ዕጩ ከዜጎቹ መካከል መጠቆም ይችላል፡፡
3. የመጀመሪያው ምርጫ ስምምነቱ ከፀናበት ዕለት ስድስት ወራት በኋላ ይደረጋል፡፡ ከእያንዳንዱ ምርጫ ቢያንስ ሦስት ወራት ቀደም ብሎ የተባበሩት መንግስታት ዋና ጸሐፊ የሚመለከታቸው አገሮች ዕጩዎቻቸውን በሁለት ወራት ጊዜ ውስጥ እንዲጠቁሙ በደብዳቤ ይጠይቃቸዋል፡፡ ዋና

ጸሐፊው በዚህ አኳኋን የተጠቆሙትን ዕጩዎች ዝርዝር በፊደል ቅደም ተከተል አዘጋጅቶ የጠቆማቸውን አገር በመጥቀስ ስምምነቱን ለተቀበሉት አገሮች ያቀርባል፡፡

4. የኮሚቴው አባላት ምርጫ ዋና ጸሐፊው በተባበሩት መንግስታት ዋና ጽሕፈት ቤት ውስጥ በሚጠራው ስምምነቱን የተቀበሉ አገሮች ስብሰባ ላይ ይካሄዳል፡፡ ስምምነቱን ከተቀበሉት አገሮች ሁለት ሦስተኛው ከተገኙ ምልዐተ ጉባዔ ይኖራል፡፡ በዚሁ ስብሰባ የኮሚቴው አባላት የሚሆኑት በስብሰባው ተገኝተው ድምፅ ከሰጡት አገሮች መካከል የአብዛኞቹን ድምፅ በአብላጫነት ያገኙት ዕጩዎች ይሆናሉ፡፡

5. የኮሚቴው አባላት ለአራት ዓመታት የስራ ጊዜ ያገለግላሉ፡፡ ነገር ግን በመጀመሪያው ምርጫ ከተመረጡት መካከል የዘጠኙ አባላት የስራ ዘመን ለሁለት ዓመታት ብቻ ይሆናል፡፡ ከመጀመሪያው ምርጫ በኋላ ወዲያውኑ የነዚህ ዘጠኝ አባላት ማንነት በኮሚቴው ሊቀመንበር አማካይነት በዕጣ ይወሰናል፡፡

6. 35ኛው አገር ስምምነቱን ካፀደቀ ወይም ከተቀበለ በኋላ የአምስቱ ተጨማሪ የኮሚቴው አባላት ምርጫ

በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2፣ 3፣ እና 4 መሰረት ይካሄዳል። ከእነዚህ ተጨማሪ አባላት መካከል የሁለቱ የስራ ዘመን ለሁለት ዓመታት ብቻ ይሆናል። የሁለቱ አባላት ማንነት በኮሚቴው ሊቀመንበር አካማይነት በዕጣ ይወሰናል።

7. በኮሚቴው ውስጥ ክፍት የስራ ቦታ ሲፈጠር ስራውን ያቋረጠው አባል ዜጋ የሆነበት አገር ሌላ ባለሙያ ከዜጎቹ መሀከል መርጦ በማቅረብ ኮሚቴው አባልነቱን ተቀብሎ እንዲያፀድቀው ያደርጋል።
8. ጠቅላላ ጉባዔው ሲያፀድቅና ይኸው አካል የኮሚቴውን ኃላፊነት ክብደት ግምት ውስጥ በማስገባት በሚወስነው ደንብና ተመን መሰረት የኮሚቴው አባላት ለድካማቸው ከተባበሩት መንግስታት ጥሪት ወጭ የሚሆን አበል ይከፈላቸዋል።
9. ኮሚቴው በዚህ ስምምነት የተሰጠውን ኃላፊነት በትክክል እንዲፈፅም የተባበሩት መንግስታት ዋና ጸሐፊ አስፈላጊውን የሰው ኃይልና ድርጅት ያሚላለታል።

## አንቀጽ 18

1. ይህን ስምምነት የተቀበሉ አገሮች ስምምነቱን ለማስፈፀም ስለወሰዷቸው ሕግ የማውጣት፣ የዳኝነት አስተዳደራዊ ወይም ሌሎች እርምጃዎች የሚገልጽ ዘገባ በኮሚቴው እንዲታይ ለተባበሩት መንግስታት ዋና ጸሐፊ ያቀርባሉ። ይህን የሚያደርጉትም፣
   ሀ/ ለዚያ አገር ስምምነቱ በፀና በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ፤
   ለ/ ከዚያ በኋላ አነሰ ቢባል በየአራት ዓመታት አንዴ እንዲሁም ኮሚቴው በጠየቀበት ጊዜ ይሆናል።
2. የሚያቀርቡት ዘገባም በዚህ ስምምነት ውስጥ የተደነገጉትን ግዴታዎች በመፈጸም ረገድ ያጋጠሙትን ችግሮችና ሁኔታዎች ሊገልጽ ይችላል።

## አንቀጽ 19

1. ኮሚቴው የራሱን የስነ-ስርዓት ደንብ ይወስናል።
2. ኮሚቴው የስራ አስፈፃሚዎቹን ለሁለት ዓመታት የስራ ዘመን እንዲያገለግሉ ይመርጣል።

## አንቀጽ 20

1. በዚህ ስምምነት አንቀጽ 18 መሰረት የቀረቡለትን ዘገባዎች ለማየት ኮሚቴው በየዓመቱ ከሁለት ሳምንታት ሳልበለጠ ጊዜ ይሰበሰባል፡፡
2. የኮሚቴው ስብሰባዎች በተባበሩት መንግስታት ዋና ጽሕፈት ቤት ውስጥ ወይም ኮሚቴው በሚያመቸው ሌላ ቦታ ይደረጋሉ፡፡

## አንቀጽ 21

1. በኢኮኖሚና ማሕበራዊ ምክር ቤት አማካይነት ኮሚቴው ስለ እንቅስቃሴዎቹ የሚገልጽ ዘገባ በየዓመቱ ለተባበሩት መንግስታት ጠቅላላ ጉባዔ ያቀርባል፡፡ በዘገባውም ውስጥ ስምምነቱን ከተቀበሉት አገሮች የደረሱትን መረጃዎችና ዘገባዎች መርምሮ የራሱን አስተያየቶችና የእርምጃ ሀሳቦች ካሉት ማካተት ይችላል፡፡ እነዚህ የሚቀርቡት ግን ከእነዚያ አገሮች አስተያየቶች ጋር ተዳምረው ነው፡፡

2. የተባበሩት መንግስታት ዋና ጸሐፊ የኮሚቴውን ዘገባዎች የሴቶችን ሁኔታ ለሚከታተለው ኮሚሽን እንዲያውቀው ያስተላልፍለታል።

## አንቀጽ 22

ልዩ ተልእኮ የተሰጣቸው ድርጅቶች የዚህ ስምምነት ድንጋጌዎች አፈፃፀም በሚታይበት ጊዜ የነሱን ተግባራት የሚመለከቱ ጉዳዮች ሲኖሩ በወኪሎቻቸው አማካይነት በስብሰባዎቹ ውስጥ የመሳተፍ መብት አላቸው። ኮሚቴውም ከስምምነቱ አፈፃፀም አንፃር እነሱን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ዘገባ እንዲያቀርቡ ድርጅቶቹን ሊጋብዝ ይችላል።

# ክፍል ስድስት

## አንቀጽ 23

በሴቶችና በወንዶች መካከል እኩልነት እንዲሰፍን ይበልጥ አመቺ ሁኔታ የሚፈጥር

ሀ/ ስምምነቱን የተቀበለ አገር ሕግ፣ወይም

ለ/ በዚያ አገር ውስጥ የፀና ሌላ ዓለም አቀፍ ስምምነት ወይም ውል፣ በዚህ ስምምነት አይሻርም፡፡

## አንቀጽ 24

በዚህ ስምምነት ዕውቅና ያገኙትን መብቶች በሙሉ ለማስከበር ይህን ስምምነት የተቀበሉ አገሮች ሁሉ በብሔራዊ ደረጃ ማንኛውንም አስፈላጊ እርምጃ ለመውሰድ ተስማምተዋል፡፡

## አንቀጽ 25

1. ሁሉም አገሮች እንዲፈርሙበት ይህ ስምምነት ክፍት ነው፡፡

2. የተባበሩት መንግስታት ዋና ጸሐፊ ስምምነቱን እንዲረከብ ተመድቧል፡፡
3. ይህ ስምምነት በየአገሩ መፅደቅ ይኖርበታል፡፡ የማፅደቂያ ማረጋገጫዎች ለተባበሩት መንግስታት ዋና ጸሐፊ መቅረብ አለባቸው፡፡
4. ይህ ስምምነት በስራ ላይ ከዋለ በኋላም ቢሆን ማንኛውም አገር እንዲቀበለው ክፍት ነው፡፡ የስምምነቱ መቀበያ ሰነድ ለተባበሩት መንግስታት ጸሐፊ ሲቀርብ አባልነት ይፈፀማል፡፡

## አንቀጽ 26

1. ስምምነቱን የተቀበለ ማንኛውም አገር የተባበሩት መንግስታት ዋና ፀሐፊን ስምምነቱ እንዲሻሻል በማንኛውም ጊዜ በፅሁፍ መጠየቅ ይችላል፡፡
2. የዚህ ዓይነት ጥያቄ በሚቀርብበት ጊዜ ምን እርምጃ መወሰድ እንዳለበት ጠቅላላ ጉባዔው ይወሰናል፡፡

## አንቀጽ 27

1. 20ኛው የማፅደቂያ ወይም ስምምነቱን የመቀበያ ሰነድ ለተባበሩት መንግስታት ዋና ጸሐፊ ከቀረበበት

ዕለት በኋላ በ30ኛው ቀን ይህ ስምምነት የፀና ይሆናል፡፡

2. 20ኛው ማፅደቂያ ወይም መቀበያ ከቀረበ በኋላ ስምምነቱን ለሚያፀድቁ አገሮች የራሳቸውን ማፅደቂያ ወይም መቀበያ ካስረከቡበት ዕለት በኋላ በ30ኛው ቀን ስምምነቱን ለነሱም የፀና ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 28

1. በስምምነቱ ማጽደቂያ ወይም መቀበያ ሰነድ ላይ አባል አገሮች የሚያስመዘግቡትን ማንኛውንም ተአቅቦ ዋና ጸሐፊው በጽሑፍ ተቀብሎ ለሌሎቹ አገሮች ቅጂውን ያስተላልፋል፡፡
2. የዚህን ስምምነት ዓላማና ግብ የሚፃረር ተአቅቦ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡
3. ማናቸውንም ተአቅቦ ለተባበሩት መንግስታት ዋና ጸሐፊ በማስታወቅ ማንሳት ወይም ማስቀረት ይቻላል፡፡ ዋና ጸሐፊውም የተአቅቦውን መነሳት ለሌሎች ስምምነቱን ለተቀበሉ አገሮች ያስታውቃል፤ እንዲህ ዓይነቱ ተአቅቦ የማንሳት ማስታወቂያ ለዋና ጸሐፊው ከደረሰበት ዕለት ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 29

1. የስምምነቱ አተረጓጎም ወይም አፈጻጸም በሚመለከት ስምምነቱን በተቀበሉ ሁለትና ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ አገሮች መካከል የሚነሳ ማንኛውም ክርክር በድርድር ሊፈታ ካልቻለ በአንደኛው ጥያቄ ለግልግል ዳኝነት ሊቀርብ ይችላል። ጥያቄው በቀረበ በስድስት ወራት ውስጥ በግልግል ዳኝነቱ አዘገጃጀት ጉዳይ ላይ የሚመለከታቸው ተከራካሪዎች ካልተስማሙ አንዱ ጉዳዩን የዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት እንዲያይላቸው የፍ/ቤቱን የመተዳደሪያ ደንብን ተከትሎ ጥያቄ ሊያቀርብ ይችላል።
2. እያንዳንዱ አገር ስምምነቱን በሚፈርምበት፣ በሚያፀድቅበት፣ ወይም በሚቀበልበት ጊዜ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እንደማይገደድ መግለጽ ይችላል። እንዲህ ዓይነቱን ተዓቅቦ የገለጸ አገርን በሚመለከት ሌሎቹ ስምምነቱን የተቀበሉ አገሮችም የንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌን የማክበር ግዴታ የለባቸውም።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ተአቅቦውን ያስመዘገበ አባል አገር ለተባበሩት መንግስታት ዋና ጸሐፊ በማስታወቅ ተአቅቦውን በማናቸውም ጊዜ ማንሳት ይችላል።

## አንቀጽ 30

ይህ ስምምነት በአረብኛ፣ በቻይንኛ፣ በእንግሊዝኛ፣ በፈረንሳይኛ፣ በሩስይኛና በእስፓንኛ ቋንቋዎች የተዘጋጀ ሲሆን፣ ሁሉም ጽሑፎች እኩልና ትክክለኛ ናቸው። ይህ ስምምነት በተባበሩት መንግስታት ዋና ጸሐፊ ዘንድ ይቀመጣል።

ይህንን በማረጋገጥ ከታች ስማቸው የተመለከተው ስልጣኑ የተሰጣቸው ሰዎች እነሆ ፊርማቸውን በዚህ የቃልኪዳን ሰነድ ላይ አስፍረዋል።

# ማሰቃየትና ሌሎች ጭካኔ የተሞላባቸው፣ ኢ-ሰብአዊና አዋራጅ አያያዞችንና ቅጣቶችን ለማስቀረት የተደረገ ስምምነት

*በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ ቁጥር 39/46 አባል አገሮች እንዲፈርሙበት እና እንደያፀድቁት ክፍት የተደረገ።*
*ሰኔ 26 ቀን 1987 እ.ኤ.አ. በሥራ ላይ የዋለ።*

**ይህንን ስምምነት የተቀበሉ አገሮች፤**

በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ቻርተር በተደነገጉት መርሆዎች መሰረት የሰው ልጅ ሁሉ ሰብአዊ ክብር፣ እኩልነትና የማይገሰሱ መብቶች ያሉት መሆኑን አውቆ መቀበል በዓለም ላይ የነፃነት፣ ፍትሕና ሰላም መሰረቶች መሆናቸውን ግምት ውስጥ በማስገባት፤

እነዚህ መብቶች ከሰው ልጅ ተፈጥሮአዊ ክብር እንደሚመነጩ በመገንዘብ፤

በቻርተሩ በተለይም በአንቀጽ 55፤ መሰረት ሰብአዊ መብቶችና መሰረታዊ ነፃነቶች ዓለም አቀፍ

ተቀባይነትና ተፈፃሚነት እንዲያገኙ ጥረት ማድረግ የአገሮች ኃላፊነት መሆኑን በመገንዘብ፤

በሰብአዊ መብቶች ዓለም አቀፍ መግለጫ ዓንቀፅ 5 እና በሲቪልና ፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ስምምነት ዓንቀጽ 7 የሰፈረው፤ በማንኛውም ሰው ላይ የማሰቃየት ድርጊት ሊፈጸምበት እንደማይገባ፣ ወይም በጭካኔና ኢ-ሰብአዊ በሆነ መንገድ መጉላላት ወይም መዋረድ ወይም መቀጣት እንደሌለበት የሚደነግግ መርሆ ግምት ውስጥ በማስገባት፤

ዲሰምበር 9 ቀን 1975 እ.ኤ.አ በጠቅላላ ጉባኤ ማንኛውም ሰው ላይ የማሰቃየት ድርጊት እንዳይፈጸምበት፤ ጭካኔ የተሞላበት፣ ኢ-ሰብአዊና አዋራጅ አያያዝና ቅጣት እንዳይደርስበት ጥበቃ ማግኘት እንዳለበት በመወሰን ላወጣው መግለጫ ትኩረት በመስጠት፤

ማሰቃየትንና ሌሎች ጭካኔ የተሞላባቸውን ኢ-ሰብአዊና አዋራጅ አያያዞችንና ቅጣቶችን ለማስወገድ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚካሄደውን ትግል ለማጠናከር

ያላቸውን ዝግጁነት በመግለጽ፤ እንደሚከተለው ተስማምተዋል፡፡

## ክፍል አንድ

## አንቀጽ 1

1. በዚህ ስምምነት ውስጥ፤ «ማሰቃየት» ማለት ከራሱ ወይም ከሶስተኛ ወገን መረጃ ለማግኘት ወይም የእምነት ቃል እንዲሰጥ ወይም እንዲናዘዝ በማቀድ አንድ ሰው ላይ የሚካሄድ ከልክ ያለፈ አካላዊ ወይም አእምሮአዊ ስቃይና ጭንቅ፣ እንዲሁም ሰውየው ወይም ሌላ ሶስተኛ ወገን በፈፀመው ወይም ፈፅሞታል ተብሎ ለተጠረጠረበት ጉዳይ ለመቅጣት፣ ሰውየውን ወይም ሌላ ሶስተኛ ወገንን ለማስፈራራት ወይም በአድልዎ ላይ የተመሰረተ ማንኛውም ጭካኔ ለመፈፀም በመንግስት ባለስልጣን ወይም በሌላ የመንግስት ሥልጣን ይዞ በሚሰራ ሰው ወይም በእርሱ አነሳሽነት፣ ስምምነት ወይም አውቆ ሳለ ባለመቃወም የሚፈፀም የማሰቃየት ተግባር ነው፡፡ ይህም ከሕጋዊ ቅጣቶች የሚመነጭ ወይም ከዚሁ

ጋር መሰረታዊ ቁርኝት ያለውን ስቃይ አይጨምርም፡፡

2. ይህ ዓንቀፅ ከዚህ የሰፋ አተገባበር ላላቸው ዓለም አቀፋዊና አገራዊ ሕጎች በሚቃረን መልኩ አይፈፀምም፡፡

## አንቀጽ 2

1. ይህንን ስምምነት የተቀበለ እያንዳንዱ አገር በማንኛውም የግዛቱ ክልል የማሰቃየት ተግባር እንዳይፈፀም ለመከላከል የሚያስችል ውጤታማ ሕግ ያወጣል፣ የአስተዳደር፣ የፍርድ ስርዓት እና ሌሎች እርምጃዎችን ይወስዳል፡፡
2. ማንኛውም ልዩ ሁኔታ፣ ጦርነት ወይም የጦርነት ስጋት፣ የውስጥ ፖለቲካዊ አለመረጋጋት፣ ወይም ሌላ የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ለማሰቃየት ተግባር ሕጋዊ መከላከያ ሊሆን አይችልም፡፡

3. ከበላይ አካል ወይም ከመንግስት ባለስልጣን የሚተላለፍ ትእዛዝ ለማሰቃየት ተግባር ሕጋዊ መከላከያ ሊሆን አይችልም።

## አንቀጽ 3

1. ለማሰቃየት ተግባር ይጳረጋል የሚል እምነት ለማሳደር አሳማኝ ሁኔታ ካለ ማንኛውም ይህንን ስምምነት የተቀበለ አገር በግዛቱ የሚገኝን ሰው ከግዛቱ አያስወጣም፣ ወደመጣበት አገር አይመልሰውም፣ አሳልፎም አይሰጠውም።

2. የማሰቃየት ድርጊት ሊደርስ የሚችል መሆን አለመሆንን ለመወሰን የሚመለከታቸው ባለስልጣናት በአገሪቱ ያለውን አጠቃላይ ሁኔታ በተለይም አግባብነት ሲኖረው በአገሪቱ ውስጥ ያለውን ከፍተኛ የጅምላ እና ተደጋጋሚ የሰብአዊ መብቶች ጥሰት ግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው።

## አንቀጽ 4

1. ስምምነቱን የተቀበለ እያንዳንዱ አገር የማሰቃየት ተግባር ወንጀል መሆኑን በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ማስፈር አለበት፡፡ በተመሳሳይ የማሰቃየት ተግባር ለመፈፀም የሚደረግ ሙከራና በማሰቃየት ተግባር ላይ መተባበርና ተሳታፊ መሆን ወንጀል መሆኑን መደንገግ አለበት፡፡

2. ይህንን ስምምነት የተቀበለ እያንዳንዱ አገር እነዚህ ወንጀሎች ክብደታቸውን ግምት ውስጥ ባስገባ አግባብ ያለው ቅጣት እንደሚያስቀጡ ማድረግ አለበት፤

## አንቀጽ 5

1. ስምምነቱን የተቀበለ እያንዳንዱ አገር በአንቀጽ 4 የተጠቀሱ ወንጀሎችን በሚመለከት በሚከተሉት ሁኔታዎች እርምጃ ለመውሰድ ሥልጣን እንዲኖረው የሚያስፈልጉትን እርምጃዎች ይወስዳል፡፡

ሀ/ ወንጀሉ በየትኛውም የግዛት ክልሉ ውስጥ ወይም በአገሩ በተመዘገበ መርከብ ወይም አይሮፕላን ላይ ከተፈፀመ፣

ለ/ በወንጀሉ የተጠረጠረ ሰው የአገሩ ዜግነት ያለው ከሆነ፣

ሐ/ አገሩ አግባብነት አለው ብሎ ካመነበት የወንጀሉ ሰለባ የሆነው የራሱ ዜጋ ሲሆን፡፡

2. ቃል-ኪዳኑን የተቀበለ እያንዳንዱ አገር ፣ በወንጀሉ የተጠረጠረው ሰው በማንኛውም የአገሩ ግዛት ክልል ውስጥ የሚገኝ ከሆነና በዓንቀጽ 8 መሠረት በዚህ አንቀጽ ንኡስ ዓንቀጽ 1 ለተጠቀሰው አገር አሳልፎ ካልሰጠ በተመሳሳይ በጉዳዩ ላይ የመወሰን ስልጣን እንዲኖረው የሚያስፈልገውን እርምጃ ይወስዳል፡፡

3. ይህ ስምምነት በአንድ አገር የውስጥ ሕግ መሰረት የወንጀል ድርጊት ላይ የሚኖረውን ስልጣን የሚያስቀር አይደለም፡፡

## አንቀጽ 6

1. ስምምነቱን የተቀበለ አገር እጁ ውስጥ የገባን መረጃ ከመረመረ በኋላ ተገቢ መሆኑን ሲያምንበት በግዛቱ ክልል ውስጥ የሚገኝ እና በአንቀጽ 4 የተጠቀሰውን ወንጀል ፈፅሟል ተብሎ የተጠረጠረውን ሰው በቁጥጥር ስር ማዋል ወይም እንዳያመልጥ ሌላ ሕጋዊ እርምጃ መውሰድ አለበት፡፡ በቁጥጥር ስር ማዋሉና ሌላው ሕጋዊ እርምጃ ሰውየው በተገኙበት አገር ሕግ መሰረት የሚፈፀም ሲሆን፣ ይህም የወንጀል ክስ እስኪመሠረትበት ወይም ለሌላ አገር ተላልፎ እስከሚሰጥበት ጊዜ ብቻ ሊቆይ ይችላል፡፡

2. እርምጃውን የወሰደው አገር ወዲያውኑ እውነታውን ለማጣራት የመጀመርያ ደረጃ ምርመራ ያካሂዳል፡፡
3. በዚሁ አንቀፅ ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት በቁጥጥር ስር የዋለ ሰው ወዲያው ባቅራቢያው ከሚገኘው ዜጋ የሆነበት አገር አግባብ ያለው ተወካይ እንዲገናኝ ድጋፍ ይሰጠዋል፡፡ ሰውየው አገር አልባ ከሆነ ደግሞ

አዘውትሮ ከሚኖርበት አገር ተወካይ ጋር እንዲገናኝ ድጋፍ ይደረግለታል፡፡

4. በዚሁ አንቀጽ መሰረት ተጠርጣሪውን በቁጥጥር ስር ያዋለ አገር ሰውየው መያዙንና በቁጥጥር ስር የዋለበትን ምክንያት በአንቀጽ 5 ንኡስ አንቀጽ 1 ለተጠቀሰው አገር ወዲያው ያሳውቃል፡፡ በዚሁ አንቀፅ ንኡስ አንቀጽ 2 የተመለከተውን የመጀመርያ ደረጃ ማጣራት ያካሄደ አገር የደረሰበትን ድምዳሜ እና በራሱ ፍርድ ቤት ለፍርድ ለማቅረብ ያቀደ መሆን አለመሆን ለእነዚሁ አገሮች በአፋጣኝ መግለጽ ይኖርበታል፡፡

## አንቀጽ 7

1. ስምምነቱን የተቀበለ አገር በአንቀጽ 4 የተጠቀሱትን ወንጀሎች ፈጽሟል ተብሎ የተጠረጠረ ሰው በግዛት ክልሉ ሲገኝ ለሌላ አገር አሳልፎ የማይሰጠው ከሆነ በአንቀጽ 5 በተመለከቱት ሁኔታዎች ለፍርድ ለማቅረብ እንዲቻል ጉዳዩን ሥልጣን ላላቸው አካላት እንዲቀርብ ያደርጋል፡፡

2. ባለስልጣናቱም አደገኛ ባህሪ ያለው ሌላ ተራ ወንጀል በሚስተናገድበት የአገሪቱ ሕግ መሰረት ውሳኔ ይሰጡበታል። በአንቀጽ 5 ንኡስ አንቀጽ 2 በተጠቀሱ ጉዳዮች ክስ ለማቅረብና የጥፋተኝነት ፍርድ ለመስጠት የሚያገለግሉ የማስረጃ መመዘኛዎች በአንቀጽ 5 ንኡስ አንቀጽ 1 ለሰፈሩት ጉዳዮች ከሚያገለግሉ መመዘኛዎች በታች መሆን የለባቸውም።

3. በአንቀጽ 4 ከተጠቀሱ የወንጀል ድርጊቶች ጋር በተያያዘ ክስ የተመሰረተበት ሰው፣ በሁሉም የክሱ ሂደት ደረጃዎች ፍትሃዊ የሆነ አያያዝ ሊደረግለት ይገባል።

## አንቀጽ 8

1. በአንቀጽ 4 የተጠቀሱት ወንጀሎች በዚህ ስምምነት ፈራሚ አገሮች መሃል ፀንተው በሚገኙ ተጠርጣሪን አሳልፎ የመስጠት ስምምነቶች "አሳልፎ ለመስጠት የሚያበቁ የወንጀል ድርጊቶች" ተብለው ይቆጠራሉ።

ስምምነቱን የተቀበሉ አገሮች ተጠርጣሪን አሳልፎ የመስጠት ስምምነት በሚያደርጉበት ወቅት እነዚህን ወንጀሎች በስምምነታቸው ውስጥ ማካተት አለባቸው፡፡

2. በወንጀል የተጠረጠረን ሰው አሳልፎ ለመስጠት የስምምነት መኖርን እንደ ቅድመ ሁኔታ ለሚመለከት ይህን ስምምነት የተቀበለ አገር፣ በወንጀል የተጠረጠረን ሰው አሳልፎ እንዲሰጥ ስምምነት ካላደረገ አገር በወንጀል የተጠረጠረን ሰው አሳልፎ የመስጠት ጥያቄ ሲቀርብለት ይህንን ስምምነትእንደ ሕጋዊ መሰረት በመውሰድ በወንጀል የተጠረጠረውን ሰው አሳልፎ መስጠት ይችላል፡፡ ጥያቄው በቀረበለት አገር ሰዎችን አሳልፎ ስለመስጠት የተደነገጉት ሌሎች ሁኔታዎች ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡

3. በወንጀል የተጠረጠረን ሰው አሳልፎ ለመስጠት ይህንን የተመለከተ ስምምነት መኖርን እንደ ቅድመ ሁኔታ የማያዩ ይህንን ስምምነት የተቀበሉ አገሮች አሳልፎ እንዲሰጥ የተጠየቀው አገር ሕግ የሚደነግገው እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ ወንጀል

በአገሮቹ መሀል አሳልፎ የሚያሰጥ መሆኑን አውቀው ይቀበላሉ።

4. ይህን ስምምነት በተቀበሉ አገሮች መካከል የወንጀሉን ፈፃሚዎች አሳልፎ መስጠት ለማስፈፀም ሲባል ይህ ወንጀል በርግጥ በተፈፀመበት ቦታ ብቻ ሳይሆን በአንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 1 በተደነገገው መሰረት የዳኝነት ሥልጣናቸውን ለማረጋገጥ በሚፈልጉ አገሮች የግዛት ክልል እንደተፈፀመ ሆኖ ይቆጠራል።

## አንቀጽ 9

1. ስምምነቱን የተቀበሉ አገሮች በአንቀጽ 4 የተጠቀሱትን ወንጀሎች ፈጽመዋል ተብለው የተጠረጠሩትን ሰዎች ለፍርድ በማቅረብ ሂደት በእጃቸው የሚገኝን ማስረጃ መስጠት ጨምሮ ያልተቆጠበ ትብብር ያደርጋሉ።
2. ስምምነቱን የተቀበሉ አገሮች በፍትህ አስተዳደር ረገድ ለመተባበር ያደረጉት ስምምነት ካለ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 የተጠቀሱትን

ግዴታዎች ከዛ ጋር በሚጣጣም መልክ ይወጣሉ፡፡

## አንቀጽ 10

1. ስምምነቱን የተቀበሉ አገሮች በቁጥጥር ስር የዋሉትን ሰዎች በማሰር፣ በመመርመርና በመያዝ የተሰማሩ የሕግ አስፈፃሚዎች፣ ሲቪሎች ወይም ወታደሮች፣ የጤና ባለሙያዎች፣ የመንግስት ባለስልጣናት ወይም ሌሎች ሰዎችን በሚያሰለጥኑበት ጊዜ ማሰቃየት የተከለከለ መሆኑን የሚያስረዳ መረጃ እና ትምህርት በስልጠናው የተካተተ መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸዉ፡፡
2. ስምምነቱን የተቀበሉ አገሮች በዚሁ የስራ መስክ ለሚያሰማርዋቸው ሰራተኞች በሚያዘጋጁት ግዴታና ተግባር የሚገልፅ መመሪያ ማሰቃየት የተከለከለ መሆኑን ማስፈር አለባቸው፡፡

## አንቀፅ 11

እያንዳንዱ ስምምነቱን የተቀበለ አገር በየትኛውም የግዛት ክልሉ በማንኛውም ሁኔታ ተይዘው

ወይም ታስረው የሚገኙ ግለሰቦች ቃል ለመቀበል የወጡ ደንቦችን፣ ለሚደረግላቸው ጥበቃ እና አያያዝ የሚያገለግሉ መመሪያዎችን፣ ስልቶችን፣ ልምዶችንና ዝግጅቶችን የማሰቃየት ድርጊትን ከማስወገድ አኳያ በየጊዜው መመርመርና ማሻሻል ይኖርበታል።

## አንቀጽ 12

እያንዳንዱ ስምምነቱን የተቀበለ አገር በየትኛውም የግዛት ክልሉ ውስጥ ማሰቃየት ተካሂዷል ብሎ ለማመን የሚያስችል ምክንያት ሲፈጠር አግባብ ያላቸው ባለስልጣናቱ አፋጣኝና ገለልተኛ ማጣራት ማካሄድ መቻላቸውን ማረጋገጥ አለበት።

## አንቀጽ 13

እያንዳንዱ ስምምነቱንየተቀበለ አገር በየትኛውም የግዛት ክልሉ ውስጥ የማሰቃየት ተግባር ተፈጽሞብኛል የሚል ግለሰብ ቅሬታውን ተገቢው ስልጣን ላላቸው ባለስልጣናት አቅርቦ አፋጣኝና

ከአድልዎ ነፃ የሆነ ማጣራት እንደሚካሄድለት ማረጋገጥ አለበት። ቅሬታ አቅራቢው ወይም ምስክሮች ከሚያቀርቡት መረጃ በተያያዘ ማንገላታትና ማስፈራራት እንዳይደርስባቸው ተገቢ እርምጃዎች ይወሰዳሉ።

## አንቀጽ 14

1. እያንዳንዱ ስምምነቱን የተቀበለ አገር የማሰቃየት ተግባር ሰለባ ለሆነ ሰው ድርጊቱ እንዲወገድለት ማድረግና፣ ፍትሐዊና በቂ ካሳ አግኝቶ በተቻለ መጠን ከጉዳቱ ሙሉ በሙሉ የሚያገግምበት ሁኔታ የሚፈጥር ሕጋዊ ስርዓት መዘርጋት አለበት። የወንጀሉ ሰለባ የሆነ ሰው በደረሰበት ማሰቃየት ምክንያት ከሞተ በርሱ ኃላፊነትና ዕርዳታ ይተዳደሩ የነበሩ ሰዎች ካሳ ማግኘት አለባቸው።
2. ይህ አንቀጽ የማሰቃየት ተግባር ሰለባ የሆነው ሰውም ሆነ የሌሎች ግለሰቦች በአገራዊ ሕግ መሰረት ካሳ የማግኘት መብት አይነካም።

## አንቀጽ 15

እያንዳንዱ ስምምነቱን የተቀበለ አገር በማሰቃየት የተገኘ ለመሆኑ የተረጋገጠ ቃል በማንኛውም የፍርድ ሂደት እንደማስረጃ እንደማይቀርብ ማረጋገጥ አለበት። ይሁን እንጂ ይህ ቃል የማሰቃየት ተግባር በመፈፀሙ በተከሰሰው ሰው ላይ ቃሉ ስለመስጠቱ እንደ ማስረጃ ሊቀርብበት ይችላል።

## አንቀጽ 16

1. እያንዳንዱ ስምምነቱን የተቀበለ አገር በአንቀጽ 1 የተመለከተውን የማሰቃየት ትርጓሜ የማያሟሉ ሌሎች ጭካኔ የተሞላባቸው ኢሰብአዊ፣ አዋራጅ ድርጊቶች በመንግስት ባለስልጣናት ወይም በሌላ ስልጣን በተሰጠው ግለሰብ፣ ወይም በርሱ አነሳሽነት፣ ወይም አውቆ ባለመቃወም እንዳይፈፀሙ ለመከላከል ግዴታ ገብቷል። በተለይም በዚሁ ስምምነት አንቀጽ 10፣ 11፣ 12 እና 13 የተጠቀሱት ግዴታዎች በማሰቃየት ተግባር ምትክ ሌሎች

የጭካኔ ዓይነቶች፣ ኢ-ሰብአዊና አዋራጅ አያያዝ ወይም ቅጣት የሚል ገብቶ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

2. የዚህ ስምምነት ድንጋጌዎች ጭካኔ የተሞላባቸው፣ ኢ-ሰብአዊ ወይም አዋራጅ አያያዞችን ወይም ቅጣት ለመከልከል ከወጡት ወይም አሳልፎ ከመስጠትና ከአገር ማስወጣት ጋር የተያያዙ ሌሎች ዓለም አቀፍ ሰነዶች ወይም አገራዊ ሕጎች  አይቃረኑም፡፡

## ክፍል ሁለት

## አንቀጽ 17

1. ማሰቃየትን ለማስወገድ የሚሰራ ካሁን በኋላ ኮሚቴው  ተብሎ የሚጠቀስ ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ተግባራት የሚያከናውን ኮሚቴ ይቋቋማል፡፡  ኮሚቴው ከፍተኛ ስነ-ምግባርና በሰብአዊ መብቶች መስክ ልዩ ብቃት ያላቸው፣ ራሳቸውን በመወከል የሚሰሩ 10 ባለሙያዎች በአባልነት የሚይዝ ይሆናል፡፡ ባለሙያዎቹ ስምምነቱን በተቀበሉ አገሮች የሚመረጡ ሲሆን፤

ምርጫውም የኮሚቴው አባሎች ስብጥርንና የሕግ ልምድን ግምት ውስጥ ያስገባ ይሆናል፡፡

2. የኮሚቴው አባሎች ስምምነቱን በተቀበሉ አገሮች ከቀረቡ ዕጩዎች መካከል በምስጢር ድምጽ አሰጣጥ ይመረጣሉ፡፡ እያንዳንዱ ስምምነቱን የተቀበለ አገር ከዜጎቹ መካከል ለምርጫው አንድ ዕጩ ማቅረብ ይችላል፡፡ በዓለም አቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ቃል-ኪዳን መሰረት በቆመው የሰብአዊ መብቶች ኮሚቴ አባላት የሆኑ ሰዎች ፈቃደኛ ሆነው እስከተገኙ ድረስ ማሰቃየትን ለማስወገድ በሚቋቋመው ኮሚቴ ውስጥ ገብተው ቢሰሩ ያለውን ጠቀሜታ፣ ስምምነቱን የተቀበሉ አገሮች በምርጫ ወቅት ግምት ውስጥ ያስገባሉ፡፡

3. የኮሚቴው አባላት ምርጫ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ በየሁለት ዓመቱ አንድ ጊዜ በሚጠራው የስምምነቱ አባል አገሮች ስብሰባ ላይ ይካሄዳል፡፡ በዚህ ስብሰባ ከአባል አገሮች ሁለት ሶስተኛ ከተገኙ ምልአተ ጉባኤ ይሆናል፡፡ የኮሚቴው አባሎች ሆነው የሚመረጡት ከፍተኛውን ድምፅ

የሚያገኙትና በስብሰባው ላይ ተገኝተው ድምጽ ከሰጡት የስምምነቱ አባል አገሮች ተወካዮች ከግማሽ በላይ የደገፋአቸው ይሆናሉ።

4. የመጀመርያው ምርጫ ስምምነቱ አስገዳጅ ከሆነበት ቀን ጀምሮ ከስድስት ወራት ባልበለጠ ጊዜ ይካሄዳል። የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ ከእያንዳንዱ ምርጫ ቢያንስ ከአራት ወራት በፊት ስምምነቱን ለተቀበሉ አገሮች በሚፅፈው ደብዳቤ በሶስት ወራት ውስጥ ለዕጩነት የመረጡት ሰው ስም እንዲልኩ ይጠይቃል። ዋና ፀሐፊው በበኩሉ በዕጩነት የቀረቡትን ግለሰቦች ስም በፊደል ቅደም ተከተል በማዘጋጀት ከጠቆሙአቸው አገሮች ስም ጋር የስምምነቱ ፈራሚ ለሆኑት አገሮች ያቀርባል።

5. የኮሚቴው አባሎች ለአራት ዓመታት የስራ ጊዜ ይመረጣሉ። እንደገና በዕጩነት ከቀረቡ ሊመረጡ ይችላሉ። ይሁን እንጂ በመጀመርያ ምርጫ ከተመረጡት የኮሚቴው አባላት የአምስቱ የስራ ዘመን ለሁለት ዓመታት ብቻ ይሆናል። የእነዚህ

የአምስቱ ሰዎች ስም የመጀመሪያው ምርጫ እንደተከናወነ በንኡስ አንቀጽ 3 በተጠቀሰው የስብሰባው ሊቀመንበር በሚወጣው ዕጣ ይለያል።

6. የኮሚቴው አባል በሞት ወይም በራሱ ፈቃድ ስራ ቢለቅ ወይም በማንኛውም ሌላ ምክንያት የኮሚቴውን ስራ መስራት ሳይችል ቢቀር በዕጩነት ያቀረበው የስምምነቱ አባል አገር፤ ከዜጎቹ መካከል ለቀሪው ጊዜ የሚያገለግል ሌላ ሰው ይመድባል። ሆኖም ምደባው የሚፀናው የስምምነቱ አባል ከሆኑት አገሮች መካከል አብዛኞቹ ከደገፉት ነው። ስምምነቱን ከተቀበሉት አገሮች መካከል ግማሽ ወይም ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ምትክ ምደባው በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ ከተገለፀላቸው በኋላ በስድስት ሳምንታት ውስጥ የተቃውሞ መልስ ካልላኩ ተተኪው ሰው ድጋፍ እንዳገኘ ይቆጠራል።

7. የኮሚቴው አባላት የኮሚቴ ስራቸውን ለማከናወን የሚያስፈልጋቸውን ወጪ ስምምነቱን የተቀበሉ አገሮች ይሸፍናሉ።

## አንቀጽ 18

1. ኮሚቴው ለሁለት ዓመታት የስራ ጊዜ የሚያገለግሉ ስራ አስፈፃሚዎች ይመርጣል፡፡ ስራ አስፈፃሚዎቹ ዳግመኛ መመረጥ ይችላሉ፡፡
2. ኮሚቴው የራሱ የስነ-ስርዓት ደንብ ይቀርፃል፡፡ ቢሆንም የሚቀረፀው ደንብ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፤

   ሀ/ ስድስት አባላት ከተገኙ ምልአተ ጉባኤ እንደሚሆን፤

   ለ/ የኮሚቴው ውሳኔዎች በስብሰባው ከተገኙ አባላት መካከል በአብዛኛዎቹ የተደገፉ መሆን እንዳለባቸው፣
3. የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ ኮሚቴው በዚህ ቃል ኪዳን መሠረት ተግባሩን በሚገባ ለማከናወን የሚያስችለውን የሰው ኃይልና አስፈላጊ ነገሮች ያሟላል፡፡
4. የኮሚቴው የመጀመርያ ስብሰባ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ ይጠራል፡፡ ከመጀመርያው ስብሰባ በኋላ ኮሚቴው በአሰራር ስነ-ስርዓት ደንቡ መሰረት በተወሰነው ጊዜ ይሰበሰባል፡፡

5. ስምምነቱን የተቀበሉ አገሮች፣ ከኮሚቴውና ከአባል አገሮች ስብሰባዎች ጋር በተያያዘ የሚወጣውን ወጪ ይሸፍናሉ። በተጨማሪም የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ለኮሚቴው የሰው ኃይልና አስፈላጊ ነገሮች ለሚሟለት በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 3 መሰረት ቀደም ሲል ያወጣው ወጪ አባል አገሮች ይተካሉ።

## አንቀጽ 19

1. ስምምነቱን የተቀበሉ አገሮች ስምምነቱ በሥራ ላይ ከዋለ በኃላ ባለው የአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ አገሮች፤ ቃል-ኪዳኑን ተግባር ላይ ለማዋል ስላከናወኗቸው ተግባራት የሚመለከት ዘገባ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ በኩል ለኮሚቴው ያቀርባሉ። ከዚያ በኋላ ደግሞ የስምምነቱን አፈፃፀም አስመልክተው ስለወሰዱዋቸው አዳዲስ እርምጃዎችና እንደነገሩ ሁኔታ ኮሚቴው በሚያቀርብላቸው ጥያቄዎች ላይ ተጨማሪ ዘገባዎችን በየአራት ዓመቱ ያቀርባሉ።

2. ዋና ፀሐፊውም እነዚህን ዘገባዎች ለሁሉም የስምምነቱ አባል አገሮች ያሰራጫል፡፡

3. እያንዳንዱ ዘገባ በኮሚቴው የሚታይ ሲሆን፣ ኮሚቴው በዘገባው ላይ አጠቃላይ አስተያየት ካለው ለሚመለከተው የስምምነቱ አባል አገር ይልካል፡፡ ስምምነቱን የተቀበለው አገርም በኮሚቴው ግምገማ ላይ ያለውን አስተያየት ለኮሚቴው ማስተላለፍ ይችላል፡፡

4. ኮሚቴው በዚሁ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 3 መሰረት የሚሰጠውን አስተያየት፣ እንዲሁም በአባል አገር የተላከለትን የመልስ አስተያየት አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው በስምምነቱ አንቀጽ 24 መሰረት በሚያዘጋጀው ዓመታዊ ዘገባ ውስጥ ሊያካትት ይችላል፡፡ በሚመለከተው ፈራሚ አገር ጥያቄ ከቀረበለትም በዚሁ አንቀጽ በንኡስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰውን ዘገባ ቅጂ ጨምሮ ያዘጋጃል፡፡

## አንቀጽ 20

1. ኮሚቴው የስምምነቱ ፈራሚ በሆነ የአንድ አገር ግዛት ውስጥ በተደጋጋሚና በተቀነባበረ ሁኔታ ማሰቃየት እየተፈፀመ መሆኑን የሚያመለክት አስተማማኝ መረጃ ከደረሰው ፈራሚው አገር መረጃውን በማጣራት ሂደት እንዲተባበርና የቀረቡትን መረጃዎች በሚመለከት ያለውን አስተያየት እንዲሰጥ ጥሪ ያቀርባል።
2. ኮሚቴው ስምምነቱን ከተቀበለ የሚመለከተው አገር በቀረበለት አስተየየትና በእጁ የገባ አግባብ ያለው መረጃ በመነሳት፤ ጉዳዩ መጣራት እንዳለበት ካመነ ከአባላቱ መካከል አንድ ወይም ከአንድ በላይ በመመደብ በሚስጥር የተያዘ ማጣራት እንዲደረግና ዘገባው ባስቸኳይ ለኮሚቴው እንዲቀርብ መመሪያ መስጠት ይችላል።
3. በዚሁ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 መሰረት ማጣራት የሚካሄድ ከሆነ ኮሚቴው የሚመለከተውን አገር ትብብር ይጠይቃል። ስምምነቱን ከተቀበለው አገር ጋር በሚካሄድ ስምምነት መሰረት የማጣራት ስራው

በአገሩ ግዛት ውስጥ ጉብኝት ማካሄድን ሊጨምር ይችላል፡፡

4. ኮሚቴው በንኡስ አንቀጽ 2 መሰረት በኮሚቴው አባል ወይም አባሎች የቀረበለትን ድምዳሜ ከመረመረ በኋላ ድምዳሜውን ተገቢ የመሰለውን አስተያየት በማከል ለሚመለከተው ፈራሚ አገር ይልካል፡፡

5. ከንኡስ አንቀጽ 1 እስከ 4 የተዘረዘሩት ሁሉም የኮሚቴው ስራዎች በምስጢር መያዝ አለባቸው፡፡ በሁሉም የስራው ደረጃዎች የስምምነቱ ፈራሚ አገር ትብብር መጠየቅ አለበት፡፡ በንኡስ አንቀጽ 2 መሰረት የሚካሄደው ምርመራና ማጣራት ከተጠናቀቀ በኂላ ከሚመለከተው ፈራሚ አገር ጋር በመመካከር የማጣራቱ ውጤት ባጭሩ በአንቀጽ 24 በተደነገገው መሠረት በሚቀርበው የዓመቱ ዘገባ እንዲካተት ኮሚቴው መወሰን ይችላል፡፡

## አንቀጽ 21

1. ቃል-ኪዳኑን የተቀበለ አገር በዚሁ ዓንቀጽ መሰረት፣ አንድ የቃል-ኪዳኑ ፈራሚ አገር በቃል-ኪዳኑ

የሰፈሩትን ግዴታዎች አልተወጣም ብሎ ለኮሚቴው መረጃ እንዲሰጥ ኮሚቴውም ይህን ለመመርመር የሚያስችል ስልጣን እንዳለው በማንኛውም ጊዜ እውቅና መስጠት ይችላል፡፡ ኮሚቴው በዚህ አንቀጽ በሰፈረው ስነ-ስርዓት መሰረት ኮሚቴው እንዲህ ዓይነቱን መረጃ የሚቀበለውና የሚያጣራው መረጃው ለኮሚቴው ስልጣን ዕውቅና ከሰጠ አገር ሲቀርብለት ብቻ ነው፡፡ እንዲህ ዓይነቱን እውቅና ስላልሰጠ አገር የሚቀርብ መረጃ አይጣራም፡፡ በዚሁ አንቀጽ መሰረት የሚቀርብ መረጃ በሚከተለው አግባብ ይስተናገዳል፡፡

ሀ/ ስምምነቱን የተቀበለ አገር ሌላ ስምምነቱን የተቀበለ አገር የስምምነቱን ድንጋጌዎች ተግባራዊ አላደረገም ብሎ ካመነ ለዚሁ አገር በጽሁፍ ያሳውቃል፡፡ ማሳሰቢያው የደረሰው አገርም ጉዳዩን የሚያብራራ ወይም የሚገልጽ ጽሑፍ ማሳሰቢያ ለላከለት አገር በሶስት ወራት ውስጥ መላክ አለበት፡፡ የሚላከው ጽሑፍ በተቻለ መጠን የአገር ውስጥ ስነ-ስርዓትና የተወሰደው

ወይም ለመውሰድ በሂደት ላይ የሚገኘው የእርምት እርምጃን ማካተት አለበት፡፡

ለ/ የመጀመሪያውን ግንኙነት ካደረጉበት ጊዜ ጀምሮ በስድስት ወራት ውስጥ ሁለቱን የሚመለከታቸው አገሮች በሚያስማማ መልኩ ጉዳዩ መፍትሔ ካላገኘ ከሁለቱ አገሮች አንዱ ለኮሚቴው እና ለሌላኛው አገር መንግስት በተፃፈ ማስተዋሻ ጉዳዩን ለኮሚቴው የማቅረብ መብት አለው፡፡

ሐ/ ኮሚቴው በዚሁ አንቀጽ መሰረት የቀረበለትን ጉዳይ የሚያጣራው ተቀባይነት ባላቸው የዓለም አቀፍ ሕግ መርሆዎች መሰረት ሁሉም የአገር ውስጥ የእርምት እርምጃዎች ጥቅም ላይ መዋላቸውን ካረጋገጠ በኋላ ነው፡፡ የእርምት እርምጃዎቹ አፈፃፀም አላግባብ የተራዘመ ከሆነና የዚህ ስምምነት ድንጋጌ በመጣሱ ምክንያት ለተጎዳው ሰው ተጨባጭ ውጤት የማይፈጥሩ ከሆነ ይህ ድንጋጌ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

መ/ ኮሚቴው በዚሁ አንቀጽ መሰረት፣ የቀረቡለትን መረጃዎች የሚያጣራው በዝግ ስብሰባ ነው::

ሠ/ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (ሐ) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚቴው የሚመለከታቸው ስምምነቱን የተቀበሉ አገሮች፣ ስምምነቱ ያሰፈራቸው ግዴታዎችን መሰረት በማድረግ ጉዳዩን በውይይት እንዲፈቱ አስፈላጊውን ትብብር ያደርግላቸዋል:: ኮሚቴው ለጉዳዩ መፍትሄ ለመስጠት ይረዳል ብሎ ካመነ ጊዜያዊ አስታራቂ ኮሚሽን ማቋቋም ይችላል::

ረ/ ኮሚቴው በዚህ አንቀጽ በተደነገገው መሠረት በሚቀርብለት ማንኛውም ጉዳይ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (ለ) የተጠቀሱት ጉዳዩ የሚመለከታቸው የስምምነቱ ፈራሚ አገሮች አስፈላጊ መረጃ እንዲያቀርቡ ጥሪ ማቅረብ ይችላል::

ሰ/ ኮሚቴው ጉዳዩን በሚያጣራበት ወቅት በዚሁ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (ለ) የተጠቀሱት ጉዳዩ የሚመለከታቸው አገሮች በተወካዮቻቸው በኩል የመገኘትና በቃልና ወይም በጽሑፍ ማብራሪያ የማቅረብ መብት አላቸው፡፡

ሸ/ ኮሚቴው በዚሁ ንኡስ አንቀጽ ክፍል (ለ) መሰረት ደብዳቤ ከደረሰው በኋላ በአስራ ሁለት ወራት ውስጥ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

1. በንኡስ አንቀጽ ክፍል (ሠ) መሰረት ጉዳዩ ዕልባት ካገኘ ኮሚቴው የሚያቀርበው ዘገባ በአጭሩ ፍሬ ነገሩንና የተደረሰበትን እልባት የሚያመለክት ይሆናል፡፡
2. በንኡስ አንቀጽ ክፍል (ሠ) መሰረት ጉዳዩ ዕልባት ካላገኘ ኮሚቴው የሚያቀርበው አጭር ዘገባ ፍሬ ነገሩንና ጉዳዩ በሚመለከታቸው የስምምነቱ አባል አገሮች የቀረበለትን የፅሑፍ መግለጫ ከቃል ክርክር ሪከርድ ጋር ተያይዞ መሆን አለበት፡፡

በሁሉም ጉዳዮች ላይ ዘገባው ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የቃል ኪዳኑ ፈራሚ ለሆኑ አገሮች ይላካል፡፡

2. በዚሁ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት ስምምነቱን የተቀበሉ አምስት አገሮች እውቅና ከሰጡ በኋላ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡ እነዚህ እውቅና መስጠትን የሚመለከቱ መግለጫዎች በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ ዘንድ ይቀመጣሉ፡፡ ዋና ፀሐፊው በበኩሉ ቅጂዎቹን ለሌሎች የስምምነቱ አባል አገሮች ያሰራጫል፡፡ እውቅና መስጠትን የሚመለከት መግለጫ ለተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ በሚላከው ደብዳቤ በማንኛውም ጊዜ ማንሳት ይቻላል፡፡ በዚሁ አንቀጽ መሰረት በማጣራት ሂደት የሚገኝ ጉዳይ የእውቅና መግለጫውን በማንሳት አይደናቀፍም፡፡ አንድ ፈራሚ አገር የላከው እውቅና ማንሳቱን የሚገልፅ ደብዳቤ ለዋና ፀሐፊው ከደረሰ በኋላ ለኮሚቴው ስልጣን እንደገና እውቅና መስጠቱን የሚገልፅ ሌላ ደብዳቤ ካልላከ ኮሚቴው በዚህ አንቀጽ በተደረገው መሠረት ከማንኛውም አገር መረጃ አይቀበልም፡፡

## አንቀጽ 22

1. ስምምነቱን የተቀበለ አገር በግዛቱ ክልል ውስጥ የስምምነቱን ድንጋጌዎች የሚፃረር ተግባር ተፈጽሞብኛል በማለት ግለሰቦች ወይም ተወካዮቻቸው የሚያቀርቡትን ክስ በሚመለከት ኮሚቴው ክሱን የመቀበልና የማጣራት ኃላፊነት እንዲኖረው በዚሁ አንቀጽ መሰረት በማንኛውም ጊዜ እውቅና መስጠት ይችላል፡፡ እንደዚህ ዓይነቱን እውቅና ባልሰጠ አገር ላይ የሚቀርብ የግለሰቦች ክስ በኮሚቴው ተቀባይነት አይኖረውም፡፡
2. በዚሁ ስምምነት ከሰፈሩት ድንጋጌዎች ጋር የሚፃረር፣ ክስ የማቅረብ መብት በአግባቡ ያልተጠቀመ ወይም የከሳሽ ስም የሌለበት ክስ በኮሚቴው ተቀባይነት አያገኝም፡፡
3. በንኡስ አንቀጽ 2 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ለኮሚቴው የደረሰ ክስ በንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት እውቅና ለሰጠውና የስምምነቱን ድንጋጌዎች አላከበረም ለተባለው አገር ይላክለታል፡፡ ተቀባዩ አገር ጉዳዩን የሚመለከት ማብራሪያ ወይም ጉዳዩን

ለማስተካከል የተወሰደ የእርምት እርምጃ ካለ የሚያስረዳ ማብራሪያ በጽሑፍ በስድስት ወራት ውስጥ ለኮሚቴው ያቀርባል፡፡

4. ኮሚቴው በዚሁ አንቀጽ መሰረት ከግለሰቡ ወይም ከተወካዩና ጉዳዩ ከሚመለከተው ፈራሚ አገር የተቀበለውን መረጃ ይመረምራል፡፡

5. ኮሚቴው በዚሁ አንቀጽ መሰረት ከግለሰብ የሚቀርበውን አቤቱታ የሚመረምረው የሚከተሉት ጉዳዮች መሟላታቸውን ካረጋገጠ በኋላ ነው፡፡

   ሀ/ ጉዳዩ በሌላ የዓለም አቀፍ ምርመራ ወይም ሽምግልና ያልታየ ወይም በመታየት ሂደት የማይገኝ መሆኑን

   ለ/ ግለሰቡ ሁሉንም በአገሩ የሚገኙ የማስተካከያ መንገዶች አሟጦ የተጠቀመ መሆን አለበት፡፡ ይሁን እንጂ የእርምት ሂደቱ በቂ ባልሆነ ምክንያት ለረጅም ጊዜ የሚቆይ ከሆነ ወይም የችግሩ ሰለባ ለሆነው ውጤት ማስገኘቱ አጠራጣሪ ከሆነ ይህ አነጋገር ተፈፃሚነት የለውም፡፡

6. ኮሚቴው በዚሁ አንቀጽ መሰረት የቀረበለትን ክስ የሚያጣራው በዝግ ስብሰባ ነው፡፡
7. ኮሚቴው አስተያየቱን ክስ ለቀረበበት ፈራሚ አገርና ለከሳሹ ግለሰብ ያቀርባል፡፡
8. በንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት የስምምነቱን የተቀበሉ አምስት አገሮች እውቅናቸውን ከገለፁ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡ ፡ የእውቅናው መግለጫዎች በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ ዘንድ ይቀመጣሉ፡፡ ዋና ፀሐፊው በበኩሉ ወደ ሌሎች የስምምነቱ ፈራሚ አገሮች ያሰራጫቸዋል፡፡ እውቅናው በማናቸውም ጊዜ ለተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ በሚፃፍ ደብዳቤ ሊነሳ ይችላል፡፡ እንደዚህ ዓይነቱ ዕውቅና የማንሳት ተግባር በዚሁ አንቀጽ መሰረት በማጣራት ሂደት ላይ የሚገኙ ጉዳዮች ላይ የሚደረገውን ምርመራ አያደናቅፍም፡፡ ተጠቃሹ አገር የላከው እውቅና የማንሳት ጥያቄ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ እጅ ከገባ በኋላ እውቅና መስጠት የሚመለከት ደብዳቤ እንዳዲስ ካልተላከ በቀር ከግለሰብ ወይም ከተወካዩ ለኮሚቴው የሚቀርብ ክስ ተቀባይነት የለውም፡፡

## አንቀጽ 23

የኮሚቴውና በአንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ/1/ /ሠ/ በተደነገገው መሠረት የሚቋቋመው ጊዜያው አስታራቂ ኮሚሽን አባላት የተባበሩት መንግስታት ድርጅት መልዕክተኞች/ ሠራተኞች ተልዕኮአቸውን በሚፈጽሙበት ወቅት በድርጅቱ መልዕክተኛነታቸውና ሰራተኝነታቸው ሊያገኟቸው ስለሚገቡ ልዩ ሁኔታዎች ልዩ መብትና ከሃላፊነት ነፃ የመሆን መብት ለመደንገግ በወጣው ስምምነት መሠረት የተመቻቹ ሁኔታዎች ልዩ ጥቅምና ከሃላፊነት ነፃ የመሆን መብት ተጠቃሚዎች ይሆናሉ፡፡

## አንቀጽ 24

ኮሚቴው በዚሁ ቃል-ኪዳን የተጠቀሱትን የስራ እንቅስቃሴዎች በማስመልከት የሚያዘጋጀውን ዓመታዊ ሪፖርት የስምምነቱን ለተቀበሉ አገሮችና ለተባበሩት መንግስታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባኤ ያቀርባል፡፡

## ክፍል ሶስት

## አንቀጽ 25

1. ይህ ስምምነት ለሁሉም አገሮች ለፊርማ ክፍት ነው::
2. ይህ ስምምነት መፅደቅ አለበት:: የማፅደቂያ ሰነዶች በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ ዘንድ ይቀመጣሉ::

## አንቀጽ 26

ይህ ስምምነት ሥራ ላይ ከዋለም በኋላ አገሮች እንዲቀበሉት ክፍት ነው:: ስምምነቱን መቀበል የሚረጋገጠው የመቀበያ ሰነድ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ ፅሕፈት ቤት በማስቀመጥ ነው::

## አንቀጽ 27

1. ይህ ስምምነት የስምምነቱን ሃያኛው የማጽደቂያ ወይም የመቀበያ ሰነድ ለተባበሩት መንግስታት

ድርጅት ዋና ጸሐፊ ከረቀበበት ጊዜ ጀምሮ በሰላሳኛው ቀን የፀና ይሆናል።

2. የስምምነቱ ሃያኛው የማፅደቂያ ወይም የመቀበያ ሰነድ ለተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ ከቀረበ በኋላ የማፅደቂያ ሰነድ ወይም የመቀበያ ሰነድ ለሚያቀርብ እያንዳንዱ አገር ስምምነቱ የሚፀናው የማፅደቂያ ሰነድ ወይም የመቀበያ ሰነድ ከአቀረበበት ጊዜ ጀምሮ በሰላሳኛው ቀን ይሆናል።

## አንቀጽ 28

1. እያንዳንዱ አገር ስምምነቱ በሚፈርምበት ወይም በሚያፀድቅበት ጊዜ በዚሁ ስምምነት አንቀጽ 20 መሰረት ለሚቋቋመው ኮሚቴ ስልጣን እውቅና እንደማይሰጥ መግለጽ ይችላል።
2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት ተአቅቦውን ያቀረበ ማንኛውም የስምምነቱ አባል አገር በማንኛውም ጊዜ ለተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ በሚጽፈው ደብዳቤ በኩል ተአቅቦውን ማንሳት ይችላል።

## አንቀጽ 29

1. ማንኛውም የስምምነቱ አባል አገር የማሻሻያ ሃሳብ ሊያቀርብ ይችላል፡፡ የማሻሻያ ሃሳቡንም የሚያቀርበው ለተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ ይሆናል፡፡ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ በበኩሉ የማሻሻያ ሃሳቡ እንደደረሰው ፈራሚ አገሮች ተሰብስበው በቀረበው የማሻሻያ ሃሳብ ላይ ለመነጋገርና ለመወሰን ይፈልጉ እንደሆነ በመጠየቅ የማሻሻያ ሃሳቡ ይልክላቸዋል፡፡ ይህ ከሆነ በአራት ወራት ውስጥ ቢያንስ የአባሎቹ አንድ ሶስተኛ መሰብሰቡን ከደገፉ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ በድርጅቱ ስም የስብሰባ ጥሪ ያስተላልፋል፡፡ የማሻሻያ ሃሳቡ በስብሰባው ላይ ተገኝተው ድምጽ ከሰጡት አባል አገሮች በብዙሐኑ ድምጽ የተደገፈ ከሆነ ሁሉም የስምምነቱ ፈራሚ አገሮች እንዲቀበሉት ዋና ፀሐፊው ያሰራጨዋል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት ተቀባይነት ያገኘውን የማሻሻያ ሃሳብ ይህን ስምምነት ከተቀበሉ አገሮች መካከል ሁለት ሶስተኛዎቹ የሕገ-መንግስታቸውን አሰራር መሰረት በማድረግ

የተቀበሉት መሆኑን በመግለፅ ለተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ ሲያሳውቁ የፀና ይሆናል፡፡

3. የማሻሻያ ሃሳቡ ከፀና በኋላ ለተቀበሉት ፈራሚ አገሮች አስገዳጅ ይሆናል፡፡ ሌሎች የስምምነቱ ፈራሚ አገሮች ግን በስምምነቱ ሕጎችና ቀደም ሲል ራሳቸው የተቀበሏቸውን የማሻሻያ ሃሳቦች ያከብራሉ፡፡

## አንቀጽ 30

1. የስምምነቱን አተረጓጎም ወይም አፈፃፀም በተመለከተ በሁለት ወይም ከሁለት በላይ የስምምነቱ አባል አገሮች መካከል የሚፈጠር አለመግባባት በውይይት መፍታት ካልተቻለ በአንዳቸው ጥያቄ ለግልግል ዳኝነት ይቀርባል፡፡ ጉዳዩ በግልግል ዳኝነት እንዲታይ ጥያቄ ከቀረበበት ጊዜ አንስቶ በስድስት ወራት ውስጥ በግልግል ዳኝነቱ አደረጃጀት ላይ ከስምምነት ላይ ካልደረሱ አንዱ አገር ጉዳዩን ወደ ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት ሊያቀርበው ይችላል፡፡ ይህ የሚሆነው በፍርድ ቤቱ ደምብ መሰረት ነው፡፡

2. እያንዳንዱ አገር ስምምነቱን በሚፈርምበት፣ በሚያፀድቅበት ወይም በሚቀበልበት ጊዜ በዚሁ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ /1/ እንደማይገደድ መግለጽ ይችላል። ሌሎች አገሮችም ተዓቅቦውን ካስቀመጠ አገር ጋር በሚኖራቸው ግንኙነት በዚሁ ንኡስ አንቀጽ ሕግ አይገደዱም።

3. በዚሁ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ /2/ ተዓቅቦ ያስቀመጠ አገር በማንኛውም ጊዜ ለተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ በሚፅፈው ደብዳቤ በኩል ተዓቅቦውን ማንሳት ይችላል።

## አንቀጽ 31

1. ማንኛውም የስምምነቱ አባል አገር ለተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ በሚፅፈው ደብዳቤ ከስምምነቱ አባልነት መውጣት ይችላል። አባልነቱ የሚቀረው፣ ውሳኔው ለተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ ከአንድ ዓመት በኋላ ይሆናል።

2. ከስምምነቱ ለመውጣት የሚደረገው ውሳኔ ስምምነቱን የተቀበለ አገር ከስምምነቱ ለመውጣት ያደረገው ውሳኔ ከመጽናቱ በፊት ከስምምነቱ ድንጋጌዎች ውጭ በመፈፀሙ ድርጊት ወይም ባለመፈፀሙ ከሚደርስበት ተጠያቂነት ነፃ አያደርገውም፣ እንዲሁም ከስምምነቱ ለመውጣት የተደረገው ውሳኔ ከመጽናቱ በፊት በኮሚቴው ተይዞ ምርመራ እየተደረገበት ያለ ጉዳይ አይቋረጥም፡፡
3. የስምምነቱ አባል በሆነ አገር የሚቀርብ አባልነት የማቋረጥ ጥያቄ ከፀናበት ጊዜ ጀምሮ የሚቀርብ አዲስ ክስ በኮሚቴው ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

## አንቀጽ 32

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ ለሁሉም የተባበሩት መንግስታት ድርጅት አባል አገሮችና ለሁሉም ስምምነቱን የፈረሙ ወይም የተቀበሉ አገሮች የሚከተሉትን ጉዳዮች ያሳውቃቸዋል፡፡

ሀ/ በአንቀጽ 25 እና 26 መሰረት መንግስታት መረፈማቸውን፣ ማጽደቃቸውንና መቀበላቸውን፣

ለ/ በአንቀጽ 27 መሰረት ስምምነቱ ተፈፃሚ የሚሆንበት ቀን እና በአንቀጽ 29 መሰረት የማሻሻያ ሃሳቦች ተፈፃሚ የሚሆኑበትን ቀን፣

ሐ/ በአንቀጽ 31 መሰረት የሚቀርብ አባልነትን የማቋረጥ ውሳኔ፣

## አንቀጽ 33

1. በዓረብኛ፣ በቻይንኛ፣ በእንግሊዝኛ፣ በፈረንሳይኛና እስፓንኛ የተዘጋጁ የስምምነቱ ሰነዶች እኩል ተቀባይነት ያላቸው ሲሆን፤ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት መዝገብ ቤት ይቀመጣሉ።
2. የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ ትክክል መሆናቸው የተረጋገጡ የስምምነቱ ቅጂዎች ወደ ሁሉም አገሮች ያሰራጫል።

# የሕጻናት መብቶች ስምምነት

*የጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ ቁጥር 44/25 1989 እ.ኤ.አ.*

## መግቢያ

**የዚህ ስምምነት ተዋዋይ አገሮች**

በተባበሩት መንግስታት ቻርተር በታወጁት መርሆች መሰረት ሰዎች ሁሉ በተፈጥሮ ክቡር መሆናቸውንና እኩልና የማይገሰሱ መብቶች ያሏቸው መሆኑን አውቆ መቀበል ለዓለም የነፃነት፣ የፍትሕና የሰላም መሰረት መሆኑን በመገንዘብ፤

የተባበሩት መንግስታት ሕዝቦች ለመሰረታዊ ሰብዓዊ መብቶችና ለሰው ክብርና ዋጋ ያላቸውን እምነት በቻርተሩ ስለአረጋገጡና ማሕበራዊ እድገትንና የተሻለ የኑሮ ደረጃን በሰፊ ነፃነት ለማራመድ መወሰናቸውን በማጤን፤

እያንዳንዱ ሰው ዘርን፣ ቀለምን፣ ጾታን፣ ቋንቋን፣ ሃይማኖትን፣ ፖለቲካን ወይም ሌላ አመለካከትን፣ ብሔርን ወይም ማሕበራዊ ምንጭን፣ ሀብትን፣ ትውልድን ወይም ሌላ አቋምን በመሳሰሉ ልዩነቶች ሳይደረጉበት በዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብቶች

መግለጫ እና በዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ስምምነቶች በተደነገጉት መብቶችና ነፃነቶች የመጠቀም መብት ያለው መሆኑን የተባበሩት መንግስታት ማወጁን በማወቅ፤

የተባበሩት መንግስታት ሕጻናት ልዩ እንክብካቤና እርዳታ እንደሚያስፈልጋቸው በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች መግለጫ ማወጁን በማስታወስ፣

ቤተሰብ የኅብረተሰብ መሰረትና ለአባሎቹ፣ በተለይም ለሕጻናት ዕድገትና ደሕንነት ተስማሚ የሆነ የተፈጥሮ ተቋም በመሆኑ በሕብረተሰቡ ውስጥ ያለበትን ኃላፊነት በሚገባ ለመወጣት እንዲችል አስፈላጊው ጥበቃና እገዛ ሊደረግለት የሚገባ መሆኑን በማመን፤

ሕጻኑ ሰብዓዊ ዕድገቱ የተሟላና የተስተካከለ እንዲሆን በቤተሰብ ውስጥ በደስታ፣ በፍቅርና በመግባባት መንፈስ ማደግ እንደሚያስፈልገው በመገንዘብ፤

ሕጻኑ በሕብረተሰብ ውስጥ የራሱን የግል ሕይወት ለመምራት እንዲችል በሚገባ መዘጋጀት ስለአለበት በተባበሩት መንግስታት ቻርተር በታወጁት መሰረተ ሀሳቦች በተለይም የሰላም፣ የክብር፣

የመቻቻል፣ የነጻነት፣ የእኩልነትና የመተባበር መንፈስ ሰርጾበት እንዲያድግ ማድረግ ተገቢ መሆኑን በመረዳት፣

ለሕጻናት ልዩ እንክብካቤ የማድረጉ አስፈላጊነት በ1924 እ.ኤ.አ በወጣው የጀኔቫ የሕጻናት መብቶች መግለጫ እንዲሁም ጠቅላላ ጉባዔው ኀዳር 20 ቀን 1959 እ.ኤ.አ በተቀበለው የሕጻናት መብቶች መግለጫ መመልከቱንና በዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ ፣ በሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳን (በተለይ በአንቀጽ 23 እና 24) በዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ማህበራዊና ባሕላዊ መብቶች ቃልኪዳን በተለየ አንቀጽ 10 እና የሕጻናት ደህንነት በሚመለከታቸው ልዩ ልዩ ተቋሞችና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ደንቦችና አግባብ ባላቸው ሰነዶች ዕውቅና ያገኘ መሆኑን በማስታወስ፤

በሕጻናት መብቶች መግለጫ እንደተመለከተው፣ አንድ ሕጻን በአካልና በአእምሮ ያልዳበረ በመሆኑ ምክንያት፣ ተገቢ የሆነ የሕግ ጥበቃ ማግኘትን ጨምሮ፣ ከመወለዱ በፊትም ሆነ ከተወለደ በኋላ ልዩ ጥንቃቄና እንክብካቤ እንደሚያሻው በማስታወስ፤

ስለሕጻናት ደህንነት ጥበቃና እንክብካቤ የወጡትን የማሕበራዊና የሕግ መርሆች መግለጫ፤ በተለም በብሔራዊና በዓለም አቀፍ ደረጃ ሕጻናት ለማሳደጊያ ተቋም የሚሰጡበትንና የጉዲፈቻ ልጅ የሚሆኑበትን ድንጋጌዎች፣ የተባበሩት መንግስታትን የወጣት ጥፋተኞች የፍትሕ አስተዳደር ደንቦች (የቤይጂንግ ደንቦች) እና በአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታና በጦርነት ወቅት ለሴቶችና ለሕጻናት ስለሚደረገው ጥበቃ የወጣውን መግለጫ በማስታወስ፤

በሁሉም አገሮች እጅግ በጣም አስቸጋሪ በሆነ ሁኔታ ውስጥ የሚኖሩ ሕጻናት ስለአሉና እነዚህም ሕጻናት የተለየ ትኩረት የሚያስፈልጋቸው መሆኑን በማወቅ፤

የእያንዳንዱ ሕዝብ ልማድና ባሕል ለሕጻናት ደህንነት ጥበቃና የተስተካከለ ዕድገት የሚኖረውን ጥቅም ከግምት ውስጥ በማስገባት፤

በእያንዳንዱ አገር፣ በተለይም በመልማት ላይ ባሉ አገሮች፣ የሕጻናትን የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻል ዓለም አቀፍ ትብብር የሚያስገኘውን ፋይዳ በመገንዘብ፤ እንደሚከተለው ተስማምተዋል::

# ክፍል አንድ

## አንቀጽ 1

ሕጻናትን በሚመለከት ሕግ፣ አካለ መጠን የመድረሻው ዕድሜ ከዚህ ያነሰ ካልሆነ በቀር፣ በዚህ ስምምነት «ሕፃን» ማለት ዕድሜው ከ18 ዓመት በታች የሆነ ማንኛውም ሰው ነው።

## አንቀጽ 2

1. ተዋዋይ አገሮች በግዛቶቻቸው ውስጥ ለሚገኝ ለእያንዳንዱ ሕጻን በርሱ፣ ወይም በወላጆቹ ወይም በሕጋዊ አሳዳሪው ዘር፣ ቀለም፣ ጾታ፣ ቋንቋ፣ ሃይማኖት፣ የፖለቲካ ወይም ሌላ አመለካከት፣ በብሔር፣ በጎሳ ወይም በማሕበራዊ ዳራ፣ በሀብት፣ በአካል ጉድለት፣ በትውልድ፣ ወይም በሌላ ሁኔታ ምክንያት ምንም ዓይነት ልዩነት ሳይደረግበት በዚህ ስምምነት የተዘረዘሩትን መብቶች ሊያከብሩለትና ሊያረጋግጡለት ተስማምተዋል።

2. ተዋዋይ አገሮች አንድ ሕጻን በወላጆቹ፣ ወይም በሕጋዊ አሳዳሪው፣ ወይም በቤተሰቡ አባላት ሁኔታ፣ ወይም እንቅስቃሴ፣ ወይም በተሰጠ አስተያየት፣ ወይም እምነት ሳቢያ ማንኛቸውም ዓይነት አድልዎ እንዳይደርስበት ወይም ቅጣት እንዳይፈጸምበት ለማረጋገጥ ተገቢ እርምጃዎችን ሁሉ መውሰድ አለባቸው።

## አንቀጽ 3

1. በመንግስት ወይም በግል የማሕበራዊ ደህንነት ተቋሞች፣ በፍርድ ቤቶች፣ በአስተዳደር ባለሥልጣኖች ወይም በሕግ አውጪ አካላት ሕጻናትን የሚመለከት ማናቸውም እርምጃ ሲወሰድ የሕጻናቱ ጥቅም የሚጠበቅበት ሁኔታ ከሁሉ ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ይሆናል።
2. ተዋዋይ አገሮች የወላጆችን፣ የሕጋዊ አሳዳሪዎችን ወይም በሕግ ኃላፊነት የተሰጣቸውን ሌሎች ሰዎች መብቶችና ግዴታዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት ለሕፃናት ደኅንነት የሚያስፈልገው ጥበቃና ጥንቃቄ ሁሉ

መደረጉን ለማረጋገጥ፤ ለዚህም ተገቢ የሆኑትን ሕግ የማውጣት እና የአስተዳደር እርምጃዎች ለመውሰድ ተስማምተዋል፡፡

3. ተዋዋይ አገሮች ለሕጻናት እንክብካቤና ጥበቃ ኃላፊነት ያለባቸው ተቋሞችና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች አግባብ ባላቸው ባለሥልጣን መስሪያ ቤቶች የወጡትን በተለይም የአደጋ መከላከልን፣ የጤና አጠባበቅን፣ የሰው ኃይል ብዛትና ተስማሚነትን እንዲሁም ቁጥጥርን የሚመለከቱ ደረጃዎች መጠበቃቸውን ያረጋግጣሉ፡፡

## አንቀጽ 4

ተዋዋይ አገሮች በዚህ ስምምነት ዕውቅና ያገኙትን መብቶች ተግባራዊ ለማድረግ አስፈላጊ የሆኑ ሕግ የማውጣት ፣ የአስተዳደርና ሌሎች እርምጃዎችን ሁሉ ይወስዳሉ፡፡ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ባሕላዊ መብቶችን በሚመለከት ተዋዋይ አገሮች የሚወስዷቸው እርምጃዎች የየአገራቸው ሀብት በሚፈቅደው ሙሉ አቅምና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም በዓለም አቀፍ ትብብር በመታገዝ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 5

ተዋዋይ አገሮች ወላጆች፣ ወይም እንደአግባቡ የቤተ ዘመድ አባላት፤ ወይም የአካባቢው ባሕል ሲፈቅድ ማኅበረሰቡ፣ ሕጋዊ አሳዳሪዎች፤ ወይም ለሕጻኑ አስተዳደር በሕግ ኃላፊነት የተሰጣቸው ሌሎች ሰዎች ሕጻኑ በዚህ ስምምነት በታወቁት መብቶች ሲጠቀም በየጊዜው ከሚያድገው ችሎታው ጋር የተገናዘበ ተገቢ አመራር በመስጠትና በመቆጣጠር ረገድ ያላቸውን ኃላፊነት፣ መብትና ግዴታ ያከብራሉ።

## አንቀጽ 6

1. ተዋዋይ አገሮች ማንኛውም ሕጻን በሕይወት የመኖር ተፈጥሯዊ መብት እንዳለው ያውቃሉ።
2. ተዋዋይ አገሮች አቅም የሚፈቅደውን እርምጃ ሁሉ በመውሰድ የሕጻናትን በሕይወት መኖርንና እድገትን ያረጋግጣሉ።

## አንቀጽ 7

1. ማንኛውም ሕጻን እንደተወለደ ይመዘገባል፤ ከተወለደበት ጊዜ ጀምሮም መጠሪያ ስምና ዜግነት የማግኘት፣ በተቻለ መጠንም ወላጆቹን የማወቅና ከወላጆቹ እንክብካቤ የማግኘት መብት አለው።
2. ተዋዋይ አገሮች በተለይ ሕጻኑ አገር የለሽ እንዳይሆን በብሔራዊ ሕጋቸው መሰረት እንዲሁም ስለ እነዚህ ጉዳዮች አግባብ ባላቸው ዓለም አቀፍ ሰነዶች የተጣሉባቸውን ግዴታዎች በማክበር እነዚህ መብቶች ስራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣሉ።

## አንቀጽ 8

1. ተዋዋይ አገሮች ሕጻኑ ሕገ-ወጥ ጣልቃገብነት ሳይደረግበት በሕግ የተረጋገጠው ዜግነቱን፣ ስሙንና የቤተሰብ ግንኙነቱን ጨምሮ ማንነቱን ለመጠበቅ ያለውን መብት ያከብራሉ።
2. ሕጻኑ ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ ከማንነቱ መገለጫዎች አንደኛውን ወይም ሁሉንም የተነፈገ ሲሆን፣ ማንነቱ በተሟላ አኳኋን በአስቸኳይ እንደገና እንዲረጋገጥ

ተዋዋይ አገሮች ተገቢ የሆነውን ዕርዳታና ጥበቃ ያደርጋሉ።

## አንቀጽ 9

1. ጉዳዩ በፍ/ቤት እንደገና ሊታይ የሚችልበት ሁኔታ እንደተጠበቀ ሆኖ አግባብ ያላቸው ባለሥልጣኖች አግባብ ባለው ሕግና ሥነ ሥርዓት መሰረት ለሕጻኑ ጥቅም ሲባል ሕጻኑ ከወላጆቹ ተለይቶ እንዲኖር ካልወሰኑ በቀር፣ ማንኛውም ሕጻን ያለወላጆቹ ፈቃድ ከወላጆቹ እንዳይለይ ተዋዋይ አገሮች ያረጋግጣሉ። ሕጻኑ ከቤተሰቦቹ ተለይቶ እንዲኖርና የት ቦታም መኖር እንዳለበት መወሰን ወላጆቹ ሕጻኑን ሲበድሉት፣ ወይም ችላ ሲሉት፣ ወይም ለየብቻ ሲኖሩ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል።
2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 በተገለጸው መሰረት ጉዳዩ በሚታይበት ጊዜ በጉዳዩ የሚያገባቸው ሁሉ ተካፋይ የመሆንና አስተያየታቸውን የመግለጽ ዕድል ይሰጣቸዋል።
3. ተዋዋይ አገሮች ለሕጻኑ ጥቅምና ደህንነት ተቃራኒ ሆኖ ካልተገኘ በቀር፣ ከአንደኛው ወይም ከሁለቱም

ወላጆቹ ለተለየ ሕጻን በየጊዜው ከወላጆቹ ጋር በግልና በቀጥታ የመገናኘት መብቱን ያከብሩለታል፡፡

4. ሕጻኑ ከወላጆቹ የተለየው ተዋዋይ አገር በወሰደው እርምጃ ፣ ለምሳሌ፣ ከወላጆቹ አንደኛው ወይም ሁለቱም ወይም ሕጻኑ በመታሰሩ ወይም ወህኒ ቤት በመግባቱ፣ በመሰደዱ፣ ከአገር በመባረሩ ወይም በመሞቱ፣ (በእስር ቤት በማንኛውም ምክንያት የሚያጋጥም ሞትን ጨምሮ) ሲሆን ለሕጻኑ፣ ወይም ለወላጆቹ አግባብነት ያለው ሲሆን ለሌላ የቤተሰቡ አባል፣ ርምጃዎች የተወሰዱበት የቤተሰብ አባል ያለበትን ቦታ በሚመለከት መረጃ መስጠቱ የሕጻኑን ደኅንነት አደጋ ላይ የሚጥል ካልሆነ በቀር፣ ተዋዋዩ አገር ጥያቄ ሲቀርብለት አስፈላጊ መረጃዎችን ይሰጣል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ተዋዋይ አገሮች እንዲህ ያለውን ጥያቄ ማቅረብ በራሱ ጉዳዩ በሚመለከታቸው ሰዎች ላይ ችግር የማያስከትል መሆኑን ያረጋግጣሉ፡፡

# አንቀጽ 10

1. በአንቀጽ 9 ንኡስ ዓንቀጽ 1 በተገለጹት የተዋዋይ አገሮች ግዴታዎች መሰረት አንድ ሕጻን ወይም ወላጆቹ ወደ ተዋዋይ አገር በመግባት ወይም ከተዋዋይ አገር በመዉጣት ቤተሰቡ እንዲቀላቀል በሕጻኑ ወይም በወላጆቹ ማመልከቻ ሲቀርብ ጉዳዩ በቀና መንፈስ፣ በሰብአዊነትና በአፋጣኝ ታይቶ እርምጃ ይወሰዳል። ከዚህ በተጨማሪም ተዋዋይ አገሮች እንዲህ ዓይነቱን ጥያቄ ማቅረብ በአመልካቾቹና በቤተሰቦቻቸው ላይ ምንም ዓይነት መዘዝ የማያስከትል መሆኑን ያረጋግጣሉ።
2. የተለየ ሁኔታ ካላጋጠመ በቀር፣ ወላጆቹ በተለያዩ አገሮች የሚኖሩበት ሕጻን በየጊዜው ከወላጆቹ ጋር በግልና በቀጥታ የመገናኘት መብት አለው። በአንቀጽ 9 ንሱስ አንቀጽ 3 የተገለጸውን የተዋዋይ አገሮች ግዴታ መሰረት በማድረግ ይህን መብት ተግባራዊ ለማድረግ ተዋዋይ አገሮች ሕጻኑና ወላጆቹ የራሳቸውን አገር ጨምሮ ከማንኛውም አገር ለመውጣትና ወደ ራሳቸውም አገር ለመግባት ያላቸውን መብት ያከብራሉ። ከማንኛውም አገር

የመውጣት መብት ሊገደብ የሚችለው በሕግ በተደነገገውና የአገራዊ ደኅንነትን፣ የሕዝብን ጸጥታ፣ ጤና ወይም መልካም ስነ ምግባር፣ ወይም የሌሎችን መብቶችና ነጻነቶች ለማስከበር አስፈላጊ በሆኑትና በዚህ ስምምነት ከተገለጹት ሌሎች መብቶች ጋር በተጣጣመ አኳኋን ብቻ ነው።

## አንቀጽ 11

1. ተዋዋይ አገሮች በሕገ ወጥ መንገድ ሕጻናትን ከአገር ማስወጣትንና ወደ አገር እንዳይመለሱ ማድረግን ለማስቀረት እርምጃዎችን ይወስዳሉ።
2. ለዚህም ዓላማ ተዋዋይ አገሮች ሁለት ወይም ብዙ ተዋዋዮችን ያቀፉ ስምምነቶች እንዲፈጸሙ ወይም ቀደም ሲል ያሉት ስምምነቶች ተቀባይነት እንዲያገኙ ያበረታታሉ።

## አንቀጽ 12

1. ተዋዋይ አገሮች ሐሳብ ለማመንጨት ችሎታ ያለው ማንኛውም ሕጻን በሚመለከተው ጉዳይ ሁሉ ሃሳቡን

በነጻነት የመግለጽ መብቱን ያረጋግጣሉ። ሕጻኑ የሚያቀርበውም ሃሳብ ዕድሜውና በአዕምሮ የመብሰል ሁኔታው እየታየ ተገቢው ክብደት ይሰጠዋል።

2. ለዚህ ዓላማ ሲባል በተለይ ሕጻኑን የሚመለከት ጉዳይ በዳኝነት ወይም በአስተዳደር አካል በሚታይበት ጊዜ ከአገሩ የሥነ ሥርዓት ሕግ ጋር በተጣጣመ ሁኔታ ራሱ በቀጥታ ወይም በእንደራሴ ወይም አግባብ ባለው አካል በኩል የመሰማት ዕድል ይሰጠዋል።

## አንቀጽ 13

1. ሕጻኑ ሃሳቡን የመግለጽ መብት አለው። ይህም መብት በአገሮች ድንበሮች ሳይወሰን ሁሉንም ዓይነት መረጃዎችና ሃሳቦች በቃል፣ በጽሑፍ፣ ወይም በሕትመት፣ ወይም በሥነ ጥበብ መልክ፣ ወይም ማንኛውም የሕጻኑ ምርጫ በሆነ መገናኛ ዘዴ የመጠየቅ፣ የመቀበልና የማስተላለፍ መብትን ይጨምራል።

2. የዚህ መብት አጠቃቀም የተወሰኑ ገደቦች ሊደረጉበት ይችላል። ነገር ግን ገደቦቹ አስቀድሞ በሕግ የተደነገጉና

   ሀ/ የሌሎችን መብትና መልካም ስም ለመጠበቅ፣ ወይም

   ለ/ የአገርን ብሔራዊ ጸጥታ ወይም የሕዝብን ሰላም ወይም ጤንነት ወይም ሞራል ለመጠበቅ፣ የሚያስፈልጉት ብቻ ይሆናሉ።

## አንቀጽ 14

1. ተዋዋይ አገሮች የሕጻኑን የሃሳብ፣ የሕሊናና የሃይማኖት ነጻነት ያከብራሉ።
2. ተዋዋይ አገሮች ወላጆች፣ ወይም አግባብ ባለው ሁኔታም ሕጋዊ አሳዳሪዎች፣ ለሕጻናት ከዕድገታቸው ጋር በተመጣጠነ ሁኔታ ስለመብታቸው አጠቃቀም አመራር ለመስጠት ያላቸውን መብትና ኃላፊነት ያከብራሉ።
3. ሃይማኖትን ወይም እምነትን በመግለጽ ነጻነት ላይ የሚደረጉት ገደቦች በሕግ የተደነገጉና የሕዝብን ደኅንነት፣ ፀጥታ፣ ጤንነት፣ ወይም ሞራል፣ ወይም

የሌሎችን መሰረታዊ መብቶችና ነጻነቶችን ለማስከበር አስፈላጊ የሆኑ ብቻ ይሆናሉ፡፡

## አንቀጽ 15

1. ተዋዋይ አገሮች ሕጻናት በማኅበር የመደራጀትና ሰላማዊ ስብሰባ የማድረግ መብት ያላቸው መሆኑን አውቀው ይቀበላሉ፡፡
2. በዴሞክራሲያዊ ኅብረተሰብ አገራዊ ደኅንነትን ወይም የሕዝብን ደኅንነት ወይም ፀጥታ፣ የሕዝብን ጤና ወይም መልካም ስነ ምግባር ወይም የሌሎች ሰዎችን መብቶችና ነጻነቶች ለመጠበቅ አስፈላጊ ከሆኑትና ከሕግ ጋር በተጣጣመ ሁኔታ ከሚደነገጉት በቀር በእነዚህ መብቶች አጠቃቀም ላይ ማናቸውም ዓይነት ገደቦች አይደረጉም፡፡

## አንቀጽ 16

1. ማንኛውም ሕጻን በግል ኑሮው፣ በቤተሰቡ፣ በመኖሪያ ቤቱ ወይም በሚጻጻፈው ደብዳቤ ሥርዓትን ያልተከተለ ወይም ሕገ ወጥ ጣልቃ

ገብነት አይፈጸምበትም፤ ክብሩና መልካም ዝናውም በሕገ ወጥ መንገድ አይደፈርም፡፡

2. ሕጻኑ እንዲህ ካለው ጣልቃ ገብነትና መደፈር የሕግ ጥበቃ የማግኘት መብት አለው፡፡

## አንቀጽ 17

ተዋዋይ አገሮች የመገናኛ ብዙሃን የሚያከናውኑትን ጠቃሚ ስራ በመገንዘብ ሕጻኑ በተለይ ማሕበራዊ፣ መንፈሳዊና የሞራል ደሕንነቱን፣ አካላዊና አዕምሯዊ ጤንነቱን ለመጠበቅ የሚያግዙትን መረጃዎችና ማቴሪያሎች ከተለያዩ አገራዊና ዓለም አቀፋዊ ምንጮች ማግኘት መቻሉን ያረጋግጣሉ፡፡ ለዚህ ተግባራዊነትም ተዋዋይ አገሮች፡-

ሀ/ የአንቀጽ 29ን መንፈስ በተከተለ መልኩ መገናኛ ብዙሃን ለሕጻናት ማሕበራዊና ባሕላዊ ሕይወት የሚጠቅም መረጃና ማቴሪያሎች እንዲያሰራጩ ያበረታታሉ፤

ለ/ የእነዚህን መረጃና ማቴሪያሎች ከተለያዩ ባሕላዊ፣ አገራዊና ዓለም አቀፋዊ ምንጮች መመንጨት፣

ልውውጥና ስርጭትን የሚመለከት ዓለም አቀፍ ትብብር እንዲኖር ያበረታታሉ፤

ሐ/ የሕጻናት መጻሕፍት እንዲታተሙና እንዲሰራጩ ያበረታታሉ።

መ/ የመገናኛ ብዙሃን ለአናሳ ብሄረሰቦች ወይም ለአካባቢው ነባር ህዝብ ተወላጅ ሕፃናት የቋንቋ ችግር የተለየ ትኩረት እንዲሰጡ ያበረታታሉ፤

ሠ/ በአንቀጽ 13 እና 18 የተደነገገውን በማጤን፣ በሕፃናት ደኅንነት ላይ ጠንቅ ከሚያስከትሉ መረጃና ማቴሪያሎች ሕጻናትን ለመጠበቅ አግባብ ያላቸው መመሪያዎች እንዲወጡ ያበረታታሉ።

## አንቀጽ 18

1. ተዋዋይ አገሮች ሁለቱም ወላጆች ለሕጻኑ አያያዝና አስተዳደግ የጋራ ኃላፊነት አለባቸው የሚለው መርህ ተቀባይነት ማግኘቱን ለማረጋገጥ የሚቻላቸውን ሁሉ ያደርጋሉ። ለሕጻኑ እድገትና አስተዳደግ ወላጆች፤ ወይም እንደሁኔታው ሕጋዊ አሳዳሪዎች ከማንም የበለጠ ኃላፊነት ያለባቸው ሲሆን ዋናው ትኩረታቸውም የሕጻኑ ጥቅም ይሆናል።

2. በዚህ ስምምነት የተመለከቱትን የሕጻናት መብቶች ተፈፃሚነትን ለማረጋገጥ፤ ሕጻናትን የማሳደግ ሃላፊነታቸውን እንዲወጡ ለማድረግና ለማበረታታት ተዋዋይ አገሮች ለወላጆችና ለሕጋዊ ኣሳዳሪዎች ተገቢውን ዕርዳታ ያደርጋሉ፤ ለሕጻናት እንክብካቤ የሚሰጡ ተቋሞች፣ ድርጅቶችና አገልግሎቶች መቋቋማቸውንም ያረጋግጣሉ፡፡

3. ተዋዋይ አገሮች ወላጆቻቸው ሰራተኞች የሆኑ ሕጻናት ለሕጻናት እንክብካቤ በተመደቡ አገልግሎቶችና ድርጅቶች የመጠቀም መብታቸውን ለማረጋገጥ ተገቢ የሆኑ እርምጃዎችን ሁሉ ይወስዳሉ፡፡

## አንቀጽ 19

1. ሕጻኑ በወላጁ/ጆቹ/፣ ወይም በሕጋዊ አሳዳሪው/ዎቹ/ ወይም በማንኛውም ሌላ ሰው ስር በሚገኝበት ጊዜ ማናቸውም ዓይነት አካላዊ ወይም አዕምሯዊ ጥቃት፣ጉዳት፣ በደል፣ ግዴለሽ ወይም ቸልተኛ አያያዝ፣ ማጉላላት ወይም ብዝበዛና የግብረ ስጋ ግንኙነት በደል ጭምር እንዳይፈጸምበት ተዋዋይ

አገሮች ተገቢ የሆኑ የሕግ ማውጣት ፣ አስተዳደራዊ፣ ማሕበራዊና ትምህርታዊ እርምጃዎችን ይወስዳሉ።

2. እንዲህ ያሉት የጥበቃ እርምጃዎች እንዳግባብነቱ ለሕጻኑና ሕጻኑን ለሚንከባከቡ ሰዎች አስፈላጊውን ድጋፍ የሚሰጡ ማሕበራዊ ፕሮግራሞችን ለመዘርጋት፤ እንዲሁም ቀደም ብሎ የተገለጹት ተገቢ ያልሆኑ የሕጻናት የአያያዝ ሁኔታዎች እንዳያጋጥሙ ለመከላከል ሲያጋጥሙም የአጥፊውን ማንነት ለመለየት፣ ዘገባ ለማቅረብ፣ ለሚመለከተው ለመምራት፣ ለመመርመር፣ ለማከም፣ ለመከታተልና እንደ አግባብነቱ ፍርድ ቤት ጣልቃ እንዲገባ ለማድረግ የሚያስችሉ አስተማማኝ ስነ ስርዓቶችን ያጠቃልላሉ።

## አንቀጽ 20

1. ለጊዜው ወይም ለዘለቄታው ከቤተሰቡ ለተለየ ወይም ለራሱ ጥቅም ሲባል ከቤተሰቡ መለየት ላለበት ሕጻን መንግስት ልዩ ጥበቃና ዕርዳታ ያደርጋል።

2. ተዋዋይ አገሮች በአገራዊ ሕጎቻቸው መሰረት እንዲህ ዓይነቱ ሕጻን አማራጭ እንክብካቤ ማግኘቱን ያረጋግጣሉ፡፡
3. እንዲህ ዓይነቱ እንክብካቤ ለማደጎ መስጠትን፣ በእስልምና ሕግ መሰረት ካፋላህ ማድረግን፣ ጉዲፈቻ መስጠትን ወይም አስፈላጊ ሲሆን ተስማሚ ለሆነ የሕጻናት መሳደጊያ ተቋም መስጠትንና የመሳሰሉትን ሊጨምር ይችላል፡፡ መፍትሔዎች በሚጤኑበት ጊዜ የሕጻኑ እድገት ቀጣይነት እንዲኖረው የማድረግ አስፈላጊነትና ለሕጻኑ የጎሳ፣ የሃይማኖት፣ የባሕልና የቋንቋ መሰረት ተገቢ ትኩረት ይሰጣል፡፡

## አንቀጽ 21

ለጉዲፈቻ ስርዓት እውቅና የሚሰጡ ወይም የሚፈቅዱ ተዋዋይ አገሮች ከሁሉም በላይ ለሕጻኑ ጥቅም ቅድሚያ መሰጠቱን ያረጋግጣሉ፤ በዚህ መሰረት እነዚህ አገሮች፦

ሀ/ ሕጻኑ ለጉዲፈቻ የተሰጠው አግባብ ባላቸው ባለስልጣኖች ፈቃድ መሆኑን፤ ባለስልጣኖቹም

አግባብ ባለው ሕግና ስነ-ስርዓት እንዲሁም አግባብ ባለውና እምነት በሚጣልበት ማንኛውም መረጃ ላይ ተመስርተው የሕጻኑ ወላጆች፣ ዘመዶችና ሕጋዊ አሳዳሪዎች ሁኔታ የሕጻኑን ለጉዲፈቻ መስጠት የሚፈቅድ መሆኑን መወሰናቸውንና አስፈላጊ ሲሆንም ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሰዎች አስፈላጊውን የምክር አገልግሎት ካገኙ በኋላ ለጉዲፈቻው ፈቃዳቸውን መስጠታቸውን ያረጋግጣሉ፡፡

ለ/ ሕጻኑን በተወለደበት አገር ላለ ማሳደጊያ ተቋም፣ ወይም በጉዲፈቻ ለሚቀበል ቤተሰብ መስጠት ወይም በሌላ ተስማሚ ዘዴ ማሳደግ ካልተቻለ በሌላ አገር ውሰጥ በጉዲፈቻ መስጠትን እንደ አማራጭ መፍትሔ ይቀበላሉ፡፡

ሐ/ በሌላ አገር ውስጥ ለጉዲፈቻ የተሰጠ ሕጻን በአገር ውስጥ ከሚደረግ ጉዲፈቻ እኩል የሆነ ጥበቃና እንክብካቤ የሚደረግለት መሆኑን ያረጋግጣሉ፡፡

መ/ በሌላ አገር ውስጥ ለጉዲፈቻ መስጠት በጉዲፈቻው ሂደት ውስጥ ተሳታፊ ለሆኑት ሰዎች የማይገባ የገንዘብ ጥቅም ማግኛ እንዳይሆን ተገቢውን እርምጃ ይወሰዳሉ፡፡

ሠ/ እንደአግባቡ ከሁለት ወይም ከብዙ አገሮች ጋር በመስማማት የዚህን አንቀጽ ዓላማዎች ያራምዳሉ፤ ሕጻኑን በሌላ አገር ለጉዲፈቻ የመስጠቱ ተግባር በሚመለከታቸው ባለስልጣኖች ወይም አካላት መከናወኑን ለማረጋገጥ ጥረት ያደርጋሉ።

## አንቀጽ 22

1. ተዋዋይ አገሮችን ጥገኝነት በመጠየቅ ላይ ያለ ሕጻን፤ ወይም አግባብ ባለው ዓለም አቀፍ ወይም አገራዊ ሕግና ስነ ስርዓት መሰረት ስደተኛ መሆኑ የታወቀ ሕጻን ብቻውን ወይም ከወላጆቹ ወይም ከሌሎች ሰዎች ጋር ቢሆንም በዚህ ስምምነትና የተጠቀሱት አገሮች ተዋዋይ በሆኑባቸው ሌሎች ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶችና ሰብዓዊ ሰነዶች ውስጥ በተደነገጉት አግባብ ያላቸው መብቶች እንዲጠቀም ተገቢውን ሰብዓዊ ዕርዳታና ጥበቃ ማግኘቱን ለማረጋገጥ ተገቢ እርምጃዎችን ይወስዳሉ።
2. ለዚህም ዓላማ ተዋዋይ አገሮች አግባብ ሆኖ እንደታያቸው የተባበሩት መንግስታትና አገሮች

በመካከላቸው የፈጠሯቸው ስልጣን ያላቸው መንግስታዊ ድርጅቶች ወይም ለተባበሩት መንግስታት ትብብር የሚያደርጉ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እንዲህ ላለው ሕጻን ጥበቃና ዕርዳታ ለማድረግ እንዲሁም ማንኛውም ስደተኛ ሕጻን ከቤተሰቡ ጋር መልሶ ለማገናኘት የሚረዱ መረጃዎችን ለማሰባሰብና ወላጆቹን ወይም ሌሎች የቤተሰቡን አባላት ለማፈላለግ በሚያደርጉት ጥረት ይተባበራሉ፡፡ ወላጆቹን ወይም ሌሎች የቤተሰቡን አባሎች ለማግኘት ባልተቻለ ጊዜ በዚህ ስምምነት በተደነገገው መሰረት ሕጻኑ በማናቸውም ምክንያት ለጊዜው ወይም ለዘለቄታው ቤተሰቡን ላጣ ሌላ ሕጻን የሚደረግ ጥበቃ ይደረግለታል፡፡

## አንቀጽ 23

1. ተዋዋይ አገሮች የአዕምሮ ወይም የአካል ጉዳተኛ የሆነ ሕጻን ሰብአዊ ክብርን በሚያረጋግጥ፣ በራስ መተማመንን በሚያበረታታና በማሕበረሰቡ ውስጥ ንቁ ተሳትፎ እንዲኖረው በሚያመቻች ሁኔታ

የተሟላና ጥሩ ሕይወት መኖር እንደሚገባው ይገነዘባሉ፡፡

2. ተዋዋይ አገሮች የአዕምሮ ወይም የአካል ጉዳተኛ የሆነ ሕጻን ልዩ እንክብካቤ ለማግኘት ያለውን መብት አውቀው ይቀበላሉ፤ የሀብት አቅማቸው በፈቀደ መጠንም ማመልከቻ ሲቀርብ ለሕጻኑና እርሱን የመንከባከብ ኃላፊነት ላለባቸው ሰዎች ሕጻኑና ወላጆቹ ወይም ሕጻኑን የሚንከባከቡ ሰዎች ከሚገኙበት ሁኔታ ጋር ተስማሚ የሆነ ዕርዳታ እንዲሰጥ ያበረታታሉ፤ መሰጠቱንም ያረጋግጣሉ፡፡
3. የአካል ወይም የአዕምሮ ጉዳተኛ የሆነን ሕጻን ልዩ ፍላጎት በመገንዘብ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት የሚደረግ ዕርዳታ የወላጆችን ወይም የአሳዳሪዎችን የገንዘብ አቅም ከግምት ውስጥ በማስገባት በተቻለ መጠን በነጻ የሚሰጥና የሕጻኑን ችሎታ ለማዳበር፣ ከሕብረተሰቡ ጋር ተቀላቅሎ እንዲኖር ለማስቻልና ባህላዊና መንፈሳዊ እድገቱ የተሟላ እንዲሆን ለማድረግ አመቺ የሆነ ትምህርት፣ ስልጠና፣ የጤናና የተሐድሶ አገልግሎት፣ የስራ ስምሪት ዝግጅትና የመዝናኛ

አገልግሎት ማግኘቱን ለማረጋገጥ የታቀደ መሆን አለበት።

4. ተዋዋይ አገሮች የአካል ወይም የአዕምሮ ጉዳተኞች ሕጻናትን በሚመለከት በሕክምና መስክ በሽታን ስለመከላከል ዘዴዎች፣ ስለ ስነ ሕክምና፣ በስነ ልቦናና በተግባር ማከምን በተመለከተ የመረጃዎች ልውውጥን በዓለም አቀፍ የትብብር መንፈስ ያበረታታሉ። ይህም ተዋዋይ አገሮች በዚህ ዘርፍ ያላቸውን ችሎታና ሙያ ለማሻሻልና ልምድ ለማስፋት የሚያግዙ የተሐድሶ ዘዴዎችን፣ የትምህርትና የሞያ ስልጠና አገልግሎቶችን የሚመለከቱ መረጃዎችን ማሰራጨትንና ማግኘትን ይጨምራል። በዚህ ረገድ በመልማት ላይ ያሉ አገሮች ላሏቸው ፍላጎቶች ልዩ ግምት መሰጠት አለበት።

## አንቀጽ 24

1. ተዋዋይ አገሮች ሕጻናት ሊደረስበት የሚቻለው ከሁሉም የተሻለ የሕክምናና የተሐድሶ አገልግሎት ተጠቃሚ ለመሆን ያላቸውን መብት ይገነዘባሉ። ተዋዋይ አገሮች ማንኛውም ሕጻን እንዲህ ያሉትን

የጤና አገልግሎቶች የማግኘት መብቱን እንደማይነፈግ ለማረጋገጥ ጥረት ያደርጋሉ፡፡

2. ተዋዋይ አገሮች ይህን መብት ሙሉ በሙሉ ስራ ላይ ለማዋል ይተጋሉ በተለይም፡-

ሀ/ የጨቅላ ሕጻናትንና የሕጻናትን ሞት መጠን ለመቀነስ፤

ለ/ ለመሰረተ ጤና እንክብካቤ ዕድገት ቅድሚያ በመስጠት ለሁሉም ሕጻናት አስፈላጊ የሕክምናና የጤና አገልግሎቶች መሰጠቱን ለማረጋገጥ፤

ሐ/ የአካባቢ መበከል በጤና ላይ የሚያስከትለውን አደጋና ጠንቅ ከግምት ውስጥ በማስገባት በመሰረተ ጤና እንክብካቤ መዋቅር ጭምር ንፁህ የመጠጥ ውሃንና አልሚ ምግቦችን በማቅረብና እንዲሁም በቀላሉ የሚገኝ ቴክኖሎጂን መጠቀም ጨምሮ በሽታንና የተመጣጠነ ምግብ እጥረትን ለመከላከል፤

መ/ እናቶች ተገቢ ቅድመ ወሊድና ድህረ ወሊድ የጤና አገልግሎት ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ፤

ሠ/ ማንኛውም የሕብረተሰብ ክፍል በተለይ ወላጆችና ሕጻናት ስለሕጻናት ጤናና አመጋገብ፣ ጡት ማጥባት ስለሚሰጠው ጥቅም፤ ስለ ግልና

የአካባቢ ንጽሕና እንዲሁም ከአደጋ ስለ መከላከል መረጃ እንዲያገኙ፣ እንዲማሩና ባገኙት መሰረታዊ እውቀት እንዲጠቀሙ አስፈላጊው ድጋፍ መሰጠቱን ለማጋገጥ፤

ረ/ በሽታን የመከላከል እና የጤና አጠባበቅ ዘዴን ለማሻሻል፣ ለወላጆች የቤተሰብ ምጣኔ ትምህርትና አገልግሎት እንዲስፋፋ ለማድረግ፣ ተገቢ የሆኑ እርምጃዎችን ይወስዳሉ።

3. ተዋዋይ አገሮች ለሕጻናት ጤና ጠንቅ የሆኑ ባሕላዊ ልምዶች ለማስወገድ ተገቢና ውጤት ሊያስገኙ የሚችሉ ርምጃዎችን ይወስዳሉ።

4. ተዋዋይ አገሮች በዚህ አንቀጽ የተመለከተውን መብት ሙሉ በሙሉ ደረጃ በደረጃ ስራ ላይ ለማዋል እንዲቻል ዓለም አቀፍ ትብብርን ያበረታታሉ። በዚህ ረገድ በመልማት ላይ ላሉ አገሮች ፍላጎቶች ልዩ ግምት ይሰጣል።

## አንቀጽ 25

ተዋዋይ አገሮች የአካል ወይም የአዕምሮ እንክብካቤ፣ ጥበቃ ወይም ሕክምና እንዲደረግለት

ስልጣን ባለው አካል ውሳኔ በአንድ በተወሰነ ቦታ እንዲቀመጥ የተደረገ ሕጻን የአያያዙ ሁኔታ እና በተወሰነ ቦታ እንዲቀመጥ የተደረገበት ሁኔታዎች በየጊዜው እንዲገመገሙለት ለማድረግ ያለውን መብት ያውቃሉ።

## አንቀጽ 26

1. ተዋዋይ አገሮች እያንዳንዱ ሕጻን ማሕበራዊ መድህንን ጨምሮ በማሕበራዊ ዋስትና ለመጠቀም ያለውን መብት ያውቃሉ፤ ይህን መብት ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ለማድረግ አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎችንም በየአገራቸው ሕግ መሰረት ይወስዳሉ።
2. እነዚህ ጥቅሞች መሰጠት ያለባቸው እንደአግባብነቱ የሕጻኑንና ለሕጻኑ ቀለብ የመስጠት ኃላፊነት ያለባቸውን ሰዎች ሀብትና ሁኔታ እንዲሁም ጥቅሙ እንዲሰጠው በሕጻኑ ወይም በእርሱ ስም ለቀረበው ማመልከቻ አግባብነት ያላቸውን ሌሎች ጉዳዮች ግምት ውስጥ በማስገባት ነው።

# አንቀጽ 27

1. ተዋዋይ አገሮች እያንዳንዱ ሕጻን ለአካላዊ፣ አዕምሯዊ፣ መንፈሳዊ፣ ሕሊናዊና ማሕበራዊ ዕድገቱ ተስማሚ የሆነ የኑሮ ደረጃ የማግኘት መብት እንዳለው ይገነዘባሉ።
2. ወላጆች ወይም ለሕጻኑ አስተዳደግ ሃላፊነት ያለባቸው ሌሎች ሰዎች ችሎታቸውና የገንዘብ አቅማቸው በሚፈቅደው መጠን ለዕድገቱ አስፈላጊ የሆኑ የኑሮ ሁኔታዎች የማመቻቸት የመጀመሪያ ሃላፊነት አለባቸው።
3. ወላጆችና ለሕጻኑ ሃላፊነት ያለባቸው ሌሎች ሰዎች ይህን መብት ስራ ላይ እንዲያውሉ ለማገዝ ተዋዋይ አገሮች በየአገሮቻቸው ሁኔታዎችና በአቅማቸው መሰረት ተገቢውን እርምጃ ይወስዳሉ፣ በተለይ በምግብ፣ በልብስና በመጠለያ ረገድ ፍላጎት ሲኖር የማቴሪያል ዕርዳታ ይሰጣሉ፣ የዕርዳታ ፕሮግራሞችንም ያዘጋጃሉ።
4. በተዋዋዩ አገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር ካሉት ወላጆቹ ወይም ለሕጻኑ ገንዘብ የመስጠት ሃላፊነት ካለባቸው ሌሎች ሰዎች ለሕጻኑ ቀለብ ለማስገኘት

ተዋዋይ አገሮች ማናቸውንም ተገቢ እርምጃ ይወስዳሉ፡፡ በተለይ ለሕጻኑ ማሳደጊያ ገንዘብ የመስጠት ሃላፊነት ያለበት ሰው ሕጻኑ ከሚገኝበት አገር ውጭ የሚኖር ከሆነ አባል አገሮች ለዚህ ተግባር የሚያገለግሉ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ማድረግን ያበረታታሉ፣ ሌሎችም አግባብ ያላቸውን ነገሮች ሁሉ ያመቻቻሉ፡፡

## አንቀጽ 28

1. ተዋዋይ አገሮች የሕጻናትን የመማር መብት ያውቃሉ፡፡ ይህንን መብት ደረጃ በደረጃና ለሁሉም እኩል ዕድል መስጠት በሚለው መርህ ላይ በመመስረት ስራ ላይ ለማዋል በተለይ፡-
   ሀ/ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ግዴታ እንዲሆንና ለሁሉም በነጻ እንዲዳረስ ያደርጋሉ፡፡
   ለ/ አጠቃላይ ትምህርትንና የሙያ ትምህርትን ጨምሮ ልዩ ልዩ ዓይነት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቶች እንዲስፋፉ ያበረታታሉ፤ እነዚህ የትምህርት ዓይነቶች ለእያንዳንዱ ሕጻን እንዲዳረሱ ያደርጋሉ፤ በተጨማሪም ለችግረኛ

ተማሪዎች ነጻ ትምህርት መስጠትን የገንዘብ እርዳታ ማድረግን የመሳሰሉ ተገቢ እርምጃዎችን ይወስዳሉ፤

ሐ/ በማናቸውም ተገቢ መንገድ ችሎታን መሰረት በማድረግ የከፍተኛ ትምህርት ለሁሉም እንዲዳረስ ያደርጋሉ፤

መ/ የትምህርትና የሙያ መረጃዎችና መመሪያዎች ለሁሉም ሕጻናት እንዲዳረሱ ያደርጋሉ፤

ሠ/ ሕጻናት ሳይስተጓጐሉ በትምህርት ገበታ ላይ እንዲገኙና ትምህርት የሚያቋርጡ ተማሪዎች ቁጥር እንዲቀንስ ለማድረግ ርምጃዎችን ይወስዳሉ::

2. ተዋዋይ አገሮች የትምህርት ቤት ስነስርዓት አጠባበቅ ከሕጻናት ሰብዓዊ ክብርና ከዚህ ስምምነት ጋር በተጣጣመ አኳኋን መመራቱን ለማረጋገጥ ማናቸውንም ተገቢ እርምጃ ይወስዳሉ::

3. ተዋዋይ አገሮች ትምህርትን በሚመለከቱ ጉዳዮች በተለይም ከዓለም ድንቁርና እና መሃይምነትን ጨርሶ ለማጥፋት አስተዋጽኦ ለማድረግ ሳይንሳዊና፣ ቴክኒካዊ ዕውቀትን ተደራሽ ለማድረግና ዘመናዊ የማስተማሪያ ዘዴዎች እንዲዳረሱ በማመቻቸት

ረገድ ዓለም አቀፍ ትብብር እንዲኖር ያበረታታሉ፡፡ በዚህ ረገድ በመልማት ላይ ያሉ አገሮች ያሏቸው ፍላጎቶች ልዩ ግምት ይሰጣቸዋል፡፡

## አንቀጽ 29

1. ተዋዋይ አገሮች ለሕጻናት የሚሰጠው ትምህርት ወደሚከተሉት አቅጣጫዎች እንዲያተኩር ተስማምተዋል፡፡

   ሀ/ የሕጻኑን ስብእና፣ ተሰጥኦ፣ የአዕምሮና የአካል ችሎታ በተሟላ አኳኋን ለማዳበር፤

   ለ/ ሰብዓዊ መብቶችንና መሰረታዊ ነፃነቶችን፣ እንዲሁም በተባበሩት መንግስታት ቻርተር ውስጥ የተደነገጉትን መርሆዎች ማክበርን ለማረጋገጥ፤

   ሐ/ ወላጆችን፣ የራስን ባሕል፣ ቋንቋ፣ ወግና ስርዓት፣ የሚኖሩበትን ወይም የመጡበትን አገር ብሔራዊ ወጎችንና ስርዓቶችን እንዲሁም ከራሳቸው የሚለዩ ስልጣኔዎችን የማክበር ዝንባሌን ለማዳበር፣

መ/ ሁሉም ሕዝቦች፣ ጎሳዎች፣ ብሔሮችና የሃይማኖት ቡድኖች፣ እንዲሁም የአገሩ ቀደምት ነዋሪዎች፣ ተወላጆች በሚኖሩበት ነጻ ሕብረተሰብ ውስጥ በመግባባት፣ በሰላም፣ በመቻቻል፣ የጾታ እኩልነትን በጠበቀና በወዳጅነት መንፈስ መኖር እንዲችሉ ሕጻናትን ኃላፊነት ላለበት ሕይወት ለማዘጋጀት፣

ሠ/ የተፈጥሮ አካባቢን የማክበር ዝንባሌን ለማዳበር።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገጉት መርሆዎችና አገሩ የትምህርት አሰጣጥን በሚመለከት በየጊዜው የሚያወጣቸው ደረጃዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ የዚህ አንቀጽ ወይም የአንቀጽ 28 ማንኛውም ክፍል ግለሰቦች ወይም የተለያዩ አካላት ወይም የትምህርት ተቋማት ለማቋቋምና ለመምራት ባላቸው መብት ውስጥ ጣልቃ ለመግባት እንደሚያስችል ተደርጎ አይተረጎምም።

## አንቀጽ 30

የሕዝብ ቁጥራቸው አናሳ የሆኑ ጎሳዎች፣ የሃይማኖት ወይም የቋንቋ ቡድኖች ወይም የአገሩ

ቀደምት ነዋሪ ሕዝቦች ተወላጆች ባሉባቸው አገሮች የእንዲህ ዓይነቱ በቁጥር አናሳ የሆነ ቡድን ወገን የሆነ ወይም የአገሩ ቀደምት ነዋሪ ሕዝቦች ተወላጅ የሆነ ሕጻን ከራሱ ቡድን አባላት ጋር በሕብረት የራሱን ባሕል ለመከተል፣ ሃይማኖቱን ለመግለጽና ስርዓቱን ለማክበር፣ እንዲሁም በራሱ ቋንቋ ለመጠቀም ያለው መብት አይነፈግም።

## አንቀጽ 31

1. ተዋዋይ አገሮች ሕጻናት ለማረፍና ለመዝናናት፣ ለዕድሜያቸው ተስማሚ በሆነ ጨዋታና የመዝናኛ እንቅስቃሴዎች ለመካፈል፣ በባሕልና ስነ ጥበብ መስክ በነጻነት ለመሳተፍ ያላቸውን መብት ያውቃሉ።
2. ተዋዋይ አገሮች ሕጻናት በባሕልና ስነ ጥበብ መስክ ለመሳተፍ ያላቸውን መብት በማክበርና በመደገፍ በባሕል፣ በስነ ጥበብና በመዝናኛ ፕሮግራሞች ሙሉ በሙሉ የመሳተፍ ዕድል ለሁሉም በእኩልነትና ተስማሚ በሆነ አኳኋን እንዲዳረስ ያበረታታሉ።

## አንቀጽ 32

1. ተዋዋይ አገሮች ሕጻኑ ከኢኮኖሚ ብዝበዛና ለአደጋ ከሚያጋልጥ፣ ወይም የሕጻኑን ትምህርት ከሚያደናቅፍ፣ ወይም ለሕጻኑ ጤና፣ ወይም ለአካላዊ፣ አዕምሯዊ፣ መንፈሳዊ፣ ሞራላዊ ወይም ማሕበራዊ ዕድገቱ ጎጂ ከሆነ ስራ ጥበቃ የማግኘት መብት ያለው መሆኑን ያውቃሉ፡፡
2. ተዋዋይ አገሮች ይህ አንቀጽ ስራ ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ ሕግ ያወጣሉ፣ የአስተዳደር፣ የማሕበራዊና ትምህርት ነክ ርምጃዎችን ይወስዳሉ፡፡ ለዚህ ዓላማና በሌሎች ዓለም አቀፍ ሰነዶች የተደነገጉትን አግባብ ያላቸው ድንጋጌዎች ግምት ውስጥ በማስገባት ተዋዋይ አገሮች በተለይ፡-
   ሀ/ ዝቅተኛ የቅጥር ዕድሜን ወይም ዕድሜዎችን ይወስናሉ፡
   ለ/ የስራ ሰዓትንና የቅጥር ሁኔታዎችን የሚመለከት ተገቢ ደንብ ያወጣሉ፤
   ሐ/ ይህ አንቀጽ በሚገባ በስራ ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ ተገቢ ቅጣቶችን ወይም ሌሎች እርምጃዎችን ይደነግጋሉ፡፡

## አንቀጽ 33

ተዋዋይ አገሮች አግባብ ባላቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ሱስ የሚያስይዙ ወይም አዕምሮን የሚያደነዝዙ ተብለው የሚታወቁ ነገሮች ሕፃናት ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ እንዳይጠቀሙ ለማድረግ፣ እንዲሁም ሰዎች ሕጻናትን እነዚህን ነገሮች በማምረት ወይም በማሰራጨት ተግባር ላይ እንዳያሰማሩ ለመከልከል የሕግ፣ የአስተዳደር፣ የማሕበራዊና የትምህርት እርምጃዎችን ጨምሮ ማንኛውንም ተገቢ ርምጃ ይወስዳሉ፡፡

## አንቀጽ 34

ተዋዋይ አገሮች በሕጻናት ላይ ማንኛውም ዓይነት የወሲብ ብዝበዛና በደል እንዳይፈጸም ጥበቃ ለማድረግ ተስማምተዋል፡፡ እነዚህን ዓላማዎች ለማሳካት ሲባል ተዋዋይ አገሮች በተለይ፡-

ሀ/ ሕጻናት ሕገ ወጥ የወሲብ ግንኙነት እንዲፈጽሙ ማነሳሳትንና ወይም ማስገደድን፤

ለ/ ሕጻናትን በሴትኛ አዳሪነት ወይም በሌላ ሕገ ወጥ የወሲብ ግንኙነት ተግባር ላይ አሰማርቶ መበዝበዝን፤

ሐ/ ሕጻናትን በአስነዋሪ(ፖርኖግራፊ) ትርዒቶችና ማቴርያሎች በመጠቀም መበዝበዝን ለመከላከል ማናቸውንም አግባብ ያላቸው አገራዊና የሁለትዮሽ ወይም ከዚህ በላይ በሆኑ አገሮች ትብብር ላይ የተመሰረቱ ርምጃዎችን ይወስዳሉ።

## አንቀጽ 35

ተዋዋይ አገሮች ለማንኛውም ዓላማ ወይም በማንኛውም መልክ ሕጻናትን የመጥለፍ፣ የመሸጥ፣ ወይም በሕጻናት የመነገድ ተግባርን ለመከላከል ማንኛውንም አግባብ ያላቸው አገራዊና የሁለትዮሽ ወይም በብዙ አገሮች ትብብር ላይ የተመሰረቱ እርምጃዎችን ይወስዳሉ።

## አንቀጽ 36

ተዋዋይ አገሮች ሕጻናትን ለደኅንነታቸው ጠንቅ ከሆኑ ሌሎች ማናቸውንም የብዝበዛ ዓይነቶች ይጠብቃሉ።

## አንቀጽ 37

ተዋዋይ አገሮች የሚከተሉት መከበራቸውን ያረጋግጣሉ፡-

ሀ/ ማንኛውም ሕጻን በሚያሰቃይ ወይም ጭካኔ በተሞላበት፣ ኢ-ሰብዓዊ በሆነ ወይም ሰብዓዊ ክብርን በሚያዋርድ ቅጣት አይቀጣም፡፡ ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ሰዎች ለፈጸሙዋቸው ወንጀሎች የሞት ወይም የመፈታት ዕድል የሌለው የዕድሜ ልክ እስራት ቅጣት አይወሰንም፤

ለ/ ማንኛውም ሕጻን በሕገ ወጥ ወይም በዘፈቀደ አሰራር ነጻነቱን አይገፈፍም፡፡ አንድ ሕጻን የሚያዘው በቁጥጥር ሥር የሚውለውና የሚታሰረው በሕግ መሰረት ነው፤ እስራቱም እንደመጨረሻ አማራጭ ብቻ ተፈጻሚ የሚሆንና ተገቢ ከሆኑት አማራጮች ከሁሉም ለሚያጥረው ጊዜ የሚቆይ መሆን አለበት፤

ሐ/ ነጻነቱን እንዲያጣ የተደረገ ማንኛውም ሕጻን ዕድሜው የሚጠይቃቸውን ፍላጎቶች ግምት ውስጥ በማስገባት ለሰብዓዊ ፍጡር ሊሰጥ በሚገባው ክብርና ርህራሄ መያዝ አለበት፡፡ በተለይም ከአዋቂዎች ቢለይ ለሕጻኑ የማይበጅ ካልሆነ በቀር፣ ነጻነቱን

እንዲያጣ የተደረገ ማንኛውም ሕጻን ከአዋቂዎች እንዲለይ ይደረጋል፤ ልዩ ሁኔታዎች ካላጋጠሙ በቀርም በመልዕክት ልውውጥና በጉብኝቶች አማካይነት ከቤተሰቦቹ ጋር ግንኙነት የማድረግ መብቱ ይጠበቃል፤

መ/ ማንኛውም ነጻነቱን እንዲያጣ የተደረገ ሕጻን የሕግና ሌላ አግባብ ያለው ዕርዳታ በአፋጣኝ የማግኘትና ፍርድ ቤት ወይም ሌላ ስልጣን ካለው ነጻና ገለልተኛ ከሆነ ባለሥልጣን ዘንድ ቀርቦ ነጻነቱን ያጣበትን ጉዳይ ሕጋዊነት የመጠየቅና በጉዳዩ ላይም ፈጣን ውሳኔ የማግኘት መብት አለው፡፡

## አንቀጽ 38

1. ተዋዋይ አገሮች በጦርነት ጊዜ በነሱ ላይ ተፈፃሚነትና አግባብነት ያላቸውን ሕፃናትን የሚመለከቱ የዓለም አቀፍ የሰብዓዊ አያያዝ ሕጎችና ደንቦችን ያከብራሉ፤ መከበራቸውንም ያረጋግጣሉ፡፡

2. ተዋዋይ አገሮች ዕድሚያቸው ከ15 ዓመት በታች የሆኑ ሰዎች በጦርነት ቀጥታ ተካፋይ እንዳይሆኑ የሚቻለውን እርምጃ ሁሉ ይወስዳሉ።

3. ተዋዋይ አገሮች ዕድሜያቸው 15 ዓመት ያልሞላ ሰዎችን ለጦር ኃይሎቻቸው ከመመልመል ይታቀባሉ። ዕድሜያቸው በ15ና በ18 ዓመት መካከል ያሉትን በሚመለምሉበት ጊዜም በዕድሜያቸው ከፍ ላሉት ቅድሚያ ለመስጠት ጥረት ያደርጋሉ።

4. ተዋዋይ አገሮች በጦርነት ጊዜ የሲቪሉን ሕዝብ ደህንነት ለመጠበቅ በዓለም አቀፍ የሰብዓዊ አያያዝ ሕግ ባለባቸው ግዴታ መሰረት፣ ጦርነት ችግር ለፈጠረባቸው ሕጻናት ጥበቃና ጥንቃቄ መደረጉን ለማረጋገጥ የተቻለውን እርምጃ ሁሉ ይወስዳሉ።

## አንቀጽ 39

ተዋዋይ አገሮች የእንክብካቤ እጦት፣ የብዝበዛ፣ የመጉላላት፣ የስቃይ ወይም የማናቸውም ዓይነት ጭካኔ የተሞላበት፣ ኢሰብዓዊ የሆነ፣ ወይም ሰብዓዊ ክብርን የሚያዋርድ አያያዝ፣ ቅጣት ወይም የጦርነት ሰለባ የሆነ

ሕጻን በአካልና በሥነ ልቦና ከደረሰበት ጉዳት እንዲያገግምና ከህብረተሰቡ ጋር እንዲቀላቀል ለማድረግ ተገቢውን እርምጃ ይወስዳሉ። በዚህ ዓይነት ከጉዳቱ እንዲያገግም የማድረጉና ወደ ሕብረተሰቡ የመቀላቀሉ ጉዳይ ለሕፃኑ ጤንነት ተስማሚና ለራስ ዋጋና ክብር የመስጠት ስሜትን ለማዳበር አመቺ በሆነ አካባቢ ይከናወናል።

## አንቀጽ 40

1. ተዋዋይ አገሮች የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ጥሷል የተባለ ፣ ጥሷል ተብሎ የተከሰሰ ወይም መጣሱ የታወቀ ማንኛውም ሕጻን ስለራሱ ክብርና ዋጋ ሊኖረው ከሚገባው ስሜት ጋር ተስማሚ የሆነ፣ ለሌሎች ሰዎች ሰብዓዊ መብቶችና መሰረታዊ ነጻነቶች ክብር መስጠትን የሚያጠናክር፣ ዕድሜውን እንዲሁም ከሕብረተሰቡ ጋር እንዲቀላቀልና በሕብረተሰብ ውስጥ ገንቢ ሚና እንዲኖረው እገዛ የማድረግን አስፈላጊነት ግምት ውስጥ ያስገባ አያያዝ የማግኘት መብቱን ያውቃሉ።

2. ለዚህ ዓላማ ከግብ መድረስ ተዋዋይ አገሮች አግባብ ያላቸውን የዓለም አቀፍ ሰነዶችን ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ በተለይ የሚከተሉትን ያረጋግጣሉ፡-

ሀ/ ማንኛውም ሕጻን አንድ ድርጊት በፈፀመ ጊዜ ድርጊቱን መፈፀሙ ወይም አለመፈፀሙ በአገራዊ ወይም በዓለም አቀፍ ሕግ ያልተከለከለ ከነበረ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ጥሷል ተብሎ የማይከሰስ ወይም እንደጣሰ የማይቆጠር መሆኑን፤

ለ/ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ጥሷል የተባለ ወይም በመጣሱ የተከሰሰ ማንኛውም ሕጻን ቢያንስ የሚተሉት ዋስትናዎች ይኖሩታል፡፡

1. በሕግ መሰረት ጥፋተኛነቱ እስኪረጋገጥ ድረስ ንጹህ ሆኖ የመገመት፤
2. የቀረበበትን ክስ በፍጥነትና በቀጥታ፣ አስፈላጊ ሲሆንም በወላጆቹ ወይም በሕጋዊ አሳዳሪዎቹ በኩል የማወቅ፣ እንዲሁም ለክሱ መከላከያ አዘጋጅቶ ለማቅረብ የሕግ ወይም አግባብነት ያለው ሌላ ዕርዳታ የማግኘት፤

3. ሥልጣን ባለውና ነጻና ገለልተኛ በሆነ የዳኝነት አካል በሕግ መሰረት ጉዳዩ ሳይዘገይና በትክክል እንዲታይለትና እንዲወሰንለት፤ ጉዳዩ በሚሰማበት ጊዜም የሕግ ወይም አግባብ ያለው ሌላ እርዳታ የማግኘት፣ እንዲሁም በተለይ ዕድሜውንና ያለበትን ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት ለሕጻኑ የማይጠቅም ሆኖ ካልተገኘ በቀር ወላጆቹ ወይም የሕግ እንደራሴዎቹ እንዲገኙለት፤
4. የምስክርነት ቃል እንዲሰጥ ወይም ጥፋተኛነቱን እንዲያምን ያለመገደድ፤ የቀረቡበትን ምስክሮች የመጠየቅ ወይም ጥያቄዎች እንዲቀርቡላቸው የማድረግና እርሱ የጠራቸው ምስክሮችም ከሌሎች እኩል እንዲሰሙለትና እንዲጠየቁለት የማድረግ፤
5. የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉን ጥሷል ተብሎ ከተፈረደበት ይህ ፍርድና በፍርዱ መሰረት የተወሰዱበት እርምጃዎች ሁሉ ሥልጣን ባለውና ነጻና ገለልገኛ በሆነ

የበላይ ባለሥልጣን ወይም የዳኝነት አካል በሕግ መሰረት እንዲመረመርለት የማድረግ፤

6. የሚሰራበትን ቋንቋ ለመረዳት ወይም ለመናገር የማይችል ከሆነ የአስተርጓሚ ዕርዳታ በነጻ የማግኘት፤
7. ጉዳዩ በሚታይበት በየትኛውም ደረጃ የግል ነጻነቱ እንዲከበርለት ማድረግ፤

3. ተዋዋይ አገሮች የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ጥሰዋል የተባሉ ጥሰዋል ተብለው የተከሰሱ ወይም መጣሳቸው የታወቀ ሕጻናትን የሚመለከቱ ሕጎች፣ ሥነ ሥርዓቶች፣ መሥሪያ ቤቶችና ተቋሞች እንዲኖሩ ለማድረግ በተለይም

ሀ/ ሕጻናት የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የመጣስ ችሎታ እንደሌላቸው ተደርገው የሚቆጠሩበትን ዝቅተኛ ዕድሜ ለመወሰን፤

ለ/ ተገቢና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሰብዓዊ መብቶችና የሕግ ጥበቃዎች እስከተከበሩ ድረስ፣ እንዲህ የመሰሉ ሕጻናትን በተመለከተ ከፍርድ ሂደት ውጭ እርምጃዎች የሚወሰዱበትን ሥርዓት ለመዘርጋት፣

4. የተለያዩ እንክብካቤዎች፣ የአመራርና የቁጥጥር ትዕዛዞች፣ የምክር አገልግሎቶች፣ አመክሮ፣ የማሳደጊያ ቤት እንክብካቤ፣ ትምህርትና የሞያ ሥልጠና ፕሮግራሞች፣ እንዲሁም የተቋሞች እንክብካቤን የሚተኩ ሌሎች ልዩ ልዩ አማራጮች እንዲኖሩ ያደርጋሉ፣ እነዚህም ለሕጻናት ደሕንነት አስተማማኝ የሆኑና ከሚገኙበት ሁኔታና ከወንጀሉ ጋር ተመጣጣኝ መሆን አለባቸው።

## አንቀጽ 41

ይህ ስምምነት የሕጻናትን መብት ስራ ላይ ለማዋል ይበልጥ አመቺ የሆኑና (ሀ) ስምምነቱን በተቀበለ አገር ሕግ፣ ወይም (ለ) በዚያ አገር ላይ ተፈጻሚነት ባለው ዓለም አቀፍ ሕግ የተገለጹትን ድንጋጌዎች የሚነካ አይሆንም።

# ክፍል ሁለት

## አንቀጽ 42

ተዋዋይ አገሮች የስምምነቱ መርሆችና ድንጋጌዎች በአዋቂዎችና በሕጻናት ዘንድ በሰፊው እንዲታወቁ ለማድረግ ተገቢውን ርምጃ ሁሉ ይወስዳሉ፡፡

## አንቀጽ 43

1. ተዋዋይ አገሮች በስምምነቱ የገቧቸውን ግዴታዎች ለመፈጸም ያደረጉትን እርምጃ ለመገምገም የሚከተሉትን ተግባሮች የሚያከናውን አንድ የሕጻናት መብቶች ኮሚቴ ይቋቋማል፡፡
2. ኮሚቴው ከፍተኛ ሥነ ምግባርና በስምምነቱ በተሸፈኑት ጉዳዮች ላይ የታወቀ ችሎታ ያላቸውን አስር ኤክስፐርቶች በአባልነት የሚይዝ ይሆናል፡፡ የኮሚቴው አባሎች ከተዋዋይ አገሮች ዜጎች መካከል በተዋዋዮቹ አገሮች ተመርጠው በግላቸው ያገለግላሉ፡፡ በምርጫው ወቅት ፍትሐዊ የሆነ ጂኦግራፊያዊ ስብጥር እንዲኖርና የታወቁ የሕግ ሥርዓቶች እንዲወከሉ ትኩረት ይሰጣል፡፡

3. የኮሚቴው አባሎች በተዋዋይ አገሮች ከቀረቡት ዕጩዎች መካከል በምስጢራዊ የድምጽ አሰጣጥ ሥርዓት ይመረጣሉ፡፡ እያንዳንዱ አገር ከዜጎች መካከል ለምርጫው አንድ እጩ ማቅረብ ይችላል፡፡
4. የኮሚቴው አባሎች የመጀመሪያ ምርጫ ይህ ስምምነት በሥራ ላይ ከዋለበት ቀን አንስቶ ከስድስት ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የሚፈፀም ይሆናል፡፡ እያንዳንዱ ምርጫ ከሚደረግበት ቀን ቢያንስ አራት ወር አስቀድሞ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ጸሐፊ ለተዋዋይ አገሮች እጩዎቻቸውን በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ እንዲያሳውቁ በደብዳቤ ይጠይቃል፡፡ በማስከተልም ዋና ጸሐፊው የሁሉንም እጩዎች ስም ዝርዝር በፊደል ቅደም ተከተልና ከየትኛው አገር በእጩነት እንደቀረቡ አዘጋጅቶ ለተዋዋይ አገሮች እንዲደርሳቸው ያደርጋል፡፡
5. ምርጫዎቹ የሚደረጉት በተባበሩት መንግሥታት ዋና ጸሐፊ በሚጠሩና ተዋዋይ አገሮች በድርጅቱ ዋና ጽ/ቤት በሚያደርጓቸው ስብሰባዎች ነው፡፡ ከተዋዋይ አገሮች ሁለት ሦስተኛው በስብሰባዎቹ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ሲሆን፣ በስብሰባዎቹ

ተገኝተው ድምጽ ከሰጡት ተዋዋይ አገሮች ተወካዮች ከግማሽ በላይና በከፍተኛ ድምጽ የተደገፉት ሰዎች የኮሚቴው አባሎች ሆነው ይመረጣሉ፡፡

6. የኮሚቴው አባሎች ለአራት ዓመታት የሥራ ዘመን ይመረጣሉ፡፡ እንደገና በእጩነት ከቀረቡም ዳግመኛ ለመመረጥ ሊወዳደሩ ይችላሉ፡፡ የአምስቱ የኮሚቴው አባሎች የሥራ ዘመን የመጀመሪያው ምርጫ በተደረገ በሁለተኛው ዓመት መጨረሻ ላይ ይፈጸማል፡፡ የመጀመሪያው ምርጫ እንደተደረገ ወዲያውኑ የስብሰባው ሊቀመንበር በሚያወጣው ዕጣ የእነዚህ አምስት አባላት ስም ይለያል፡፡
7. የኮሚቴው የማጽደቅ ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ፣ አንድ የኮሚቴ አባል የሞተ ወይም በራሱ ፈቃድ ሥራውን የለቀቀ ወይም በማናቸውም ምክንያት የኮሚቴውን ሥራ ማከናወን የማይችል መሆኑን የገለጸ እንደሆነ፣ ለቀረው የሥራ ዘመን የሚያገለግል ምትክ ኤክስፐርት በእጩነት ያቀረበው አገር ከዜጎቹ መካከል መርጦ ይሾማል፡፡
8. ኮሚቴው የራሱን የሥነ ሥርዓት ደንቦች ያወጣል፡፡

9. ኮሚቴው የራሱን ሹማምንት ለሁለት ዓመታት የሥራ ጊዜ ይመርጣል።

10. የኮሚቴው ስብሰባዎች በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና መሥሪያ ቤት ወይም ኮሚቴው በሚወስነው ሌላ ተስማሚ ቦታ ይደረጋሉ። ኮሚቴው በዓመት አንዴ ይሰበሰባል። የኮሚቴው ስብሰባዎች የሚቆዩበት ጊዜ ተዋዋይ አገሮች በሚያደርጉት ስብሰባ ይወሰናል፣ እንደ አስፈላጊነቱም ይሻሻላል፣ በጠቅላላው ጉባዔም እንዲጸድቅ ይደረጋል።

11. የተባበሩት መንግሥታት ዋና ጸሐፊ ኮሚቴው በዚህ ስምምነት የተመለከቱ ሥራዎቹን በብቃት ለማከናወን የሚያስችለውን አስፈላጊ የሰው ኃይልና ዝግጅት ያሟላል።

12. በጠቅላላው ጉባዔ ሲፀድቅና ጉባዔው በሚወስናቸው ሁኔታዎች መሰረት በዚህ ስምምነት የተቋቋመው ኮሚቴ አባላት ከተባበሩት መንግሥታት የአገልግሎት ክፍያ ይቀበላሉ።

## አንቀጽ 44

1. ተዋዋይ አገሮች በስምምነቱ የተደነገጉትን መብቶች ሥራ ላይ ለማዋል ስለወሰዷቸው ርምጃዎችና በመብቶቹ በመጠቀም ረገድ ስለታየው መሻሻል ቀጥሎ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ በተባበሩት መንግሥታት ዋና ጸሐፊ በኩል ለኮሚቴው ዘገባ ለማቅረብ ተስማምተዋል፡፡
   ሀ/ ጉዳዩ በሚመለከተው አገር ስምምነቱ ሥራ ላይ ከዋለበት ቀን አንስቶ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ፤
   ለ/ ከዚያ በኋላ በየአምስት ዓመቱ፤
2. በዚህ አንቀጽ መሰረት የሚቀርቡ ዘገባዎች በዚህ ስምምነት የተደነገጉትን ግዴታዎች አፈጻጸም በሚመለከት ያጋጠሙትን ሁኔታዎችና ችግሮች ካሉ መጥቀስ ይኖርባቸዋል፡፡ ዘገባዎቹ ጉዳዩ በሚመለከተው አገር ውስጥ ስምምነቱ ስላለው ተፈጻሚነት ኮሚቴው አጠቃላይ ግንዛቤ እንዲኖረው በቂ መረጃዎች መያዝ አለባቸው፡፡
3. የመጀመሪያውን ዝርዝር ዘገባ ለኮሚቴው ያቀረበ አገር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) መሰረት

የሚያቀርባቸውን ተከታይ ዘገባዎች በሚያቀርብበት ጊዜ ቀደም ሲል ያቀረባቸውን መሰረታዊ መረጃዎች መድገም አያስፈልገውም፡፡

4. ኮሚቴው ለስምምነቱ ተፈጻሚነት አግባብነት ያላቸውን ተጨማሪ መረጃዎች ከተዋዋይ አገሮች መጠየቅ ይችላል፡፡
5. ኮሚቴው ስለስራው እንቅስቃሴ በተባበሩት መንግሥታት የኢኮኖሚና የማሕበራዊ ምክር ቤት በኩል ለጠቅላላ ጉባዔው በየሁለት ዓመቱ ሪፖርት ያቀርባል፡፡
6. ተዋዋይ አገሮች ዘገባዎቻቸውን በአገሮቻቸው ላሉ ሕዝቦች በሰፊው እንዲዳረሱ ያደርጋሉ፡፡

## አንቀጽ 45

ስምምነቱ በሚገባ ሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግና በስምምነቱ በተሸፈነው መስክ ዓለም አቀፍ ትብብርን ለማበረታታት፡-

ሀ/ ልዩ የሥራ ኃላፊነት የተሰጣቸው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅቶች፣ የተባበሩት መንግሥታት የሕጻናት መርጃ ድርጅትና ሌሎች የተባበሩት

መንግሥታት ድርጅት አካላት የዚህን ስምምነት ድንጋጌዎች ሥራ ላይ ለማዋል በሚደረግ ውይይት ላይ የተሰጣቸውን የሥራ ኃላፊነት በሚመለከት የመወከል መብት ይኖራቸዋል:: ኮሚቴው ልዩ ተልእኮ የተሰጣቸውን የተባበሩት መንግሥታት አካላት፣ የተባበሩት መንግሥታትን የሕጻናት መርጃ ድርጅትና ሌሎች አግባብ አላቸው ብሎ የሚገምታቸውን የድርጅቱን አካላት በየኃላፊነት ድርሻው ስምምነቱን ሥራ ላይ በማዋል ረገድ የባለሞያ ምክር እንዲሰጡት መጋበዝ ይችላል:: ኮሚቴው ልዩ ተልእኮ የተሰጣቸውን የተባበሩት መንግሠታት ድርጅቶች፣ የተባበሩት መንግሥታት የሕጻናት መርጃ ድርጅትና ሌሎች የድርጅቱ አካላት በየሥራ ድርሻቸው ስለ ስምምነቱ ተፈጻሚነት ዘገባዎች እንዲያቀርቡ መጠየቅ ይችላል::

ለ/ ኮሚቴው ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው አባል አገሮች የቴክኒክ ምክር ወይም ዕርዳታ እንዲሰጣቸው የሚያቀርቧቸውን ማናቸውንም ጥያቄዎች የራሱን አስተያየት በማከል ልዩ ተልእኮ ለተሰጣቸው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅቶች፣ ለተባበሩት

መንግስሥታት የሕጻናት መርጃ ድርጅትና ለሌሎች አግባብ ላላቸው የተባበሩት መንግሥታት አካላት ያስተላልፋል፡፡

ሐ/ ኮሚቴው የሕጻናትን መብቶች በሚመለከቱ የተወሰኑ ጉዳዮች ላይ በኮሚቴው ስም ጥናት እንዲደረግ ጠቅላላ ጉባዔው የተባበሩት መንግሥታት ዋና ጸሐፊን እንዲጠይቅ የውሳኔ ሐሳብ ማቅረብ ይችላል፡፡

መ/ ኮሚቴው በዚህ ስምምነት አንቀጽ 44 እና 45 መሰረት በሚደርሱት መረጃዎች ላይ በመመርኮዝ አስተያየቶችንና አጠቃላይ የውሳኔ ሐሳቦችን ማቅረብ ይችላል፡፡ እንዲህ ያሉት አስተያየቶችና አጠቃላይ የውሳኔ ሃሳቦች ለማንኛውም ለሚመለከተው ተዋዋይ አገር ይተላለፋሉ፣ ለጠቅላላ ጉባዔውም ተዋዋይ አገሮች ከሚሰጧቸው አስተያየቶች ጋር ሪፖርት ይደረጋሉ፡፡

## ክፍል ሦስት

## አንቀጽ 46

ስምምነቱ ሁሉም አገሮች እንዲፈርሙት ክፍት ይሆናል።

## አንቀጽ 47

ስምምነቱ መጽደቅ ያስፈልገዋል። የማጽደቂያዎቹ ሰነዶች በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ጸሐፊ ዘንድ ይቀመጣሉ።

## አንቀጽ 48

ስምምነቱ ማንኛውም አገር እንዲቀበለው ክፍት ሆኖ ይቆያል። የመቀበያዎቹ ሰነዶች በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ጸሐፊ ዘንድ ይቀመጣሉ።

## አንቀጽ 49

1. ሃያኛው የስምምነቱ ማጽደቂያ ወይም መቀበያ ሠነድ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ጸሐፊ ዘንድ በተቀመጠ በሰላሳኛው ቀን ስምምነቱ የጸና ይሆናል።
2. ሃያኛው የማጽደቂያ ወይም የመቀበያ ሠነድ ከተቀመጠ በኋላ ስምምነቱን ለሚቀበል ወይም ለሚያጸድቅ ለእያንዳንዱ አገር የስምምነቱ ማጽደቂያ ወይም መቀበያ ሰነድ ባስቀመጠ በሰላሰኛው ቀን ስምምነቱ የጸና ይሆናል።

## አንቀጽ 50

1. ማንኛውም ተዋዋይ አገር የማሻሻያ ሃሳቦችን ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ጸሐፊ በጽሑፍ ማቅረብ ይችላል። ከዚህ በኋላ ዋና ጸሐፊው የማሻሻያ ሐሳቦቹ ለተዋዋይ አገሮች እንዲደርሱ ያደርጋል፤ እንዲሁም በቀረቡት የማሻሻያ ሐሳቦች ላይ ለመነጋገርና ድምጽ ለመስጠት የተዋዋይ አገሮች ጉባኤ እንዲዘጋጅ ይፈልጉ እንደሆነ

ሃሳባቸውን እንዲገልፁ ይጠይቃል:: የማሻሻያ ሐሳቦቹ ለተዋዋይ አገሮች እንዲደርሱ በተደረገ በአራት ወር ጊዜ ውስጥ ከተዋዋይ አገሮቹ መካከል ቢያንስ አንድ ሦስተኛው ጉባኤ እንዲዘጋጅ የሚደግፉ ከሆነ ዋና ጸሐፊው በተባበሩት መንግሥታት አዘጋጅነት ጉባኤ ይጠራል:: በጉባኤ ላይ ከተገኙትና ድምጽ ከሰጡት ተዋዋይ አገሮች አብላጫው የደገፉት ማንኛውም የማሻሻያ ሃሳብ እንዲጸድቅ ለጠቅላላ ጉባዔው ይቀርባል::

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ አንድ መሰረት ተቀባይነት ያገኘ የማሻሻያ ሃሳብ በጠቅላላ ጉባዔው ሲጸድቅና ከተዋዋይ አገሮች መካከል ሁለት ሦስተኛው ሲቀበሉት የጸና ይሆናል::
3. አንድ የማሻሻያ ሃሳብ በሚጸናበት ጊዜ በተቀበሉት አገሮች ላይ አስገዳጅነት ይኖረዋል፤ ሌሎች ተዋዋይ አገሮች በስምምነቱ ድንጋጌዎችና ቀደም ሲል በተቀበሏቸው ማሻሻያዎች ብቻ ይገደዳሉ::

## አንቀጽ 51

1. አገሮች ስምምነቱን ሲያጸድቁ ወይም ሲቀበሉ ያላቸውን ተአቅቦ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ጸሐፊ በጽሑፍ ተቀብሎ ለሁሉም አገሮች እንዲደርሱ ያደርጋል፡፡
2. ከዚህ ስምምነት ዓላማዎች ጋር የማይጣጣም ተአቅቦ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡
3. ተአቅቦ ለዋና ጸሐፊው በሚላክ ማስታወቂያ በማናቸውም ጊዜ ማንሳት ይቻላል፤ ዋና ጸሐፊውም ይህንኑ ጉዳይ ለሁሉም አገሮች ያሳውቃል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ማስታወቂያ ለዋና ጸሐፊው ከደረሰበት ቀን አንስቶ ውጤት ይኖረዋል፡፡

## አንቀጽ 52

አንድ ተዋዋይ አገር ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ጸሐፊ በጽሑፍ በማስታወቅ ስምምነቱ እንዳይጸናበት ማድረግ ይችላል፡፡ ስምምነቱ እንዳይጸና የማድረጊያው ማስታወቂያ ውጤት የሚኖረው ዋና ጸሐፊው ዘንድ ከደረሰ ከአንድ ዓመት በኋላ ነው፡፡

## አንቀጽ 53

ስምምነቱ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ጸሐፊ ዘንድ ይቀመጣል፡፡

## አንቀጽ 54

የዚህ ስምምነት ዋና ቅጂ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ጸሐፊ ዘንድ ይቀመጣል፡፡ የዐረብኛ፣ የቻይንኛ፣ የእንግሊዝኛ፣ የፈረንሳይኛ፣ የራሺኛና የእስፓኚኛ ቅጂዎች እኩል እውቅና ይኖራቸዋል፡፡

# ሁሉም ዓይነት የዘር ልዩነቶች ለማስወገድ የተደረገ ዓለም አቀፍ ስምምነት

ይህንን ስምምነት የተቀበሉ አገሮች፣

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ቻርተር በተፈጥሮአዊ የሰው ልጅ ክብርና እኩልነት መርሆዎች መመስረቱን፣ እንዲሁም ሁሉም የተባበሩት መንግስታት ድርጅት አባል አገሮች ድርጅቱ የተመሰረተበት ዓላማ ማለትም ምንም ዓይነት የዘር፣ የቀለም፣ የፆታ፣ የቋንቋ ወይም የሃይማኖት ልዩነት ሳይደረግ የማንኛውም ሰው ሰብአዊ መብቶችና መሰረታዊ ነፃነቶች በዓለም አቀፍ ደረጃ ለማስከበርና ለማረጋገጥ ከድርጅቱ ጋር በመተባበር በግልና በጋራ እርምጃ ለመውሰድ የገቡትን ቃል ኪዳን ግምት ውስጥ በማስገባት፣

የሰብአዊ መብቶች ዓለም አቀፍ መግለጫ ሁሉም ሰብአዊ ፍጡር ነፃ መሆኑን፣ እኩል ሰብአዊ ክብርና መብቶች ተጎናፅፎ መወለዱን፣ ማንኛውም ሰው ምንም ዓይነት የዘር፣ የቀለም ወይም የማህበራዊ ኑሮ

ደረጃ ማበላለጥ ሳይደረግበት በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌ የሰፈሩ መብቶች መጎናፀፍ እንዳለበት መደንገኑን በመገንዘብ፣

ሁሉም የሰው ልጆች በሕግ ፊት እኩል መሆናቸው፣ አድልዎ እንዳይደርስባቸውና አደልዎ እንዲፈፀምባቸው ግፊት እንዳይደረግባቸው እኩል የህግ ከለላ መጎናፀፍ እንዳለባቸው በመረዳት፣

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት በማንኛውም ቦታ በማንኛውም መልኩ የሚከሰት ቅኝ አገዛዝና ከሱ ጋር የተሳሰረሩ ሁሉም የአድልዎና የማበላለጥ መልኮች ማውገዙን፣ እ.ኤ.አ ዲሰምበር 14 ቀን 1960 ዓ/ም የወጣውና የተባበረሩት መንግስታት (አጠቃላይ ጉባኤ ውሳኔ 1514 /XV/) በቅኝ ግዛት ስር የሚገኙ አገሮችና ህዝቦች ነፃነት የሚያጎናፅፈው መግለጫ፣ እነዚህ ህዝቦች ባስቸኳይና ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ነፃነታቸው እንዲቀዳጁ ማረጋገጡን በይፋ ማወጁን ግምት ውስጥ በማስገባት፣

እ.ኤ.አ ኖቨምበር 20 ቀን 1963 ዓ/ም ሁሉም ዓይነት የዘር ልዩነቶች ለማስወገድ የወጣው የተባበሩት መንግስታት ድርጅት አዋጅ (አጠቃላይ ጉባኤ ውሳኔ 1904 /XVII/) የዘር ልዩነት ከሁሉም መልኮቹና

መገለጫዎቹ ከመላው ዓለም ባፋጣኝ እንዲወገድና የሰው ልጅ ተፈጥሮአዊ ክብር እንዲጠበቅና ዋስትና እንዲያገኝ በይፋ ማረጋገጡን በመገንዘብ፣

በዘር ልዩነት የተመሰረተ የበላይነት መርሆ በሳይንስ ረገድ ስህተት፣ በሞራል በኩል የተወገዘ፣ በማሕበረሰብ ረገድም ኢ-ፍትሃዊና አደገኛ መሆኑ እና በፅንሰ ሃሳብም ሆነ በተግባር ለዘር ልዩነት መነሻ የሚሆን ህጋዊ መሰረት የሌለ መሆኑን በማመን፣

በዘር፣ በቀለም ወይም በትውልድ ሃረግ በመመስረት በሰዎች መካከል የሚፈጠር አድልዎ በአገሮች መካከል በወዳጅነት የተመሰረተ ሰላማዊ ግንኙነት እንዳይኖር የሚያደናቅፍ፣ እንዲሁም በህዝቦች መካከል መኖር የሚገባውን ሰላምና መረጋጋት የሚያደፈርስ ከመሆኑም በላይ በአንድ አገር ውስጥ የሚኖሩ ዜጎች አንድነት የሚቃረን መሆኑን በማረጋገጥ፣

የዘር ገደብ ከሁሉም የሰው ልጅ እሴቶች ጋር እንደሚቃረን በማመን፣

እስካሁን ድረስ በግልፅና በተጨባጭ የሚንፀባረቁትንና በአንዳንድ የዓለም አካባቢዎችና የመንግስት ፖሊሲዎች የሚታዩት በዘር የበላይነት

ወይም ጥላቻ የተመሰረቱ እንደ የአፓርታይድ ፖሊሲዎች፣ አድልዎና ማበላለጥ የመሳሰሉት የዘር ልዩነቶች አሳሳቢ መሆናቸውን በመረዳት፣

ሁሉም የዘር ልዩነት ዓይነቶችና መገለጫዎች በአስቸኳይ ለማስወገድ የሚያስችሉ ተገቢ እርምጃዎች መውሰድና የዘር ልዩነት መርሆዎችና ተግባሮች በመዋጋት በሰው ልጅ ዘሮች መካከል መግባባት የሰፈነበት፣ ከማንኛውም ዓይነት የዘር ልዩነትና አደልዎ ነፃ የሆነ የዓለም አቀፍ ማህበረሰብ ለመገንባት ያለው ዝግጁነት በመግለፅ፣

የዓለም አቀፍ የስራ ድርጅት እ.ኤ.አ በ1958 ዓ/ም ባወጣው በስራና በስራ ቅጥር ሂደት የሚያጋጥም ልዩነት የሚመለከት ቃል ኪዳን እና የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የትምህርት፣ የሳይንስና የባህል ተቋም እ.ኤ.አ በ1960 ዓ/ም ያወጣው በትምህርት የሚያጋጥም ልዩነት የሚያስወግድ ቃል ኪዳን ግምት ውስጥ በማስገባት፣

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ሁሉም ዓይነት የዘር ልዩነቶች ለማስወገድ ባወጣው መግለጫ የሰፈሩት መርሆዎችን ለመተግበርና አስቀድሞ በማፅደቅ አስፈላጊ

ተግባራዊ እርምጃ ለመውሰድ፣ እንደሚከተለው ተስማምተዋል፡፡

## ክፍል አንድ

## አንቀጽ 1

1. በዚህ ስምምነት «የዘር ልዩነት» ማለት ማንኛውም ዓይነት አድልዎ፣ ማግለል፣ መገደብ ወይም ማስበለጥ ወይም በዘር፣ በቀለም፣ በትውልድ፣ በብሄር ወይም በዘር ሃረግ በመመስረት የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የማሕበራዊ፣ የባህላዊ ወይም በማንኛውም የሕብረተሰብ የኑሮ መስክ ያሉት ሰብአዊ መብቶችና መሰረታዊ ነፃነቶች በእኩልነት የማግኘትና የመጠቀም ዕድል የመፃረር ዓላማ ያለው ተግባር ይገልፃል፡፡
2. ይህ ስምምነት በዜጎችና ዜጎች ባልሆኑ ሰዎች መሃከል አድልዎ፣ ማግለል ወይም ገደብ ባስቀመጠ የቃል ኪዳኑ ፈራሚ በሆነ አገር ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡
3. የዚህ ስምምነት አንቀጾች የስምምነቱ ፈራሚ የሆኑ አገሮች አገራዊ ማንነትና በትውልድ ወይም በሕግ

ዜግነት ማግኘት በሚመለከት ለሚያወጧቸው ሕጎች በሚቃረን መልኩ በፍፁም አይተረጎሙም። ይህ የሚሆነው ግን አገሮቹ የሚያወጧቸው ሕጎች የአንዱን ወገን ዜግነት የማግለል ዓላማ የሌላቸው ከሆኑ ነው።

4. አንድ የተወሰነ ዘር ወይም የጎሳ ስብስብ ወይም ግለሰቦች ሰብአዊ መብቶቻቸው እና መሰረታዊ ነፃነታቸው በእኩልነት እንዲያገኙ በማቀድ ብቻ ለእነኝህ የጎሳ ስብስብ ወይም ግለሰቦች ተብሎ የሚደረግ ልዩ ድጋፍ እንደ የዘር ልዩነት አይወሰድም፣ ይሁን እንጂ ይህ ልዩ ድጋፍ ለተለያዩ የጎሳ ስብስብ የተለያዩ መብቶች በሚያጎናፅፍ መልኩ መተግበር የለበትም ብቻ ሳይሆን፤ ይህ ልዩ ድጋፍ የታለመለት ግብ ከመታ በኋላ መቆም አለበት።

## አንቀጽ 2

1. ይህን ስምምነት የተቀበሉ አገሮች የዘር ልዩነትን በማውገዝ በማንኛው መልኩ የሚገለፅ የዘር ልዩነት ለማስወገድ የሚያስችል ፖሊሲ በተቻለ መጠንና

በአስቸኳይ በመንደፍ በሰው ልጅ ዘሮች መካከል መቻቻል ለማስፈን፤

ሀ/ ይህንን ስምምነት የተቀበሉ አገሮች በሰዎች፣ በሰዎች ስብስብ ወይም ተቋሞች መካከል ልዩነት የሚፈጥር እርምጃ አይወስዱም ወይም ተግባር አያካሂዱም፤ የአገራቸው ወይም ግዛታቸው መንግስታዊ ባለስልጣናት እና መንግስታዊ ተቋማት ቃል-ኪዳኑን የሚፃረር ተግባር አይፈፅሙም፤

ለ/ ይህንን ስምምነት የተቀበሉ አገሮች የዘር ልዩነት የሚያካሂዱ ሰዎችን ወይም ተቋማትን አይደግፉም፣ አይረዱም ወይም ከላላ አይሰጡም።

ሐ./ ይህንን ስምምነት የተቀበሉ አገሮች መንግስታዊ፣ አገራዊ ወይም አካባቢያዊ ፖሊሲዎች ለማስተካከል፣ እንዲሁም የዘር ልዩነት የሚፈጥሩና የሚያስፋፉ ሕጎችና መመሪያዎች ለማሻሻል፣ ለመሰረዝ ወይም ለመሻር የሚያግዙ ተገቢ እርምጃዎች መውሰድ አለባቸው፣

መ/ ይህንን ስምምነት የተቀበሉ አገሮች በሰዎች፣ በቡድኖች ወይም በተቋሞች የሚካሄድ የዘር ልዩነት ለመግታትና ለማስወገድ ማንኛውም ዓይነት ጥረት ማካሄድ አለባቸው:: አስፈላጊ ሆኖ በተገኘበት ወቅትም ሕግ ማውጣት አለባቸው፣

ሠ/ ይህንን ስምምነት የተቀበሉ አገሮች አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ ውሁድ ብዝሃ ዘር የያዙ ድርጅቶችና እንቅስቃሴዎች ለማበረታታት፣ እንዲሁም በሰው ልጅ ዘሮች መካከል የሚፈጠሩ አጥሮች ለማስወገድና የዘር ልዩነት ለማስቀረት የተለያዩ ጥረቶች ያካሂዳሉ::

2. ይህንን ስምምነት የተቀበሉ አገሮች በግዛታቸው ውስጥ የሚኖሩ ጎሳዎች እና ግለሰቦች ሰብአዊ መብቶቻቸውና መሰረታዊ ነፃነታቸው በተሟላ መንገድና በእኩልነት እንዲጠቀሙ የማሕበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ባህላዊ እና ሌሎች ጥቅሞቻቸውና እድገታቸው የሚያረጋግጡ የተለዩና ተጨባጭ እርምጃዎች መውሰድ አለባቸው:: እነዚህ እርምጃዎች ለተለያዩ ጎሳዎች አኩል ያልሆኑ እና የተለያዩ መብቶች የሚያጎናፅፉ መሆን የለባቸውም::

እንዲሁም መነሻ ያደረጉት ዓላማ ግቡን ከመታ በኋላ ማቋረጥ አለባቸው።

## አንቀጽ 3

ይህንን ስምምነት የተቀበሉ አገሮች በተለይም የዘር አድልዎና አፓርታይድ እንዲያወግዙና የዘር ልዩነት የሚያስከትል ተግባርና ባህሪ በግዛታቸው ውስጥ እንዳይንሰራፉ መከላከል፣ መግታትና ማስወገድ አለባቸው።

## አንቀጽ 4

ይህንን ስምምነት የተቀበሉ አገሮች የአንድ ጎሳ ወይም የሰዎች ስብስብ የቀለም ወይም ብሄራዊ አመጣጥን የበላይነት የሚሰብክ ወይም በማንኛውም መልኩ የዘር ጥላቻና ልዩነት የሚያራምድ ፕሮፓጋንዳና ተቋም ማውገዝ አለባቸው። እንዲህ ዓይነቱን ቅስቀሳና ተግባር የሚያስወግዱ ገምቢ ሕጎች ባስቸኳይ በማርቀቅ ከሰብአዊ መብቶች አለም አቀፋዊ መግለጫ እና በዚሁ ስምምነት አንቀጽ 5 ከሰፈሩት መብቶች ጋር የተሳሰሩ

ደምቦች መንደፍ አለባቸው። ከሚቀረፁት ደምቦች መካከል፣

ሀ/ በዘር የበላይነት እና ጥላቻ ላይ በመመስረት የሚሰራጭ ቅስቀሳና በዘር ልዩነት የሚመሰረት ማነሳሳት በሕግ የሚያስቀጣ ወንጀል መሆኑን የሚገልፅ ሕግ መደንገግ፣ እንዲሁም የማንኛውም ዘር ወይም የሰዎች ስብስብ ቀለም ወይም ብሄራዊ ምንጭ የሚፃረር ተግባርና ዓመፅ ወይም ማነሳሳት የሚቃወም፣ ዘረኛ እንቅስቃሴዎችን መደገፍና የገንዘብ እርዳታ ማድረግ ወንጀል መሆኑን የሚያስገነዝብ ሕግ መቅረጽ፣

ለ/ የዘር ልዩነት የሚያራምዱና የሚያነሳሱ፣ እንዲሁም የተደራጁና ማንኛውም ዓይነት የዘር ፕሮፓጋንዳ የሚያስፋፉ ተቋሞች ማገድና ሕገ ወጥ መሆናቸውን ማወጅ፣ በእንደነዚህ ዓይነቶቹ ተቋሞችና እንቅስቃሴዎች ተሳታፊ መሆን በሕግ የሚያስቀጣ ወንጀል መሆኑን እውቅና መስጠት አለባቸው።

ሐ/ የመንግስት ባለስልጣናት ወይም የመንግስት ተቋሞች የዘር ልዩነት እንዲያራምዱና እንዲያነሳሱ መፍቀድ የለባቸውም።

# አንቀጽ 5

በዚሁ ስምምነት አንቀጽ 2 ከሰፈሩት መሰረታዊ ግዴታዎች በተጣጣመ መልኩ ይህንን ስምምነት የተቀበሉ አገሮች ማንኛውም ዓይነት የዘር ልዩነት ለመከላከልና ለማስወገድ፣ እንዲሁም የዘር፣ የቀለም፣ የብሄር ወይም የትውልድ ሃረግ ማበላለጥ ሳይደረግበት ማንኛውም ሰው በሕግ ፊት በእኩልነት የሚታይበት ሁኔታ ለመፍጠርና የሚከተሉት መብቶች እንዲጎናፀፍ ተገቢ እርምጃ ይወስዳሉ።

ሀ/ በዳኝነት ተቋማት እና በማንኛውም የፍትህ አስተዳደር አካላት ፊት በእኩልነት የመስተናገድ መብት፣

ለ/ ከመንግስት ባለስልጣን፣ ከግለሰብ፣ ከሰዎች ስብስብና ከተቋም ለሚደርስ ጥቃትና የአካል ጉዳት የመንግስት ጥበቃ የማግኘትና የግል ፀጥታ የማግኘት መብት፣

ሐ/ ፖለቲካዊ መብት በተለይ ደግሞ ሁሉ አቀፍና እኩል ተሳትፎ በሚያረጋግጡ ምርጫዎች በመራጭነትና ተመራጭነት የመሳተፍ መብት፣ በሁሉም የመንግስት አስተዳደር ደረጃዎች

የመሳተፍና በሁሉም ደረጃ በሚገኙ ህዝባዊ ጉዳዮች እኩል አገልግሎት የማግኘት መብት፣

መ/ ሌሎች የሲቪል መብቶች፤ በተለይም

i. በአገሩ የግዛት ክልል ውስጥ በነፃነት የመንቀሳቀስና የመኖር መብት፣
ii. ከየትኛውም አገር፣ ከራስ አገርም ጭምር ለቆ ለመውጣትና ወደ ራስ አገር ተመልሶ የመግባት መብት፣
iii. ዜግነት የማግኘት መብት፣
iv. የማግባትና የትዳር ጓደኛዉን ሰው የመምረጥ መበት፣
v. በግል ወይም ከሌሎች ጋር በመሆን ንብረት የማፍራት መብት፣
vi. የውርስ መብት፣
vii. የማሰብ፣ የህሊናና የሃይማኖት ነፃነት መብት፣
viii. የራስ አመለካከት የመያዝና የመግለፅ መብት፣
ix. ሰላማዊ ስብስብ የማካሄድና የመደራጀት ነፃነት መብት፣

ሠ/ ኢኮኖሚያዊ፣ ማሕበራዊና ባህላዊ መብቶች፤ በተለይም

i. የመስራት፣ በነፃ ፍላጎት የመቀጠር፣ ፍትሃዊና አመቺ የስራ ሁኔታ እና የስራ ዋስትና የማግኘት፣ ለእኩል ስራ እኩል ክፍያ የማግኘት፣ እንዲሁም ፍትሃዊና ተመጣጣኝ ክፍያ የማግኘት መብቶች፣

ii. የሰራተኛ ማህበራት የማቋቋምና የመደራጀት መብት፣

iii. የመኖርያ ቤት የማግኘት መብት፣

iv. መንግስታዊ የሕክምና አገልግሎት፣ የጤና እንክብካቤ ማሕበራዊ ዋስትና እና ማሕበራዊ አገልግሎት የማግኘት መብት፣

v. ትምህርትና ስልጠና የማግኘት መብት፣

vi. በባህላዊ እንቅስቃሴዎች በእኩልነት የመሳተፍ መብት፣

ረ. መጓጓዣ፣ ሆቴል፣ ምግብ ቤት፣ ቡና ቤት፣ ትያትር ቤት፣ የመናፈሻ ቦታ በመሳሰሉት ህዝብን ለማገልገል የተቋቋሙ አገልግሎት ሰጪዎች ከሚሰጡት አገልግሎት በእኩልነት የመጠቀም መብት፣

## አንቀጽ 6

ይህንን ስምምነት የተቀበሉ አገሮች ስምምነቱን የሚቃረን ሰብአዊ መብቶችንና መሰረታዊ ነፃነቶችን የሚጋፋ ማንኛውም የዘር ልዩነት ተግባር ለመመከት የሚያስሷልዋቸው ብሄራዊ የዳኝነት ተቋሞች ሌሎች የመንግስት ተቋማት በመጠቀም በግዛታቸው ክልል ውስጥ የማንኛውም ሰው ዋስትና ለማረጋገጥ የሚያስችላቸው ስርዓት መዘርጋት አለባቸው። ከዚህ በተጨማሪ በደረሰው ጉዳትና መድልዎ መጠን ከችሎቶቹ ፍትሃዊና በቂ ካሳ የማግኘት መብት መረጋገጥ አለበት።

## አንቀጽ 7

ይህንን ስምምነት የተቀበሉ አገሮች ወደ ዘር መድልዎ የሚያመሩ የተሳሳቱ አመለካከቶችን ለመመከት ብሎም በአገሮች ወይም የዘርና የጎሳ ስብስቦች መካከል መቻቻልንና ወዳጅነትን ለማስፈን፣ እና የተባበሩት መንግስታት ቻርተር፣ ዓለም አቀፋዊ

የሰብዓዊ መብቶች መግለጫና ሁሉንም ዓይነት የዘር መድለዎችን ለማስወገድ የወጣው የተባበሩት መንግስታት መግለጫና የዚህ ስምምነት ዓላማዎችንና መርሆዎችን ለማራመድ በተለይም በትምህርት፣ ባህልና መረጃ መስኮች አፋጣኝና ውጤታማ እርምጃዎችን ይወስዳሉ፡፡

## ክፍል ሁለት

## አንቀጽ 8

1. በዘር ላይ የተመሰረተ መድልዎን ለማስወገድ የሚሰራ ከዚህ በኋላ ኮሚቴው ተብሎ የሚጠቀስ ኮሚቴ ይቋቋማል ፡፡ ይህ ኮሚቴ የስምምነቱ ፈራሚ ከሆኑት አገሮች ዜጎች መካከል በአገሮቹ የሚመረጡ፣ በከፍተኛ ስነ ምግባርና ገለልተኛነት የሚታወቁ 18 ባለሙያዎችን ያቅፋል፡፡ እነኝህ አባላት ራሳቸውን በመወከል በግል የሚያገለግሉ ሲሆን፣ በሚመረጡበት ወቅትም ጂኦግራፊያዊ ስብጥርና የተለያየ የስልጣኔ እንዲሁም ዋና ዋና

የህግ ስርዓቶችን የሚወክሉ መሆናቸውን ግምት ውስጥ ይገባል፡፡

2. የኮሚቴው አባላት ስምምነቱን ከተቀበሉ አገሮች ከቀረቡ እጩዎች መሃል በምስጢራዊ የምርጫ ስርዓት ይመረጣሉ፡፡ እያንዳንዱ ይህንን ቃል ኪዳን የተቀበለ አገር ከዜጎቹ መካከል አንድ መጠቆም ይቻላል፡፡

3. የመጀመርያው ምርጫ ስምምነቱ ከፀናበት ቀን ጀምሮ ከስድስት ወራት በኋላ ይካሄዳል፡፡ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ ለእያንዳንዱ ምርጫ ቢያንስ ሶስት ወር ሲቀረው የሚመለከታቸው የ ስምምነቱ አባል አገሮች በሁለት ወር ውስጥ እጩዎቻቸውን እንዲገልፁ በደብዳቤ ይጠይቃቸዋል፡፡ ዋና ፀሐፊው የእጪዎች ስም ዝርዝር በፊደል ቅደም ተከተል በማዘጋጀት የተወከሉበት አገር ጨምሮ በመጥቀስ ስምምነቱን ለተቀበሉ አገሮች ያሳውቃል፡፡

4. ዋና ፀሐፊው በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፅሕፈት ቤት በሚጠራው የ ስምምነቱ አባል አገሮች ስብሰባ የኮሚቴው አባላት ምርጫ ይካሄዳል፡፡ የስምምነቱ ፈራሚ ከሆኑት አገሮች

መካከል ሁለት ሶስተኛ በስብሰባው ከተገኙ ምልአተ ጉባኤ ይሆናል፡፡ የኮሚቴው አባላት ሆኖው የሚመረጡትም በስብሰባው በመገኘት ድምፅ ከሰጡት የስምምነቱ ፈራሚ አገሮች ከፍተኛው እና ፍፁም አብላጫ ድምፅ ያገኙት ይሆናሉ፡፡

5. ሀ/ የኮሚቴው አባላት ለአራት ዓመታት የስራ ጊዜ ያገለግላሉ፡፡ በመጀመሪያ ምርጫ ከተመረጡት ውስጥ የዘጠኙ አባላት የስራ ጊዜ ግን ሁለት ዓመት ብቻ ይሆናል፡፡ የመጀመሪያው ምርጫ እንደተካሄደ የዘጠኙ የኮሚቴው አባላት ማንነት የኮሚቴው ሊቀመንበር በሚያወጣው ዕጣ ይለያል፡፡

   ለ/ ከኮሚቴው አባላት ሰው ሲጓደል፣ በዕጩነት ያቀረበው አባል አገር ከዜጎቹ መካከል አንድ ባለሞያ መርጦ ይመድባል፡፡ ይህ ምደባ የሚፀናው ኮሚቴው ከተቀበለው ነው፡፡

6. ይህንን ስምምነት የተቀበሉ አገሮች፣ የኮሚቴው አባላት በኮሚቴው የተሰጣቸው የስራ ሃላፊነት በሚያከናውኑበት ወቅት የሚያስፈልጋቸው ወጪ የመሸፈን ግዴታ አለባቸው፡፡

## አንቀጽ 9

1. ይህንን ስምምነት የተቀበሉ አገሮች የስምምነቱን አፈፃፀም በሚመለከት የወሰዱዋቸውን ህግ የማውጣት፣ የሚሰጡት የዳኝነት፣ የአስተዳደር ወይም ሌሎች እርምጃዎች የሚገልፅ ዘገባ በኮሚቴው እንዲታይ ለተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ ያቀርባሉ፡፡ ይህንን የሚፈፅሙትም፣

   ሀ/ ስምምነቱ ለሚመለከተው አገር አስገዳጅ መሆን ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ፣

   ለ/ ከዚያ በኋላ የሚቀርቡ ዘገባዎች በየሁለት ዓመትና ኮሚቴው ዘገባ እንዲቀርብለት በሚጠይቅበት ጊዜ ይሆናል፡፡ ቃል ኪዳኑ የተቀበሉ አገሮች ተጨማሪ መረጃ እንዲያቀርቡ ኮሚቴው ጥያቄ ማቅረብ ይችላል፡፡

2. ኮሚቴው የስራ እንቅስቃሴውን የሚዳስስ ዘገባ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ አማካኝነት በየዓመቱ ለተባበሩት መንግስታት

ድርጅት ጠቅላላ ጉባኤ ያቀርባል፡፡ በሪፖርቱ ስምምነቱን ከተቀበሉ አገሮች ያገኘው መረጃና ሪፖርት በመመርመር የራሱ አስተያየትና የመፍትሄ ሃሳብ ሊያካትት ይችላል፡፡ አስተያየቶችና አጠቃላይ የመፍትሄ ሃሳቦች፣ የስምምነቱ ፈራሚ አገሮች የሰጡት አስተያየት ካለም በማከል ነው ለጠቅላላ ጉባኤው የሚቀርቡት፡፡

## አንቀጽ 10

1. ኮሚቴው የራሱን የስነ ስርዓት ሕግ ያወጣል፡፡
2. ኮሚቴው ለሁለት ዓመት የሚያገለግሉ ስራ አስፈፃሚዎች ይመርጣል፡፡
3. ለኮሚቴው አስፈላጊ የሆነ አገልግሎት የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ ፅሕፈት ቤት ያቀርብለታል፡፡
4. በመደበኛነት የኮሚቴው ስብሰባዎች በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፅሕፈት ቤት ይካሄዳሉ፡፡

## አንቀጽ 11

1. ይህንን ስምምነት የተቀበለ አንድ አገር ስምምነቱን የተቀበለ ሌላ አገር የስምምነቱን ድንጋጌዎች ተግባራዊ አላደረገም የሚል እምነት ከያዘ ጉዳዩን ለኮሚቴው ማቅረብ ይችላል፡፡ ኮሚቴው በበኩሉ የቀረበለትን ቅሬታ ለሚመለከተው አገር ያስተላልፋል፡፡ ተቀባዩ አገርም ቅሬታው ከደረሰው ጊዜ ጀምሮ በሶስት ወራት ውስጥ ጉዳዩን የሚያብራራና የተወሰደ የማስተካከያ እርምጃ ካለም በፅሑፍ ለኮሚቴው ያሳውቃል፡፡
2. የመጀመሪያው ቅሬታ የስምምነቱን ድንጋጌዎች አላከበረም ለተባለው አገር ከደረሰ ከቀረበ በኋላ በስድስት ወራት ውስጥ በሁለትዮሽ ድርድር ወይም በሌላ ስነ ስርዓት ሁለቱን ጉዳዩ የሚመለከታቸው አገሮች የሚያግባባ መፍትሔ ካልተገኘ ከሁለቱም አንዱ ጉዳዩን በድጋሚ ወደ ኮሚቴው የማቅረብና ስለጉዳዩ ለሌላኛው አገር የማሳወቅ መብት አለው፡፡
3. ኮሚቴው በዚሁ ዓንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 2 መሰረት በቀረበለት ጉዳይ ላይ ውሳኔ የሚሰጠው፣ የሚመለከተው አገር የዓለም ዓቀፍ ሕግ መርሆዎች

በመከተልና ሁሉንም የመፍትሄ አገባቦች በመጠቀም ለጉዳዩ እልባት ለመስጠት አለመቻሉን ካረጋገጠ በኋላ ነው:: መፍትሄ ለመስጠት የሚወስደው ጊዜ በአእምሮ ግምት ረጅም የሚባል ጊዜ ከሆነ ሕጉ ተፈፃሚነት አይኖረውም::

4. ኮሚቴው የቀረበለት ቅሬታ በሚመለከት ስምምነቱን የተቀበሉ የሚመለከታቸው አገሮች አስፈላጊነት ያለው ተጨማሪ መረጃ እንዲያቀርቡ ጥሪ ያቀርባል::
5. በዚሁ አንቀጽ የተመለከቱ ጉዳዮች በኮሚቴው በሚታዩበት ወቅት ስምምነቱን የተቀበሉና ጉዳዩ የሚመለከታቸው አገሮች በኮሚቴው ስብሰባዎች ድምጽ የመስጠት መብት ሳየኖራቸው የሚሳተፉ ተወካዮች የመላክና የማጣራቱን ሂደት እንዲከታተሉ የማድረግ መብት አላቸው::

## አንቀጽ 12

1. ሀ/ ኮሚቴው አስፈላጊ ናቸው ያላቸው መረጃዎች ከያዘና ካመሳከረ በኋላ ሊቀመንበሩ የኮሚቴው አባላት የሆኑ ወይም ያልሆኑ አምስት ሰዎችን

በአባልነት የያዘ (ከዚህ በኋላ ኮሚሽን በማለት የሚጠቀስ) ጊዜያዊ የሽምግልና ኮሚሽን ይሰይማል፡፡ የኮሚሽኑ አባላት ስምምነቱን በተቀበሉ ባለጉዳይ የሆኑ አገሮች ሙሉ ፈቃድ የሚሰየሙ ይሆናሉ፡፡ ኮሚሽኑ በዚሁ ስምምነት በሰፈሩት መርሆዎች በመመስረት ለጉዳዩ መፍትሄ ለመስጠት በማቀድ ባለ ጉዳይ ለሆኑት አገሮች አገልግሎቱን ይሰጣል፡፡

ለ/ ጉዳዩ የሚመለከታቸው አገሮች በሁሉም ወይም በከፊል የኮሚሽኑ አባላት ምርጫ በሶስት ወራት ውስጥ ካልተስማሙ፣ ኮሚቴው ከራሱ አባላት ውስጥ በምስጢራዊ የምርጫ አካሄድ በሚያካሂደው ምርጫ የሁለት ሶስተኛው ድምፅ ያገኙ ሰዎች የኮሚሽኑ አባላት ሆነው እንዲሰሩ ያደርጋል፡፡

2. የኮሚሽኑ አባላት ራሳቸውን በመወከል ስራቸውን ያከናውናሉ፡፡ የባለጉዳይ አገሮች ዜጎች መሆን የለባቸውም፤ በተጨማሪም ስምምነቱን ያልፈረሙ አገሮች ዜጎች መሆን የለባቸውም፡፡
3. ኮሚሽኑ የራሱ ሊቀ መንበር ይመርጣል፣ የሚመራበት የስነ ስርዓት ደንብም ያወጣል፡፡

4. የኮሚሽኑ ስብሰባ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ጽ/ቤት ወይም ኮሚሽኑ በሚወስነው ሌላ ተስማሚ ቦታ ይካሄዳል፡፡
5. በዚሁ ስምምነት አንቀጽ 10 መሰረት የሚሰጠው የፅሕፈት ቤት አገልግሎት የስምምነቱ ፈራሚ በሆኑት አገሮች መካከል ያለመስማማት ሲኖር ጉዳዩን ለመመርመር ለሚሰየመው ኮሚሽንም አገልግሎት ይሰጣል፡፡
6. የጉዳዩ ባለቤት የሆኑ አገሮች የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ በሚያቀርብባቸው ግምት መሰረት ሁሉንም የኮሚሽኑን ወጪዎች እኩል ይከፍላሉ፡፡
7. አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ በዚሁ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 6 መሰረት የጉዳዩ ባለቤትና የስምምነቱ ፈራሚ የሆኑ አገሮች የወጣውን ወጪ እስከሚተኩ ድረስ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ የኮሚሽኑ አባላት ወጪ የመሸፈን ስልጣን አለው፡፡
8. ለኮሚቴው የደረሰውና በራሱ መንገድ ያጠናቀረው መረጃ ለኮሚሽኑ ይቀርባል፡፡ በተጨማሪም ኮሚሽኑም ጉዳዩ የሚመለከታቸው አገሮች ሌላ

ተጨማሪ መረጃ እንዲያቀርቡ ጥሪ ማቅረብ ይችላል።

## አንቀጽ 13

1. ኮሚሽኑ ጉዳዩን ሙሉ በሙሉ ከመረመረ በኋላ ከክስ አቅራቢዎች ጉዳይ ጋር ግንኙነት ባላቸው የፍሬ ነገር ጭብጦች ላይ፣ ራሱ የደረሰበትን ድምዳሜና ውዝግቡን ለመፍታት የሚጠቅሙ አግባብነት ያላቸው የመፍትሄ ሃሳቦችን ያካተተ ዘገባ በማዘጋጀት ለኮሚቴው ሊቀመንበር ያቀርባል።
2. የኮሚቴው ሊቀመንበር ከኮሚሽኑ የደረሰውን ዘገባ ባለጉዳይ ለሆኑ አገሮች ለያንዳንዳቸው ያስተላልፋል። አገሮቹም በኮሚሽኑ ዘገባ የተቀመጡትን የመፍትሄ ሃሳቦች መቀበላቸውንና አለመቀበላቸውን በሶስት ወራት ውስጥ ለኮሚቴው ሊቀመንበር ማሳወቅ አለባቸው።
3. በዚሁ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 2 ከተጠቀሰው ጊዜ በኋላ የኮሚቴው ሊቀመንበር የኮሚሽኑ ዘገባና የተወዛጋቢ አገሮች መግለጫ በማጣመር ይህንን ስምምነት ለተቀበሉ አገሮች ያስተላልፋል።

## አንቀጽ 14

1. ይህንን ስምምነት በተቀበለ አገር ግዛት ክልል ውስጥ በዚሁ ስምምነት የሰፈሩ መብቶቻችን ተጥሰዋል በማለት ከግለሰቦች ወይ ከቡድኖች የሚቀርብ ክስ ኮሚቴው ተቀብሎ የመመርመር ስልጣን እንዳለው ስምምነቱን የተቀበለ አገር በማንኛውም ጊዜ መግለፅ ይችላል፡፡ ይህንን እውቅና ባልሰጠ አገር የሚቀርብ ክስ በኮሚቴው አይመረመርም፡፡
2. በዚሁ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 1 በተገለፀው መሰረት እውቅና የሰጠ አገር በግዛቱ ክልል ከሚገኙ ግለሰቦችና ቡድኖች የሚቀርቡ በዚሁ ስምምነት የሰፈሩ መብቶቻችን ተጥሰዋል የሚሉትን ክሶች የሚመረምር ብቃት ያለው አገራዊ ተቋም ማቋቋም ይችላል፡፡ ሕጋዊ ተቋሙ በሁሉም አካባቢያዊ መፍትሄዎች መቋጫ ያላገኙ ጉዳዮችን ይመረምራል፡፡
3. በዚሁ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 1 መሰረት የሚሰጥ እውቅና እና በዚሁ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 2 መሰረት የሚቋቋም ተቋም የሚመለከት ሰነድ ጉዳዩ የሚመለከተውና የ ስምምነቱ አባል የሆነ አገር

ለተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ እንዲደርስ ያደረጋል፡፡ ዋና ፀሐፊውም የዚሁ ሰነድ ቅጂዎች የስምምነቱ ፈራሚ ለሆኑት አገሮች እንዲደርስ ያደርጋል፡፡

4. የተመዘገበው ክስ በዚሁ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 2 መሰረት ከሚቋቋመው አካል ጋር ይቀመጣል፣ የክሱ የተረጋገጡ ቅጂዎች አግባብ ባለው አሰራር ለተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ በየዓመቱ ይላካሉ፡፡ የክሶች ይዘት ግን ይፋ አይደረጉም፡፡
5. በዚሁ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 2 የተቋቋመው አካል የሚሰጠው የመፍትሄ ሃሳብ በቂ ነው ብሎ ካላመነ ክስ አቅራቢው በስድስት ወራት ውስጥ ለኮሚቴው ማመልከቻ የማቅረብ መብት አለው፡፡
6. ሀ/ ኮሚቴው የቀረበለትን ክስ የስምምነቱ ሕጎች ጥሰዋል በማለት ክስ የቀረበበት አገር እንዲያውቀው ይልክለታል፡፡ ይሁን እንጂ ክስ ያቀረበው ግለሰብ ወይም ቡዱን ካልፈቀደ ማንነቱ አይገልፅም፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚቴው የከሳሽ ስም የሌለበት ክስ አይቀበልም፡፡

ለ/ ተቀባዩ አገር ጉዳዩን የሚያብራራ ወይም ለጉዳዩ የተሰጠ መፍትሄ ካለ የሚገልፅ ፅሑፍ በሶስት ወራት ውስጥ ለኮሚቴው ያቀርባል፡፡

7. ሀ/ ኮሚቴው ስምምነቱን ከተቀበለ ተከሳሽ አገርና ከከሳሽ በቀረቡለት መረጃዎች በመመስረት የማጣራት ግንኙነት ያካሂዳል፡፡ ከሳሹ በአገሩ ውስጥ የሚገኙት ሁሉም የክስ አቀራረብ ደረጃዎች ሳይጠቀም ክሱን ለኮሚቴው ካቀረበ ኮሚቴው ጉዳዩን አይቀበልም፡፡ ይሁን እንጂ የመፍትሄው ሂደት በአእምሮ ግምት ረጅም ጊዜ ከወሰደ ይህ ህግ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

ለ/ ኮሚቴው በጉዳዩ አስተያየትና የመፈትሄ ሃሳቦች ካለው ለተከሳሹ አገርና ለከሳሹ ያቀርባል፡፡

8. ኮሚቴው ባደረገው ጉዳዩን የማጣራት ግንኙነት ያገኘው ጭማቂ ሃሳብ፣ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም ክስ የቀረበበት አገር የሰጠው ማብራርያና መግለጫ እንዲሁም የራሱ አስተያየትና የመፍትሄ ሃሳቦች ያካተተ ፅሑፍ በሚያቀርበው ዓመታዊ ዘገባ ያካትታል፡፡

9. ኮሚቴው በዚሁ አንቀፅ የተመለከቱ ተግባራትን ማከናወን የሚችለው በዚሁ አንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 1

መሰረት ስምምነቱን ከተቀበሉ አገሮች መካከል ቢያንስ አስሩ እውቅና ከሰጡት ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 15

1. እ.ኤ.አ ዲሰምበር 10 ቀን 1960 ዓ.ም በተባበሩት መንግስታት ድርጅት አጠቃላይ ጉባኤ ውሳኔ ቁጥር 1514 (XV) የተደነገገውና በቅኝ ግዛት ስር የሚገኙት አገሮችና ህዝቦች ነፃነት ያቀዳጀው መግለጫ ተግባራዊነት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በዚሁ የሰፈሩ ሕጎች እኒኝህ ህዝቦች በሌላ የዓለም አቀፍ አሰራር ወይም ልዩ ተልእኮ ባላቸው የተባበሩት መንግስታት ድርጅት አካላት የተጎናፀፉት ክስ የማቅረብ መብት በማንኛውም መንገድ አይገደብም፡፡
2. ሀ/ በዚሁ ስምምነት አንቀፅ 8 ንኡስ አንቀፅ 1 መሰረት የሚቋቋመው ኮሚቴ የአጠቃላዩ ጉባኤ ውሳኔ 1514 (XV) ተግባር ላይ በሚውልባቸው በሞግዚታዊ እና ራስ ገዝ ባልሆነ መስተዳድር የሚተዳደሩ ነዋሪዎች የሚያቀርቡት ክስ ቅጂ ይቀበላል፡፡ ይህንን ክስ ለመመርመርና በዚሁ

ስምምነት የሰፈሩት መርሆዎችና ግቦች በቀጥታ ለመፈፀም ለሚቋቋሙ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት አካላት በክሱ ያለውን አስተያየትና የመፍትሄ ሃሳቦች ያቀርባል።

ለ/ ኮሚቴው በዚሁ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ (ሀ) የተጠቀሱት ግዛቶች ለማስተዳደር የሚሰየሙት ጉዳዩን የሚመለከታቸው የተባበሩት መንግስታት ድርጅት አካላት ከቃል ኪዳኑ ዓላማ ጋር ትስስር ያላቸው የሕግ አውጪ፣ ፍርድ ቤት፣ አስተዳደራዊና ሌሎች ተግባራት በሚመለከት የሚያዘጋጁት ዘገባ ቅጂ ይቀበላል።

3. ኮሚቴው ለተባበሩት መንግስታት ድርጅት አጠቃላይ ጉባኤ በሚያቀርበው ዘገባ ከተባበሩት መንግስታት ድርጅት የተለያዩ አካላት የተቀበለው ክስና ዘገባ፣ እንዲሁም ኮሚቴው በክሱና ዘገባው በመመስረት የሚሰጠው አስተያየት፣ መግለጫና የመፍትሄ ሃሳብ ያካትታል።

4. ኮሚቴው ለስምምነቱ ግቦች አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችና በዚሁ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 2 (ሀ) ከተጠቀሱት ግዛቶች ትስስር ያላቸው ጉዳዮች

በማስመልከት ለተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ መጠየቅ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 16

የዚሁ ስምምነት ዓንቀፆች ከአድልዎና ልዩነት ተያያዥነት ያላቸው ውዝግቦችና ክሶች መፍትሂ ለመስጠት ከሚወጡት ሌሎች ስነ ስርዓቶች በማይቃረን መልኩ ተግባራዊ ይሆናሉ፡፡ ልዩ ተልእኮ የተሰጣቸው የተባበሩት መንግስታት ድርጅት አካላት ከሚያወጡት ስነ ስርዓትና ስምምነቱን የተቀበሉ አገሮች ዓለም አቀፍ ስምምነቶች መሰረት በማድረግ ግጭት ለመፍታት ከሚደነግግዋቸው ስነ ስርዓቶችም አይቃረኑም፡፡

## ክፍል ሶስት

## አንቀጽ 17

1. ይህ ስምምነት፤ የተባበሩት መንግስታት ድርጅትና ልዩ ተልእኮ የተሰጣቸው የተባበሩት መንግስታት ድርጅት አካላት አባል የሆነ፣ የዓለም አቀፍ ፍትሕ ፍርድ ቤት የተመሰረተበት ሕግ የተቀበለ ወይም

በተባበሩት መንግስታት ድርጅት አጠቃላይ ጉባኤ ይህንን ስምምነት እንዲቀበል ጥሪ የቀረበለት ማንኛውም አገር እንዲፈርምበት ክፍት ነው::

2. ይህ ስምምነት ተፈፃሚ የሚሆነው በፈራሚ አገሮች ሲፀድቅ ነው:: የማፅደቂያ ሰነዶቹም በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ ፅ/ቤት ይቀመጣሉ::

## አንቀጽ 18

1. ይህ ስምምነት በአንቀፅ 17 ንኡስ አንቀፅ 1 የተጠቀሱት አገሮች እንዲቀበሉት ክፍት ነው::
2. የመቀበያ ሰነዶችም ለተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ መቅረብ አለባቸው::

## አንቀጽ 19

1. የስምምነቱ ሃያ ሶስተኛው የማፅደቂያ ወይም የመቀበያ ሰነድ ለተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ በሰለሳኛው ቀን ስምምነቱ የፀና ይሆናል::

2. የስምምነቱ ሃያ ሰባተኛው የማፅደቂያ ወይም የመቀበያ ሰነድ ለተባበሩት መንግስታት ድርጅት ከቀረበ በኋላ ስምምነቱን የሚያፀድቁ አገሮች የየራሳቸው የማፅደቂያ ወይም የመቀበያ ሰነድ ከአቀረቡበት ጊዜ ጀምሮ በሰላሳኛው ቀን በስምምነቱ ይገደዳሉ፡፡

## አንቀጽ 20

1. የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ ስምምነቱን የሚቀበሉ አገሮች ስምምነቱን ሲያፀድቁ ወይም ሲቀበሉ ያስመዘገቡት ተአቅቦ ለሌሎች የስምምነቱ ፈራሚ አገሮች ያሳውቃል፡፡ ተአቅቦውን የሚቃወም ማንኛውም አገር መልእክቱ ከደረሰው በኋላ በዘጠና ቀናት ውስጥ እንደማይቀበለው በመግለፅ ለተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ ማሳወቅ አለበት፡፡
2. ከስምምነቱ መሰረታዊ ዓላማና ግብ ጋር በሚቃረን አኳኋን የተመዘገበ ተአቅቦ ተቀባይነት አይኖረውም፤ በስምምነቱ መሰረት የሚቋቋም አካል የስራ

እንቅስቃሴም አያደናቅፍም፡፡ ከፈራሚ አገሮች መካከል ሁለት ሶስተኛው የተቃወሙት ተአቅቦ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

3. የተመዘገበው ተአቅቦ ለተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ ደብዳቤ በመፃፍ አንስቻለሁ ማለት ይቻላል፡፡ ተአቅቦየን አንስቻለሁ የሚለው ደብዳቤ ለተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ ከደረሰ በኋላ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

## አንቀጽ 21

የዚህ ስምምነት ፈራሚ የሆነ አገር አባልነቱን ለማቋረጥ ሲወስን በፅሑፍ ለተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ ያቀርባል፡፡ አባልነቱም የሚቀረው ፅሑፉ ለተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ከአንድ ዓመት በኋላ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 22

በስምምነቱ አተረጓጎም ወይም አፈፃፀም ዙርያ በሁለት ወይም ከሁለት በላይ በሆኑ የስምምነቱ ፈራሚ

አገሮች የሚነሳ ውዝግብ በውይይት ወይም በስምምነቱ በሰፈሩ ስነ ስርዓቶች መፍታት ካልተቻለ የጉዳይ ባለቤት ከሆኑት አገሮች መካከል በአንዱ በኩል ወደ ዓለም አቀፍ የፍትሕ ፍርድ ቤት ለውሳኔ መቅረብ ይችላል፡፡ ይህ መሆን የሚችለው ውዝግብ ውስጥ የገቡት አገሮች በሌላ የአፈታት ስርዓት ለጉዳዩ ዕልባት መስጠት ካልቻሉ ነው፡፡

## አንቀጽ 23

1. ስምምነቱን የተቀበለ ማንኛውም አገር በማንኛውም ጊዜ ለተባበሩት መንግስታት ድርጅት በሚፅፈው ደብዳቤ በኩል በስምምነቱ የማሻሻያ ሃሳብ ማቅረብ ይችላል፡፡
2. የተባበሩት መንግስታት ድርጅት አጠቃላይ ጉባኤ የማሻሻያ ሃሳብ ጥያቄ የሚያስተናግድበት ስርዓት ካለው በዛ በኩል ይወሰናል፡፡

## አንቀጽ 24

የተባበሩት መንግስታት ዋና ፀሐፊ በዓንቀፅ 17 ንኡስ ዓንቀፅ 1 ለተመለከቱት ሁሉም አገሮች ስምምነቱን በሚመለከት የሚከተሉት ጉዳዮች እንዲያውቁ ያደርጋል፣

ሀ/ በአንቀፆቹ መሰረት የማካሄዱ ፊርማዎች፣ የማፅደቂያና መቀበያ ሰነዶች፣

ለ/ በአንቀፅ 19 መሰረት ስምምነቱ የሚፀናበት ቀን፣

ሐ/ በአንቀፅ 14፣ 20 እና 23 መሰረት የደረሱት መልእክቶችና መግለጫዎች፣

መ/ በአንቀፅ 21 መሰረት የሚቀርብ አባልነት የማቋረጥ ውሳኔ፣

## አንቀጽ 25

1. በቻይንኛ፣ በእንግሊዝኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ ሩስያኛና እስፓኚኛ የተዘጋጁ የስምምነቱ ሰነዶች ቅጂዎች እኩል ተቀባይነት ያላቸው ሲሆን፣ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት መዝገብ ቤት ይቀመጣሉ።

**2. የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ ትክክል መሆናቸው የተረጋገጡ የስምምነቱ ቅጂዎች በዚሁ የስምምነት አንቀፅ 17 ንኡስ አንቀፅ 1 ለተመለከቱት ክፍሎች ያሰራጫል፡፡**